በመጽሐፉ ሽፋን ላይ የተገኘውን ሥዕል የሚያሳየው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በዐረብኛ ቋንቋ ነው። ቃሉም እንደሚከተለው ነው:-

በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥
　　መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።
የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥
　　መጽናናትን ያገኛሉና።
የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥
　　ምድርን ይወርሳሉና።
ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥
　　ይጠግባሉና።
የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥
　　ይማራሉና።
ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥
　　እግዚአብሔርን ያዩታልና።
የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥
　　የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።
ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥
　　መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

ማቴዎስ 5:3-10

## ማውጫ ገጽ


መግቢያ.................................... 1

1. መጽሐፍ ቅዱስ፡- ምንድ ነው .................. 3

2. መጽሀፍ ቅዱስ ከየት መጣ?........................ 10

3. መጽሐፍ ቅዱስ ሊታመን የሚችለው ለምንድነው? (1)........ 14

4. መጽሐፍ ቅዱስ ሊታመን የሚችለው ለምንድነው? (2)........ 20

5. እግዚአብሔር ስለ ራሱ እናውቀው ዘንድ የገለጠልን ነገሮች...... 24

6. እግዚአብሔር ስለ ሰው የገለጠው ነገር.................... 29

7. እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት የገለጠው ነገር................ 33

8. የእግዚአብሔር ሕግ................................ 37

9. የኢየሱስ ሕይወት................................ 41

10. የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ............................45

11. የእግዚአብሔር መንግሥት........................ 51

12. የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ መሆን እንዴት እንደሚቻል........55

13. የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ የሕይወት አኗኗር ስልት..........60

14. ኢየሱስ፡- ከነቢይ በላይ ነው........................ 63

15. መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ........................ 70

16. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ................................73

17. የእግዚአብሔር ሰዎች በሕይወት ውሥጥ ያላቸው ዓላማ.......76

18. የእግዚአብሔር ሕዝቦች የወደፊት ጉዳይ ዋስትና ያለው ነው።... 78

# «አል-ኪታብ» ማለት መጽሐፍ ማለት ነው

## መግቢያ

ውድ አንባቢ፡-

አስቀድመን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እምነት የሚያስተምረውን ይህንን ጥናት ለመከታተል በመፍቀድህ የተሰማንን ደስታ እንገልጽልሃለን። በ13ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የኖረው ጃልአሉል ዲን ሩሚ በመባል የታወቀው የእስልምና ባለቅኔ በአንድ ጨለማ ክፍል ይኖር ስለነበረ ስለአንድ ዝሆን ታሪክ እንዲህ ሲል ተናግሯል። ይህንን ዝሆን ሰዎች ወደ አረብ አገር ይዘውት በመጡ ጊዜ ዝሆኑን ለማየት በርካታ ሰዎች ተሰበሰቡ ሆኖም የተጠበቀበት ሥፍራ እንዲጋጣሚ ጨለማ ሥፍራ ስለነበር ዝሆኑን ለማየት የመጡ ሰዎች ዝሆኑን «ማየት» የሚችሉት ወደጨለማ ክፍል ገብተው ዝሆኑን በመዳሰስ ነበር። ከእነዚህ ሰዎች አንዱ የዝሆኑን ኩምቢ ዳሰሰና ዝሆን ትልቅ ቧንቧ ይመስላል አለ። ሌላው ደግሞ ጆሮውን ዳሰሰና ማርገብገቢያ ይመስላል አለ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ ጎንና ጎኑን ብቻ ስለዳሰሱ ግድግዳ ነው የሚመስለው ብለው ተከራከሩ። ሌሎች ጭራውን በመንካት ገመድ ወይም አለንጋ ይመስላል አሉ ወዘተ። እነዚህ ሰዎች ሁሉ ጥቂት እውነት ቢኖራቸውም እንኳ ማናቸውም ቢሆኑ ዝሆኑ ምን እንደሚመስል በትክክል አላወቁም።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተዘጋጀው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደ ዝሆን የሚመስለውን የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት እንዲረዱ ለማድረግ ነው። ይህም ማለት መጀመሪያ በተጻፈበት ሁኔታ ማለትም በአልኪታብ ወይም እንዲያውም በአልኪቱቡል መካአዳዳአስ በሚባለው በቅዱስ መጽሐፍነቱ እንዲያስተውለው ታስቦ ነው ይህም መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የተለያዩ የክርስትና እምነት ክፍሎች በቅርፃቸው ወይም በባሕላዊ ድርጊታቸው የተለያዩ ቢሆኑም በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ግን የሚስማሙ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምታገኘው እውነተኛው መልእክት አንተ ስለክርስትና እምነት ካለህ አስተሳሰብ የተለየ ሊሆን ይችላል። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እምነት ያለህ ዕውቀት የተመሠረተው ከመጽሐፍ ቅዱስ ካልሆነ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ አልፎ አልፎ በተወሰዱ ጥቅሶች ላይ ብቻ ከሆነ ይህ ልዩነት የሚጠበቅ ነው።

ጥናትህን እየቀጠልክ ስትሄድ በምዕራቡ ዓለም የምታየው ልቅነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር የጎደለው ኑሮ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ንቆ ከመተው የሚመጣ እንጂ የክርስትና ሕይወት አኗኗር እንዳልሆነ የበለጠ እየተረዳህ ትመጣለህ። ሱረቱ 10፡94 እንደሚለው

«ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፤ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል፥ ከተጠራጣሪዎቹ አትሁን።»

ይህ ጥናት በመጽሐፍ ቅዱስና በውስጡ ባሉ ትምህርቶች ላይ ጠለቅ ያለና ዝርዝር ትንተናዎችን ባይሰጥም እንኳን ሌሎች ጥናቶችህ ሊገነቡበት የሚያስችል መሠረታዊ ነገሮችን ያቀርባል። ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ጥናት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስን አብረኸን

እንድትመረምር እንጋብዝሃለን። ይህንን መጽሐፍ በማጥናት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የተለማመዱትን አዲስ ሕይወትንና ታላቅ ደስታን ልትካፈል ትችላለህ።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በስተመጨረሻ የምዕራፉን መልእክት መረዳትህን ለማረጋገጥ የሚያግዙህ የፈተና ጥያቄዎች ታገኛለህ።

ለዚህ ጥናት የተጠቀምንበት ቁርዓን በሰይድ መሐመድ ሳዶቅና በሐጂ መሐመድ ሣኒ ሐቢብ ወደ አማርኛ የተተረጎመውንና በ1961 ዓ.ም. የታተመውን የቁርዓንን የአማርኛ ትርጉም ነው።

የዚህን ጥናት የመጨረሻ ፈተና ከመውሰድህ በፊት ትምህርቶቹን በሙሉ አጠናቅቅ

# 1. መጽሐፍ ቅዱስ - ምንድነው?

## 1. መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት መዘጋጀት

ያለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክርስትናንና የመጽሐፍ ቅዱስን እምነት መረዳት ጨርሶ የማይቻል ነገር ነው። በተከፈተ አእምሮ በዚህ ጥናት ለመካፈል ፈቃደኛ በመሆንህ እጅግ ደስ ብሎናል። ይኸንንም በማድረግህ እንደማትፀፀት እርግጠኞች ነን። እባክህን! በደንብ ልትረዳው በምትችለው ቋንቋ የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ይኑርህ። በዓለም ላይ ከተጻፉ ከማንኛቸውም መጻሕፍት ይልቅ በብዙ ቋንቋ የተተረጎመ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው በዚህ የጥናት መጽሐፍ ውስጥ የምታገኛቸው ጥቅሶች የተጠቀሱት፥ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1947 ዓ.ም. ካሳተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ ትርጉም በትክክለኛነታቸው ተአማኒነት ካላቸው ትርጉሞች አንዱ ነው በእርግጥ የቀድሞውን የዕብራይስጥን ቋንቋና ሄሌኒስቲክ በመባል የሚታወቀውን የግሪክን ቋንቋ የምታውቅ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስን መጀመሪያ በተጻፈበት ቋንቋ ለማንበብ ትችላለህ። በጣም ጥሩ የሆነ የዐረብኛ መጽሐፍ ቅዱስም በ1973 ዓ.ም. የተተረጎመ ስለሆነ ለማግኘት ከፈለግህ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን መጠየቅ ትችላለህ። ማንኛውም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስ ለማግኘት ከፈለግክ ለኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጻፍ።

## 2. መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ መጻሕፍት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስህን ግለጥና የመጻሕፍቱን ማውጫ ዝርዝር የአለበትን የመጀመሪያ ገጽ ክፈት። መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መከፈሉን ተመልከት። እነዚህም ሁለት ክፍሎች:-


ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የሚባሉት ናቸው። እያንዳንዱ ክፍልም በርከት ያሉ የተለያዩ መጻሕፍትን እንደያዙ ትመለከታለህ። ብሉይ ኪዳን 39 መጻሕፍት ያሉት ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ 27 መጻሕፍት አሉት። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ አይደለም ነገር ግን በአንድ ጥራዝ ውስጥ 66 የተለያዩ መጻሕፍትን የያዘ ቤተ መጻሕፍት ነው።

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስን ለማግኘት ስትፈልግ ከማውጫው ላይ ያለበትን ገጽ ተመልከት። በማውጫው እያንዳንዱ መጽሐፍ የሚጀምርበትን ገጽ ታገኛለህ። ይህ የገጽ አቆጣጠር ለአዲስ ኪዳን መጽሐፍም ሲሆን እንደገና ከገጽ 1 ብሎ ስለሚጀምር ገጾችን ከመፈለግህ በፊት ጥቅሱ የተጠቀሰው ከብሉይ ኪዳን ይሁን ከአዲስ ኪዳን ማጣራት (ለይተህ ማወቅ) አለብህ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት በሙሉ በምዕራፎች ተከፋፍለዋል። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በቁጥሮች ተከፋፍሏል። 1ኛ ሳሙኤል 3፡4-14 አንብብ። ማለት የመጀመሪያው የሳሙኤል መጽሐፍ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 4-14 ድረስ አንብብ ማለት ነው። (በዚህ ጥናት ምንም ዓይነት አሳጥሮ የመጻፍ ዘዴዎችን አንጠቀምም።)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መጻሕፍት በመልእክታቸው ይዘት መሠረት ተከፋፍለዋል። የሚቀጥለው ሥዕላዊ መግለጫ ይህንን ለመረዳት ይጠቅማል።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ቤተ መጻሕፍት




## 3. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

ብሉይ ኪዳን ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በነበሩት ጊዜያት ለሰው ልጆች የተሰጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጦች በሙሉ በአንድነት የሚጠሩበት ስም ነው። እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር በገባው ቃል ኪዳን በመመሥረትም አንዳንድ ጊዜ የብሉይ (የቀድሞው) ቃል ኪዳን በመባልም ይታወቃል። ይህ ቃል ኪዳን ለሙሴና ሰዎችን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር በምሣሌነት እንዲመሩ በእግዚአብሔር ተመርጠው ለነበሩት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ለእሥራኤላውያንም እንደገና ተሰጥቶአቸው ነበር።

ኢየሱስ ደግሞ ሰዎች ሁሉ ሕያው የሆነውን እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበትን አዲስ ቃል ኪዳን አወጣ። መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም ትውልድ ለሚገኙ አማኞች ሁሉ የሚሆን የማያረጅ መልእክት አለው።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለያየ ቡድን በሚከተለው ሁኔታ ተከፋፍሏል። «የሙሴ መጻሕፍት» እነዚህ መጻሕፍት በዕብራይስጥ (ታውራት) ደግሞም ቶራህ (ሕግ) በመባል ሲታወቁ በግሪክ ደግሞ ፔንታቱክ (አምስቱ መጻሕፍት) በመባል ይታወቃሉ።

3፡1፡1- ዘፍጥረት፡- «ጅማሬ»፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዓለምና በዓለም ያሉት ነገሮችን ሁሉ አፈጣጠር እንማራለን። ደግሞም የአዳምን፥ የኖህን፥ የአብርሃምን፥ የይስሐቅን፥ የእስማኤልን፥ የያዕቆብንና የ12ቱ ልጆቹን የሕይወት ታሪክ ከዚህ መጽሐፍ እንማራለን።

3፡1.2- ዘጸአት፡- «በነፃ መውጣት»፥ ይህ መጽሐፍ ደግሞ እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን በሙሴ መሪነት ከግብፅ እንዴት እንዳወጣቸው፥ ቀይ ባሕርን በተአምር ስላቋረጡበት ሁኔታና አሥርቱ ትዕዛዛት በሲና ተራራ ስለመሰጠታቸው ይገልጻል።

3፡1፡3- ዘሌዋውያን፡- እግዚአብሔር፥ለአምልኮና መሥዋዕትን ለማቅረቢያ ሥርዓት በእስራኤል ስለሚያገለግሉ ካህናት የሰጠውን ትዕዛዝ ከበርካታ የሥነ ምግባር ሕግጋት ጋር የያዘ መጽሐፍ ነው። በተጨማሪ ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅ ስለ ማድረግና ስለ ቅድስና የቀረቡ ጥሪዎችን አካትቶ ይዟል።

3፡1፡4- ዘኍልቁ፡- መጽሐፉ ስያሜውን ያገኘው በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ በተደረገ ቆጠራ ነው። የሚናገረውም ከሲና ተራራ እስከ ተስፋይቱ ምድር ድረስ የተደረገውን ጉዞ ሲሆን በተጨማሪም የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ስላሳየው የልብ ጥንካሬ ይገልጻል።

3፡1፡5- ዘዳግም፡- (ለዳግም ሕግ)፥ ቀደም ብለው የተሰጡትን ሕጎች የሚደግምና ሕግን ለመጠበቅ የሚሆኑ መለኮታዊ ትዕዛዛትን የሚሰጥ መጽሐፍ ነው። በተጨማሪም የሚታዘዙት ስለሚያገኙት በረከትና የማይታዘዙ ስለሚደርስባቸው ርግማን የተሰጠ ትንቢታዊ መልእክትን ይዟል። እግዚአብሔር አፍቃሪና ታማኝ ስለሆነ አማኝም እግዚአብሔርን ሊወድና ሊታዘዝ እንደሚገባ ያስተምራል።

3፡2- የእስራኤላውያን የታሪክ መጻሕፍት፡- ይህ ታሪክ ከሙሴ ሞት ጀምሮ እስከ 500 ዓ.ዓ. ድረስ ያለውን የ1000 ዓመት ጊዜ ያጠቃልላል።

3፡2፡1- ኢያሱ፡- ከሙሴ ሞት በኋላ እስራኤላውያን የፍልስጥኤም ምድርን ስለ መውረሳቸው ይናገራል።

3፡2፡2- መሳፍንት፡- ባለመታዘዝ ምክንያት እስራኤላውያን በችግር በነበሩበት 400 ዓመታት ውስጥ ያስተዳድሩ ስለነበሩት ስለ መሳፍንት የሚናገር መጽሐፍ ነው።

3፡2፡3- ሩት፡- በመሳፍንት ዘመን ከአሕዛብነት እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ፊቷን ስለመለሰች ስለ አንዲት ሴት የሚናገር ታሪክ ነው።

3፡2፡4- 1ኛ ና 2ኛ ሳሙኤል፡- የሚናገሩት ስለ ንጉሥ ሳኦል (ታሉት)ና ስለ ንጉሥ ዳዊት (ዳውድ) ታሪክ ነው።

3፡2፡5- 1ኛ ና 2ኛ ነገሥት፡- በመቀጠል የንጉሥ ሰለሞንን (ሱለይማን) ና ባቢሎናውያን በ597 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን እስካጠፉበት ጊዜ ድረስ በተከታታይ ስለነገሡት ነገሥታት ታሪክ የሚናገሩ መጻሕፍት ናቸው።

3:2:6- 1ኛና 2ኛ ዜና መዋዕል፡- የሳሙኤልና የነገሥት መጻሕፍት የሚናገሩትን ተመሳሳይ ታሪኮች ይናገራሉ።

3:2:7- ዕዝራና ነህምያ፡- እስራኤላውያን በባቢሎን ከተማረኩ በኋላ ጥቂቶቹ እንደገና ወደ አገራቸው ስለ መመለሳቸውና ቤተመቅደሱና የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደገና ስለ መሥራታቸው የሚናገሩ መጻሕፍት ናቸው።

3:2:8- አስቴር ፡- በፋርስ መንግሥት (ኢራን) ውስጥ ንግሥት ሆና የነበረች አንዲት አይሁዳዊት ሴት የተፈተነችውን ፈተና ያሳያል። ደግሞም እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዴት ደኅንነትን በእርሷ በኩል እንደሰጠ ይናገራል።

3:3:- የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት፡- እነዚህ መጻሕፍት በመጀመሪያ የተጻፉት በጊዜያቸው በነበረው የግጥምና የቅኔ የአጻጻፍ ዘይቤ ነበር።

3:3:1- ኢዮብ (ኢዮብ)፡- ስቃይን ስለ መቀበል አስቸጋሪነት የሚናገር መጽሐፍ ሲሆን የመጽሐፉ ስም የተሰየመበት ኢዮብ የተባለው ነቢይ ያለፈበትን የሕይወት ልምምድ የሚያሳይ ነው።

3:3:2- መዝሙረ ዳዊት፡- (ዘቡሮ)፤ የምስጋና ጸሎትና መዝሙራት ስብስብ የያዘ መጽሐፍ ሲሆን አብዛኛው የምስጋና መዝሙሮችና ጸሎቶች የተጻፉት የእስራኤል ንጉሥ በነበረው በነቢዩ በዳዊት (ዳውድ) ነው።

3:3:3- ምሳሌ፡- ለጽድቅ ኑሮ የሚጠቅም ተግባራዊ ትዕዛዛትን የሚሰጥ መጽሐፍ ነው። 3:3:4- መክብብ፡- በእግዚአብሔር ብርሃን ሲታይ የሰው አስተሳሰብ ከንቱና ሞኝነት እንደሆነ ያሳያል።

3:3:5- መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፡- የፍቅር መዝሙራት ስብስብ ያለበት መጽሐፍ ነው። 3:3:6- ሰቆቃወ ኤርምያስ፡- ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን በደመሰሱ ጊዜ በኢየሩሳሌም የደረሰውን እጅግ አስጨናቂ መከራ ያሳያል።

3:4- የነቢያት መጻሕፍት፡- ነቢያት እግዚአብሔርን ወክለው ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚናገሩ ሰዎች ነበሩ። ምሕረትን፥ ማስጠንቀቂያንና ፍርድን በመልእክታቸው ያስተላልፉ ነበር። በተጨማሪ በቅርብና በሩቅ ወደፊት ስለሚፈጸሙ ነገሮች እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት ይናገሩ ነበር።

3:4:1- ትላልቅ ነቢያት፡- ኢሳይያስ፥ኤርምያስ፥ሕዝቅኤልና ዳንኤል ነበሩ። 3:4:2- 12ቱ ትናንሽ ነቢያት፡- ትናንሽ የተባሉት መልእክታቸው ትላልቅ ካልናቸው ነቢያት ያነሱና ልንሰጣቸው የሚገባው ትኩረትም ዝቅ ያለ መሆን ያለበት ሆኖ ሳይሆን የመልእክታቸው መጠን ከትላልቁ ጋር ሲወዳደር አጠር ያለ ስለሆነ ነው።

እነዚህ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ቢያንስ 27 በሚሆኑ የተለያዩ ጸሐፊዎች ሲሆን የተጻፉበት ጊዜ በግምት ከ1500-400 ዓ.ዓ. ይሆናል።

## 4. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ዋና ክፍል የተጻፈው ከ40-96 ዓ.ም. ባለው በ60 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ ክፍል በተለይ የሚያተኩረው በኢየሱስ (በነቢዩ ዒሣ.)፥ ሕይወትና ትምህርት ሲሆን ደግሞም በመጀመሪያይቱ ቤ.ክ ዕድገት ላይ ነው። የሚጀምረው በአራት የተለያዩ ጸሐፊዎች በተጻፉት ወንጌላት (ኢንጅል) ነው። ወንጌል ማለት «መልካም የምሥራች» ማለት ነው።

4፡1- <u>ታሪካዊ መጻሕፍት</u>፡- ይህ ንዑስ ክፍል አራቱን ወንጌላትንና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን የሚጨምር ነው።

4፡1፡1- <u>ማቴዎስ</u>፡- ይህ ሰው የኢየሱስ ሐዋርያ የነበረ ሲሆን ወንጌሉንም የጻፈው ለአይሁዶች ነበር። ማቴዎስ እንደ አይሁዳዊ ሆኖ ኢየሱስን እንደ ንጉሥና እንደ መሢሕ በማየት ወንጌሉን ጻፈ።

4፡1፡2- <u>ማርቆስ</u>፡- ይህ ሰው የሐዋርያው ጴጥሮስ ጸሐፊ የነበረ ሲሆን ወንጌሉንም የጻፈው በተለይ ለሮማውያን ነው።

4፡1፡3- <u>ሉቃስ</u>፡- ይህ ሰው በትውልዱ ግሪካዊ ነበር። ወንጌሉንም የጻፈው በተለይ አይሁዳዊ የሆነ አስተሳሰብና መሠረት ለሌላቸው ሰዎች ነው።

4፡1፡4- <u>ዮሐንስ</u>፡- ይህ ሰው የኢየሱስ ሐዋርያ ነበር። ወንጌሉንም የጻፈው ከሌሎቹ ወንጌላት ሁሉ መጨረሻ ሲሆን በኢየሱስ አካላዊ ሕልውናና መልእክት ላይ ያተኩራል።

4፡1፡5- <u>የሐዋርያት ሥራ</u>፡- (የተጻፈው በሉቃስ ነው)፤ የኢየሱስን ዕርገት፥ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ፥ በሜዲተራኒያን ዓለም ሁሉ የወንጌልን መሥፋፋት ይናገርና ክርስቲያኖች በኑሮ የደረሰባቸው ስደት ከመጀመሩ ከጥቂት ጊዜ በፊት ይጠቃለላል።

4፡2- <u>ትምህርት ሰጭ የሆኑ ደብዳቤዎች</u>፡- (መልእክቶች)፥ የተጻፉት በኢየሱስ የተስፋ ቃሎች አማካይነት ነው።

«የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ። ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል። እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል፤» (ዮሐ 16፡12-13)።

«አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፤ (ዮሐ 14፡26)።

እነዚህ የመመሪያ፥ የትምህርትና የትንቢት ደብዳቤዎች የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካይነት ነው (ጸሐፊዎቹ መልእክቶቻቸውን በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ጻፉት)።

እነዚህ መልእክቶች የወንጌልን መልእክት በማሥፋት በተጨማሪ ለመበረታቻና ለመመሪያ የሚሆኑ በርካታ ሠፊ ርዕሶችን አካተዋል፡- ጸሐፊዎቹ

ዮሐንስ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ይሁዳና ጳውሎስ ነበሩ። የጳውሎስ መልእክቶች የተሰየሙት መጀመሪያ በተጻፈላቸው ግለሰቦች ወይም ቤ.ክ ስም ነው። እነዚህ የማስተማሪያ መልእክቶች የሚከተሉት ናቸው:-

4፡2፡1- ሮሜ

4፡2፡2- 1ኛ፣ 2ኛ ቆሮንቶስ

4፡2፡3- ገላትያ

4፡2፡4- ኤፌሶን

4፡2፡5- ፊልጵስዩስ

4፡2፡6- ቆላስይስ

4፡2፡7- 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ

4፡2፡8- 1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ

4፡2፡9- ቲቶ

4፡2፡10- ፊልሞና

4፡2፡11- ዕብራውያን

4፡2፡12- ያዕቆብ

4፡2፡13- 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ

4፡2፡14- 1ኛ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ

4፡2፡15- ይሁዳ

4፡2፡16- የትንቢት መጽሐፍ

በስሙ የተሰየመውን የዮሐንስን ወንጌል የጻፈው ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፍ ደግሞ እስከ መጨረሻው ፍርድ ድረስ ስለሚኖረው የዓለምንና የቤ.ክን ታሪክ በራእይ ያየውን ነገር ጽፏል። ይህም የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ዓላማ እንዴት እንደሚፈጸም የሚያሳይ ነው።

## ፈተና ቁጥር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና የሰጠኸውን መልስ በገጽ 83 ከሚገኘው መልስ ጋር አወዳድር።

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ምንና ምን ናቸው?

   ..............................................................

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት ብዛት ምን ያህል ነው?

..........................................................

3. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አራት ዋና ዋና ክፍሎችን ጥቀስ

3:1...........................................................

3:2...........................................................

3:3...........................................................

3:4...........................................................

4. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሦስት ዋና ዋና ክፍሎችን ዘርዝር

4:1...........................................................

4:2...........................................................

4:3...........................................................

## 2. መጽሐፍ ቅዱስ ከየት መጣ?

አንድ ሰው ብዙ ሀብት ያለበትን ትልቅ ሳጥን ቢያገኝ የሳጥኑን ውጫዊ ገፅታ መመልከቱ ብቻ በቂ አይደለም። ሲከፍተውና በውስጡ ተቀልፎበት ያለው ንብረት ምን እንደሆነ ሊመለከትም ያስፈልገዋል። መጽሐፍ ቅዱስንም መጠቀም ያለበት ልክ እንደዚህ ነው። እስካሁን ድረስ የተመለከትነው የዚህን ብዙ ሀብት ያለበትን ትልቅ ሳጥን ውጫዊ ገፅታ ብቻ ነው። አሁን ደግሞ በውስጡ ተደብቆ ያለውን ንብረት ለማየት እንከፍተዋለን። በውስጡ በምታገኘው ነገር እጅግ ሀብታም እንደምትሆን እርግጠኞች ነን።

### የመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ዋና መልእክት

መጽሐፍ ቅዱስህን በምታነብበት ጊዜ ያልተለመዱና እንግዳ የሆኑ እውነቶችን መመልከት ትጀምራለህ። መጽሐፉ በጠቅላላ ተጽፎ ለማለቅ 1500 ዓመታት ያህል የፈጀና ከ40 በሚበልጡ የተለያዩ ጸሐፊዎች የተጻፈ ቢሆንም እንኳ በውስጡ ባሉ መጻሕፍት መካከል አስደናቂ የሆነ አንድነትን እናያለን። እንዲያው የተለያዩ ሐሳቦች ያላቸው ጽሑፎች ስብስብ አይደሉም። አንዱ ሌላውን የሚጠቅስና የሚገልጽ ሆነው እርስ በእርስ የሚደጋገፉ ተከታታይ መጻሕፍት ናቸው። ሁሉም መጻሕፍት ሁለት የማያቋርጡ ዋና ዋና ዓላማዎች አሏቸው። እነዚህም የኃጢአት አስጨናቂ ውጤትና የእግዚአብሔር ፀጋ የተሞላበት ፍቅር ናቸው። ይህ የሆነው አብዛኛዎቹ ጸሐፊዎች እርስ በእርስ የማይተዋወቁ ሆነው ሳለ ነው። ለዚህም በእርግጥ አንድ መግለጫ መኖር አለበት።

### መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ምስጢሩን ይገልጻል:-

ከመጽሐፍ ቅዱስህ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16 አውጣ። (በአዲስ ኪዳንህ በገጽ 193 ላይ ይገኛል።) ከጥቅሱ ላይ የጎደሉትን ቃላት ሙላ።

«.............. ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት፥ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።»

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው የጻፉት ነው።

እግዚአብሔር በዝምታ ከፍጥረቱ አልተለየም። እግዚአብሔር ፈቃዱን ገልፆአል።

### የእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቧል።

እግዚአብሔር እራሱን ለመግለጥና ዓላማውንና ፈቃዱን ለእኛ ለማሳወቅ የተጠቀመው በዚህ በቃሉ ነው። የዚህ መገለጥ መሠረታዊ ዕውቀት ሳይኖረው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የሚችል ሰው የለም።

እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠው እንዴት ነው? ከላይ በተመለከትነው ጥቅስ መሠረት እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር ቃሉን ለእያንዳንዱ የቅዱስ መጽሐፍ ጸሐፊ ሰጥቷል ማለት ነው።

ይህ ነገር እንደ አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ሆነህ ስታየው አዲስ ሐሳብ አይሆንብህም፤ ምክንያቱም ይህ ከቁርዓን መሠረታዊ ትምህርቶች አንዱ ነውና (ለምሣሌ:- ሱረቱ 2፡136፥5፡47-48፥10፡95፥21፡7፥29፡46።)

## እግዚአብሔር ፈቃዱን በተለያዩ መንገዶች ገልጧል

መጽሐፍ ቅዱስን በምታነብበት ጊዜ እግዚአብሔር መልእክቱን ለመልእክተኞቹ በመንፈሱ አማካይነት የሰጣቸው በተለያየ መንገድ መሆኑን ትገነዘባለህ። አእምሮ እንደሌላቸው ግዑዝ ዕቃዎች (ሮቦቶች) ሁሉን ነገር ቃል በቃል በማጻፍ አልተጠቀመባቸውም። የእግዚአብሔርን መገለጥ በራሳቸው ቋንቋ እንዲጽፉ በመንፈሱ ነዳቸው። የእ/ር መንፈስ ሁለንተናቸውን በመቆጣጠር እንዲጽፉ አደረጋቸው። (ይህንን አባባል በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ራስህ እንድታረጋግጥ ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ ጥቅሶች ቀርበዋል።)

### 1. እግዚአብሔር በቀጥታ ለሰዎች መልእክቱን የሰጠበት ወቅት አለ

- ለአዳም፡- ዘፍጥረት 2፡16-17፤ 3፡9፥ 16-19።
- ለኖህ፡- ዘፍጥረት 6፡13-21።
- ለአብርሃም፡- ዘፍጥረት 12፡1-3፤ 22፡1-2
- ለሙሴ፡- ዘጸ 3፡4-4፡16።
- ለኢያሱ፡- ኢያሱ 1፡1-9።
- ለሳሙኤል፡- 1ኛ ሳሙኤል 3፡1-14።
- ለኤርምያስ፡- ኤርምያስ 1፡4-19።
- ለኢየሱስ ሐዋርያት፡- ማቴዎስ 17፡5 ወዘተ.

### 2. በራእይና በሕልም

- ለአብርሃም፡- ዘፍጥረት 12፡17፤ 15፡1።
- ለያዕቆብ፡- ዘፍጥረት 46፡2፤ 28፡12-17።
- ለኢሳይያስ፡- ኢሳይያስ 6፡1-10።
- ለሕዝቅኤል፡- ሕዝቅኤል 1፡1-28፤ 10፡1-22።
- ለዳንኤል፡- ዳንኤል 2፡19፤ 7፡1-28።
- ለዮሴፍ፡- ማቴዎስ 2፡13።
- ለጴጥሮስ፡- የሐዋርያት ሥራ 10፡9-20።
- ለጳውሎስ፡- የሐዋርያት ሥራ 16፡9-10፤ 9፡3-4 ከ26፡19 ጋር
- ለዮሐንስ፡- ራእይ 1፡1-2፥ 12-19 ወዘተ

## 3. በነቢያት በኩል

አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል የተጻፈው በነቢያት ነው። በእነዚህ ለነቢያት በተሰጡ መልእክቶች እግዚአብሔር ፈቃዱን ገለጠ። ደግሞም ገና ወደፊት ሊፈፀሙ ያሉ ነገሮችን አሳወቀ። እነዚህ መልእክቶች በተለይ የሚያተኩሩት፡-

ሀ. በእስራኤልና በይሁዳ ታሪክ፥

ለ. በመሢሑ (አል መሢሕ) መምጣት፥

ሐ. የዓለምን ፍጻሜ ለመምጣት ስለሚፈጸሙ ነገሮች በማሳወቅ ላይ ነው።

ይህ ዕውቀት በቀጥታ ሰናየው ከሰዎች ግንዛቤ በላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን ሲገልጥ እንዲህ ይላል፡-

« ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ጻፉ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» (2ኛ ጴጥሮስ 1፡21፤)

ቀጥሎ የተወሰኑ ምሳሌዎች ተሰጥተዋል፥

- ሳሙኤል፡- 1ኛ ሳሙኤል 9፡15-17፤ 13፡13-14፤ 16፡7-13።
- ናታን፡- 2ኛ ሳሙኤል 12፡1-15።
- ኢሳይያስ፡- ኢሳይያስ 1፡1-20፤ 58፡1-59።
- ኤርምያስ፡- ኤርምያስ 2፡1-13፤ 3፡6-23።
- ሚልክያስ፡- ሚልክያስ 1፡1-14

## 4. ታሪካዊ ተግባራትን በመመዝገብ

እግዚአብሔር እራሱን ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነትም ገልጧል።

1ኛ ቆሮንቶስ 10፡6፤ 11 በማንበብ (በአዲስ ኪዳን ገጽ 53 ላይ ይገኛል) የሚከተለውን ጥያቄ መልስ፡- እግዚአብሔር የእስራኤላውያን ታሪክ እንዲጻፍ ያደረገበት ምክንያት ምንድነው? ..............................................

..............................................

መጽሐፍ ቅዱስ፤ እንደ እግዚአብሔር ዓላማ፥ ሕዝቡ በሚያስፈልገው ጉዳዮችና ሊረዳው በሚችለው የአስተሳሰብ አድማስ መጠን ቀስ በቀስ በእድገት የተገለጠ መልእክት ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት

ብሉይ ኪዳን ወይም የቀድሞው ቃል ኪዳን ስያሜውን ያገኘው እግዚአብሔር በመጀመሪያ ከአብርሃም ቀጥሎም የእርሱ ዝርያዎች ከሆኑት ከእስራኤላውያን ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ነው። (ቃል ኪዳን ከሰጭው ዘንድ ተስፋንና በረከትን የሚያስገኝ ሲሆን ከተቀባዩ ዘንድ ደግሞ ሊፈጸም የሚገባ ግዴታን ያስቀምጣል። እግዚአብሔር

ቃሉን የሚገልጥላቸው ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ እነርሱን መርጧል። ስለዚህ አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን ኅብረት ውስጥ ገብቶ ነበር። ለእርሱ የተለዩ ሕዝቦች እንዲሆኑ መርጦአቸው ነበር። የተገለጠውን ቃሉን ይታዘዙ ዘንድና ለልጆቻቸው ያስተምሩት ዘንድ ይገባ ነበር ይህም ወደፊት የሚመጣው ትውልድ የተሰጠውን የመሢሑን (የተቀባውን) ያውቅና ይቀበል ዘንድ ነው። (ዘዳ 6፡4-7።)

ሙሴ የዚህ ሕዝብ መሪ እንዲሆን ተጠርቶ ስለነበር በእርሱም በኩል ቃል ኪዳኑ ታደሰ። በኦሪት ዘጸአት ምዕ.20፡ከቁ.1-17 ድረስ የተጻፈው አሥርቱ ትዕዛዛት የሚገልጠው በእ/ር የተመረጠው ሕዝብ እንዴት መኖር እንደሚገባው ለማሳየት ነው። ከእነዚህ ትዕዛዛት ጋር አብሮ አንድ ሰው እነዚህን ትዕዛዛት ሲጥስ ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅ እንዴት እንደሚያደርግ የሚናገሩ መመሪያዎችንም ሰጥቷል፤ (ዘሌዋ.ምዕ.4ና ምዕ.16) ተመልከት።

ቀጥሎም ታማኝ ስለሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች እናነባለን። በተጨማሪ ግን የእስራኤል ሕዝብ እንዴት የማይታዘዝና አመፀኛ ሕዝብ እንደሆነም እንመለከታለን። እግዚአብሔር ብዙ ነቢያትንና እንዲሁም ቅጣትን ወደ ሕዝቡ የላከው ወደ ራሱ ሊመልሳቸው ነበር። ሆኖም ግን ያገኘው ምላሽ ጥቂት ወይም ምንም ነገር አልነበረም። በመጨረሻም ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ በ (ገላትያ 4፡4) እንደተጻፈው እግዚአብሔር መሢሑን ኢየሱስን ወደዚህች ምድር ላከው።

በኢየሱስ በኩል አዲስ ኪዳን (አዲሱ ቃል ኪዳን) መሥራት ጀመረ። በእርሱም የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ተፈጸሙ፤ (ሉቃስ 24፡44-45)። የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ ለሙሉ ለመጠበቅ የቻለ ፍጹም ሰው እርሱ ብቻ ነበር። ንጹሕ ስለነበር አንዳችም እንከን የሌለበት የእግዚአብሔር መሥዋዕት ለመሆን በቃ። «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (1ኛ ዮሐንስ 1፤29) ብሎ በማወጅ ወደ ኢየሱስ ያመለከተው መጥምቁ ዮሐንስ (ያሕያ) ነበር።

አዲስ ኪዳን በመቀጠል የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት፥ ተግባርና ሞት ከዚህም በተጨማሪ ይህ እውነት የተከታዮቹን ሕይወት እንዴት እንደለወጠና ወደፊትም እንደሚለውጥ፥ ኢየሱስ ዳግመኛ ተመልሶ የሚመጣው እንዴት እንደሆነ መግለፁን ይቀጥላል። ቀጥለን በምንመለከታቸው ትምህርቶች እነዚህ ሁሉ ግልፅ ይሆኑልናል።

## ፈተና ቁጥር 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ትክክለኛዎቹን መልሶች በገጽ 83 ታገኛቸዋለህ

1. በብዙ መቶ ዓመታት ተለያይተው የሚኖሩ በርካታ ጸሐፊዎች አንድ መልእክት ብቻ እንዴት ሊኖራቸው ይችላል?..............................

2. እግዚአብሔር ፈቃዱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠው እንዴት ነው?

2፡1.......................................
2፡2.......................................
2፡3.......................................
2፡4.......................................

## 3. መጽሐፍ ቅዱስ ሊታመን የሚችለው ለምንድነው?

በሱረቱ 29:46 በተጻፈው ቃል መሠረት አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ እግዚአብሔር ለአይሁዶችና ለክርስቲያኖች የገለጠውን የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን መቀበል እንዳለበት ታስታውስ ይሆናል።

«የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፤ ከነሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፡ በሉም፡-በዚያ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን። አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፤ እኛም ለርሱ ታዛዦች ነን።»

ይህ ትዕዛዝ በሱረቱ 2:136 ላይ የበለጠ ተስፋፍቶና ተብራርቶ እናገኘዋለን። «በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርዓን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኢልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቆብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያው ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱም በአንድ መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።»

ነገር ግን አሁን በዚህ ጉዳይ አንድ በጣም ጥሩ ጥያቄ ለመጠየቅ ትችላለህ። ጥያቄውም በአሁኑ ጊዜ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ፥ ቁርዓን የሚናገርለት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠው መገለጥ መሆኑን በምን አውቃለሁ? ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ቅዱሳት መጻሕፍትን በርዘውትና አበላሽተውት ሊሆን አይችልምን? አንድ መገለጥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር መምጣቱን በምን አረጋግጣለሁ? የሚል ሊሆን ይችላል።

ቀጥሎ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በምን እርግጠኛ መሆን እንደምንችል እንመለከታለን

### አሲድ - የእውነተኛ መገለጥ መመዘኛ

ዓለም ባሳለፈችው የብዙ መቶ ዓመታት ታሪኳ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች እራሳቸውን የእግዚአብሔር ነቢያት አድርገው አቅርበዋል። ብዙዎቹ ተከታይ ያገኙ ሲሆን አንዳንዶቹ ዓለም አቀፍ የሆኑ ሃይማኖቶች ጀማሪ ሆነዋል። አንዳንዶቹ አምልኮን እንኳ ተቀብለዋል። ይህ ነገር እጅግ አስፈላጊና ተገቢ ወደሆነ «ሕያውና ሁሉን ቻይ የሆነው የእግዚአብሔር እውነተኛ ነቢያትንና አታላዮችን ነቢያት እንዴት ልንለያቸው እንችላለን» ወደሚል ጥያቄ ያመጣናል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ለመለየት ይረዳናል።

ዘዳግም 18:21-22 በማንበብ የጎደሉትን ቃላት ሙላ። (በብሉይ ኪዳን ገጽ 159 ላይ ይገኛል)። «በልብህም እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፥ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም ያ ነገር እግዚአብሔር . . . ነው። ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።»

ነቢይነት ከስብከትና ከትምህርት ያለፈ፥ በሰዎች ዘንድ ካለ ተቀባይነትና ከተከበረ ባሕርይም ሁሉ የላቀ ነው። መልእክተኛውን የላከው እግዚአብሔር ከሆነ መልእክቱ በእርግጥ መለኮታዊ መልእክት ለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት አለበት።

ማረጋገጫ መስጠት ለእውነተኛ ሃይማኖት ዋጋ ያለው እንደሆነ የሚጠበቅ ቢሆንም ብዙ ሃይማኖቶች ተጨባጭ ማረጋገጫ ለመስጠት ተጨንቀው አያውቁም። እምነት ብዙ ጊዜ የተመሠረተው በጭብጥ ላይ ሳይሆን በስሜታዊ መሠረት ላይ ነው። በብዙ ሃይማኖቶች ኃይለኛ የሆነ ሰብአዊ አቀራረብ የሰዎቹን አእምሮ የሚገዛ ሲሆን ከተከታዮቻቸውም ጥቂቶች ብቻ እምነታቸውን ሲተቹ ወይም ሲመራመሩ ይገኛሉ።

ከዘዳግም ቀደም ብለን በተመለከትነው ጥቅስ እግዚአብሔር አታላዮች የሚለዩበትን መመዘኛ ሰጥቷል። ከ700 ዓመት በኋላ ኢሳይያስ የተባለው ነቢይ ጣኦት አምላኪዎችን በሚወቅስበት ጊዜ ይህንን መመዘኛ አጠናክሯል።

«አማልክት መሆናችሁን እናውቅ ዘንድ በኋላ የሚመጡትን ተናገሩ። እንደነገጥም ዘንድ በአንድነትም እናይ ዘንድ መልካምን ወይም ክፉውን አድርጉ! » (ኢሳይያስ 41:23።)

ይህ ማለት እውነተኛ ነቢይ መተንበይ ያለበት ትክክለኛውን ነገር ሳያስበልጥም ሳያሳንስም መሆን አለበት ማለት ነው። መተንበይ ማለት እግዚአብሔር ስላለፈው፥ ስለ አሁኑና ስለ ወደፊቱ ጊዜ ያለውን ፈቃድ መግለጥ ማለት ነው። ስለ ወደፊቱ ጉዳይ የተተነበዩ ትንቢቶች መፈጸማቸው በእግዚአብሔር የታወቀ ነው። ነቢይ፥ነቢይ የሆነው ስለሚተነብይ ነው። ስለ ወደፊቱ ጉዳይ የሚነገሩ ትንቢቶች ከሰው ግንዛቤ ደረጃ ያለፉ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም ከሌሎች ተግባራት ጋር የሚያሻሙ እንዳይሆኑ በግልጽና በዝርዝር የመቀመጣቸው ጉዳይ አስፈላጊነት የግድ ነው። አጠቃላይ የሆኑ ነገሮችን መስጠት መልካም አይደለም። እግዚአብሔር ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ነቢያትን ለሕዝቡ የሚሆን መልእክቱን ያመጡ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ከመንዳቱ ሌላ መልእክቶቹ የመጡትም ከእርሱ መሆኑን የሚለዩና እውነተኛነታቸውን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ትንቢቶችን ሰጥቷል።

ስለወደፊቱ ጉዳይ የተነገሩ ትንቢቶች ከተአምራት የተሻሉ መመዘኛዎች ናቸው እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑ አንዳንድ ሰዎችን የተለያዩ ተአምራት እንዲፈጽሙ አስችሏቸዋል። ለምሣሌ:- መፈወስ (2ኛ ነገሥት 5)፥ ሙታንን ማስነሣት (1ኛ ነገሥት 17፤ ሉቃስ 7:11፤8:11፤ የሐዋ 9:36) ከዐለት ውኃ ማውጣት (ዘጸአት 16)፤ ከሰማይ እሳትን ማውረድ (1ኛ ነገሥት 18:30-39፤ 2ኛ ዜና መዋዕል 7)፤ የመጥረቢያ ብረት ማንሳፈፍ (2ኛ ነገሥት 6:5)፤ እና ሌሎችም።

አልሐጅ ማሁልአና ፉዝሉል ካሪም በሚሽካቱል ማሳአቢህ፥ ምዕራፍ44:2468 ላይ በጻፈው ገለጣ በትክክል እንደተናገረው ትንቢት ከተአምራት ይበልጣል ምክንያቱም:-

«ትንቢት፥ በታሪክ ውስጥ ሊረጋገጥ የሚችል ሲሆን ተአምር ግን አይችልም። ትንቢት እግዚአብሔር የወደፊቱን ነገር እንደሚያውቅ ሲገልጥ ተአምር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል ይገልጣል። ዕውቀት ከኃይል እንደሚበልጥ ሁሉ ትንቢትም ተአምራትን ከማድረግ ይበልጣል።» አንዳንድ ተአምራት የአስማትን ኃይል በሚጠቀሙ ጠንቋዮች ተመስለው ሊቀርቡ ቢችሉም ከነቢዩ ታማኝነትና ቀደም ብሎ ከተሰጠ መግለጥ ጋር መልእክቱ ባለው ወጥነትና ተመሳሳይነት በውሕደት የሚቀርብ ተአምር ለመለኮታዊ መረጃነት ሲቀርብ ተቀባይነት ያገኝ ነበር። ይህ መመሪያ የመሐመድ ነቢይነት ጥያቄ ባስነሣ ጊዜ ተገልጧል። (ሱረቱ 17:90-99)። እንደ ሙሴ ያለ ምልክትን (ከምድር

ውኃ ማውጣት)፣ እንደ ሰለሞን (የወርቅ ቤት) ወይም እንደ ያዕቆብ (ወደ ሰማይ የሚያደርስ መሰላልን) ጠይቀው እንደነበር የተረጋገጠ ነው። የመሐመድ መልሶች (በሱረቱ 17፡93፡ 59፡ 13፡7፡6፡37 እና 2፡118-119 ተጽፈው ይገኛሉ። በእርሱ ላይ ለተነሣው ትችት የሰጠው መልስ ሳያረካቸው ስለቀረ በላንጫነትና ክፉ ደባን በእርሱ ላይ ማድረግ ጀመሩ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት ዓይነት የተለያዩ ዋና ዋና ትንቢቶችን እናገኛለን፡-

1. የእስራኤልና በአካባቢዋ ያሉ መንግሥታትን ታሪክ
2. የመሢሑ ሕይወትና
3. የመጨረሻ ዘመን

## ከተፈጸሙ ትንቢቶች ውስጥ ጥቂት ምሳሌዎች

የተወሰኑ ነገሮችን ብቻ ለማቅረብ እንዲቻል ስለ መሢሑ ሕይወት የሚናገሩ ጥቂት የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ብቻ እንጠቅሳለን። በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ቢያንስ 21 የተፈጸሙ ትንቢቶችን እናነባለን።

ዮሐንስ 5፡39 ን በማንበብ በተሰጠህ ክፍት ቦታ የጎደሉትን ቃላት ሙላ። ኢየሱስ ለአይሁዶች እንዲህ ብሏል፡-

«እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለ.....የሚመሰክሩ ናቸው።»

ቀጥለን ከእነዚህ ከተፈጸሙ ትንቢቶች አንዳንዶቹን ብቻ እንመለከታለን።

(ዓክልበ - ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ማለት ነው።)

| የትንቢቱ ይዘትና የተነገረበት ጊዜ | ትንቢቱ የሚገኝበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | ትንቢቱ መፈጸሙን የሚያሳዩ ቅዱስ ክፍሎች |
|---|---|---|
| 1. መሢሑ የተወለደበት ሥፍራና ከመወለዱ በፊት ስለመኖሩ (700 ዓክልበ) | ሚክያስ 5፡2 | ሉቃስ 2፡4-7 |
| 2. ከድንግል ስለመወለዱ (700 ዓክልበ) | ኢሳይያስ 7፡14 | ማቴዎስ 1፡18-23 |
| 3. መለኮታዊነቱ (700 ዓክልበ) | ኢሳይያስ 9፡6 | ማቴዎስ 1፡23 |
| 4. ስለሚመጣበት ጊዜ (500 ዓክልበ ተጻፈ) | ዳንኤል 9፡24 | ገላትያ 4፡4 |

| | | |
|---|---|---|
| 5. ለማዳንና ለመፈወስ ስለመምጣቱ (700 ዓክልበ) | ኢሳይያስ 53:3-6 | ማቴዎስ 1:21<br>ሉቃስ 19:10<br>ሉቃስ 18:40-43<br>ማቴዎስ 4:23-24<br>ማቴዎስ 11:2-6<br>8:16-17<br>ሉቃስ 8:41-55 ወዘተ |
| 6. የመሢሑ ስም (700 ዓክልበ) | ኢሳይያስ 49:1-8 | ማቴዎስ 1:21 |

(ማሳሰቢያ:- «ደኅንነት» የሚለው የዕብራይስጡ ቃል «ኢያሱ» (ጂሹዋ) የሚል ነው። ኢየሱስ የሚለው ስም የዕብራይስጡ የግሪክ ትርጉም «ኢያሱ» የሚል ነው።)

| | | |
|---|---|---|
| 7. ወደ ኢየሩሳሌም በውርን ጭላ ላይ ተቀምጦ በትህትና መግባቱ (480 ዓክልበ) | ዘካርያስ 9:9 | ማቴዎስ 21:1-9 |
| 8. የኢየሱስ በወዳጁ መከዳትና አልፎ መሰጠቱ (480 ዓክልበ) | መዝሙር 41:9<br>ዘካርያስ 11:12-13 | ማርቆስ 14:10-21፥ 43-46<br>ማቴዎስ 27:3፥ 8 |
| 9. ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ የደረሰበት «መከራ» | ኢሳይያስ 60:6 | ማቴዎስ 26:66-67<br>ዮሐንስ 18:22-23 |
| 10. በመስቀል ላይ የደረሰበት መከራና ሞት | ኢሳይያስ 53<br>መዝሙር 22:1-18 | ዮሐንስ 18:36-19:37 |
| 11. ቀብሩ | ኢሳይያስ 53:9 | ማቴዎስ 27:60 |
| 12. ትንሣኤው | መዝሙር 16:8-11 | የሐዋርያት ሥራ 2:25-32 |

| | | |
|---|---|---|
| 13. ዕርገቱ | መዝሙር 110፡1 | የሐዋርያት ሥራ 1፡6-11<br>ዕብራውያን 1፡13 |

በዓለም ላይ የሚሰጥ ማንኛውም ዓይነት ትችት ይህ ታሪክና የሃይማኖት መጻሕፍት ሁሉ ፍጹም የተለየ ክስተት ነው። የእነዚህን የተፈጸሙ ትንቢቶች መረጃነት ሊያስቀር አይችልም። ማንኛውም በቅንነትና በታማኝነት እውነትን የሚፈልግ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አስረግጦ የሚያውቅበት፥ እግዚአብሔር መልእክቱን ለሰው ልጅ ለማረጋገጥ ያደረገው ማኅተም ይህ የትንቢቶች ፍጻሜ ነው። ይህ መጽሐፍ አንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች የራሳቸውን አመለካከት በሌሎች ላይ ለመጫን የጻፉት መጽሐፍ አይደለም። ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ከተመለከተ በኋላ ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስ የተበላሸ ወይም የተበረዘና የጠፋ መጽሐፍ ነው ማለት አይችሉም።

ይህም ሆኖ ግን እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፥ «የብሉይ ኪዳን የተወሰነ ክፍል እንደዚህ ዓይነት ትንቢቶችን ለመስጠት በከፊልም ቢሆን አዲስ ኪዳን ከተጻፈ በኋላ የተጻፈ ይሆንን?» ይህ በብዙ ምክንያቶች የማይታሰብ ነው። አይሁዶች የሚቻላቸውን ነገሮች ሁሉ በማድረግ ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠብቀዋል። እነዚህ ትንቢቶች ከራሳቸው እምነትና ተግባር የሚጋጩ ስለነበሩ በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ እንዲኖሩ እንኳ አይፈልጉም ነበር።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት እንኳ የተለያዩ ሥፍራዎች ሊደርሱ በሚችሉበት ሁኔታ በሠፊው ተሰራጭተው ነበር። የግሪኩ ትርጉም የተዘጋጀው ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ከ200 ዓመታት በፊት በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር።

በሠፊው የተሰራጨውን እንደዚህ ዓይነት መጽሐፍ ከልሶ መጻፍ ጨርሶ የማይቻል ነገር ነበር። ከዚህ ሌላ ከክርስቲያኖች ጎልውና በፊት የነበሩ እነዚህን ትንቢቶች የያዙ የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች ተገኝተዋል።

## ፈተና ቁጥር 3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ከሰጠህ በኋላ የሰጠኸቸውን መልሶች በገጽ 83 ከሚገኙ ትክክለኛ መልሶች ጋር አወዳድር።

1. እውነተኛ ነቢይ የሚፈተንበት መመዘኛ ምንድነው? ................

.......................................................

2. የትንቢት ፍፃሜ ከተአምራት የተሻለ መመዘኛ የሆነው ለምንድነው? .......

.......................................................

3. ቅዱሳት መጻሕፍት የሚመሰክሩት ስለማን ነው? ..................

.......................................................

4. ብሉይ ኪዳን ከኢየሱስ በኋላ ያለመጻፉን የምናውቅባቸውን ሁለት ምክንያቶች ተናገር።

4.1..........................................

4.2 ..........................................

## 4. መጽሐፍ ቅዱስ ሊታመን የሚችለው ለምንድነው? (2)

### የዐይን ምስክሮች ዘገባ

መጽሐፍ ቅዱስን የምንታመንበት ሁለተኛ ምክንያት የዓይን ምስክሮችን ዘገባ ስለያዘ ነው። እነዚህ ክስተቶች የተፈጸሙት ከዐይን ምስክሮች ተሰውረው በድብቅ ሥፍራ አልነበሩም። እስራኤላውያን ሁሉ እያወቁት በሕዝብ ፊት የተፈጸሙ ነገሮች ነበሩ። በአዲስ ኪዳን የሚገኙ እውነታዎች በሚጻፉበት ጊዜ የተጭበረበሩ ቢሆኑ ኖሮ እስራኤላውያን ሁሉ በተቃወሙት ነበር። ይህ ስላልሆነ ግን ሐዋርያት በተደጋጋሚ ነገሮቹን ለማረጋገጥ የዐይን ምስክሮችን መጠየቅ እንደሚቻል ይናገሩ ነበር። ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት ተከሶ በቀረበ ጊዜ ለመከላከያ ባቀረበው ንግግር እንዲህ አለ፤ «ክቡር ፊስጦስ ሆይ የእውነትንና የእምሮን ነገር እናገራለሁ እንጂ እብደትስ የለብኝም። በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉሥ ይህን ነገር ያውቃል ከዚህ ነገር አንዳች እንዳይሰወርበት ተረድቼአለሁና ይህ በስውር የተደረገ አይደለምና፤» (የሐዋርያት ሥራ 26፡25-26።)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እጅግ ብዙ ሆነው ተሰብስበው ለነበሩ አይሁዶች ጴጥሮስ እንዲህ አለ፡-

« የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው ሐሳቡና በቀደመው ዕውቀቱ ተሰጥቶ በዐመጸኞች እጅ ሰቅላችሁት ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና።» (የሐዋርያት ሥራ 2፡22-24።)

የኢየሱስ ክርስቶስን የመስቀል ሞት አይሁዶች አልካዱም። የካዱት መሢሕ መሆኑንና ከሞት መነሣቱን ብቻ ነው። ጴጥሮስ፥ በብዙ ሺህ አይሁዶች ፊት ይህን ጠንካራና አሳማኝ የሆነ ንግግር ያደረገው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ ከ7 ሳምንት በኋላ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በእርግጥ ባይሞት ኖሮ በዚያን ቀን ብቻ 3000 ሰዎች እምነታቸውን በእርሱ ላይ ያደርጉ ነበርን?

ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያት ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በዚህ ትምህርታቸው ወደ እስር ቤት ተጣሉ። የአይሁድ ምክር ቤት በሆነው ሸንጎ በሚመረመሩበት ጊዜ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጡ፡-

«እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው። ይህን እግዚአብሔር ለእስራኤል ንስሐን የኃጢአትንም ስርየት ይሰጥ ዘንድ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው፤ እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን። ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው፤» (የሐዋርያት ሥራ 5፡30-32።)

በእንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ሁኔታ ጳውሎስ አጥፎ መከላከያን ሲያቀርብ «በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው» ና (ሕግንና /ቶራህ/ ነቢያትን መጥቀሱ ነበር።) በዚያን ጊዜ

ሊጠየቁ የሚችሉ ብዙዎች እንደመሰከሩለት በማለት ይናገራል። ጳውሎስ ይህን ነገር የጠቀሰው በግልጽና በገሃድ ለሚያውቁት ለእስራኤላውያን ሳይሆን ለግሪኮች በተጻፈ ደብዳቤ ነበር።

«እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ:- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም። መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ፤ በኋላም ለአሥራ፤ ሁለቱ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙት እስከ አሁን አሉ፤ አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል። ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ፤ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ፤» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3-7።)

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሐዋርያው ጴጥሮስ በዐይን ምስክሮች ላይ ትኩረት አድርጎ ሲናገር ይህንን ሐሳብ ደግፎታል። ዳሩ ግን የተፈጸመው ትንቢት «ከእርሱ ይልቅ እጅግ የጸና» ነው ይላል። ብዙ ምስክሮች ቢኖሩም እንኳ በምስክርነታቸው ውሸት ሊኖርበት ይችላል። ዳሩ ግን በተፈጸመ ትንቢት ውስጥ ምንም ዕብለት የለበትም።

«የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ። ከገናናው ክብር በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን፤ ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን። ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ ሰው በጨለማ ሥፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ:- በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፤» (2ኛ ጴጥሮስ 1፤16-21።)

በተጨማሪ 1ኛ ዮሐንስ 1፡1-4 ማንበብ ትችላለህ

## ታሪክ ጸሐፊዎችም ወንጌልን አረጋግጠዋል

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ መሆኑን የምናውቅበት ሦስተኛ ምክንያት ደግሞ አለ። በየጊዜው ይጻፉ የነበሩ የጥንት ታሪካዊ ጽሑፎችና መዛግብት ከጦርነቶች፥ ከጀግኖችና በዚያን ዘመን ከነበሩት መሪዎች ታሪክ በስተቀር አንዳችም ነገር አይጽፉም ነበር። ስለዚህ እንደ ገሊላና ይሁዳ ባሉ ጠረፍና ያልታወቁ አገሮች የተፈጸሙ የታሪክ ክንውኖች ይጠቀሳሉ ብሎ ማሰብ ጨርሶ የማይቻል ነው። ይህንን ቢያደርጉም እንኳ የጦርነት ጉዳዮች የነገሥታትና የጀኔራሎች ጉዳይ ዋና ገፅታ እንደሚሆን አጠያያቂ አይሆንም ይህም ቢሆን እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን የሚደግፉ መረጃዎች እናገኛለን። ቆርነሊዎስ ታኪተስ የተባለው፥ ከ54-117 ዓ.ም. የኖረው ታላቁ የታሪክ ሰው እንዲህ ሲል ጽፏል:- «ክርስቲያን የሚለው መጠሪያ ስም የመጣው ጢብሮስ በተባለ ሥፍራ በጴንጤናዊው ጲላጦስ በመስቀል ሞት በተቀጣው ክርስቶስ ከሚባለው ሰው ስም ነው። ይህ አደገኛ የሆነ የጥንቆላ፥ የአስማትና የልዩ ልዩ ምልክቶች አምልኮ ለጊዜው የታፈነ ቢመስልም እንኳ በኋላ እንደ አዲስ ፈንድቶ የበሽታው ምንጭ በሆነችው በይሁዳ ብቻ

ሳይሆን እጅግ አስቃቂና አሳፋሪ የሆኑ ነገሮች በሚፈልቁበትና በአደባባይ በሚታዩባት በሮም ግዛት በሙሉ ተሥፋፋ»

ይህ ታኪተስ የተባለው ታሪክ ጸሐፊ ለክርስትና ምንም መልካም አስተሳሰብ እንዳልነበረው ከጻፈው ነገር ግልጽ ሆኖ ይታያል። ስለዚህ እርሱ የሰጠው መረጃ እጅግ ዋጋ ያለው ነው። (ሚካኤል ግሪን የተባለው ጸሐፊ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ራንአዌይ ወርልድ በሚል ርዕስ ከጻፈው መጽሐፍ ገጽ 14 የተወሰደ።)

አይሁዳዊ ጀኔራል የነበረውና ሮማውያን ኢየሩሳሌምን በ70 ዓ.ም. በደመሰሷት ጊዜ ከደረሰው ጥፋት በመዳኑ ለእስራኤላውያን የሮም ታሪክ ጸሐፊ ሆኖ የነበረው ጆሲፈስ የተባለው ሰው በ93 ዓ.ም. እንዲህ ሲል ጽፏል:-

«በዚያን ወቅት የታላላቅ ድንቅና ተአምራት ሠሪ፥ እውነትን በደስታ የሚቀበሉ ሰዎች አስተማሪ፥ የነበረ አንድ ሰው ነበረ። እርሱን ሰው ብሎ መጥራት ሕጋዊና የማያስጠይቅ ከሆነ ይህ ጥበበኛ ሰው ኢየሱስ በሚባል መጠሪያ ስም ይታወቃል። እርሱ ብዙ አይሁድንና ብዙ አሕዛብን ወደ ራሱ ስቧል፤ እርሱም ክርስቶስ (መሢሕ) ነበረ። በመካከላቸው ካሉ አንዳንድ መሪዎች አሳሳቢነት ጲላጦስ በመስቀል ሞት ሲቀጣው፥ በመጀመሪያ ይወዱት የነበሩት ሰዎች አልካዱትም ነበር፤ በሦስተኛውም ቀን ለእነርሱ እንደገና በመገለጥ በሕይወት ታይቷልና። ቅዱሳን ነቢያትም ይህንንና ሌሎች 10000 ድንቅ ነገሮች ስለ እርሱ አስቀድመው ተናግረው ነበር። ከእርሱም ስም መጠሪያቸውን ያገኙት ክርስቲያኖችም እስከ ዛሬ ከምድር ላይ አልታጡም። (የአይሁድ ሕዝብ የጥንት ታሪክ:-18ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 3፡3 ፍላቪያስ ጆሲፈስ እንደጻፈው በዊሊያም ዊስተን ሚልነርና ሰወርቢ እንደተተረጎመ፤ ለንደን ገጽ 392።)

በእነዚህ ሁሉ መረጃዎች ምክንያት ማንኛውም ታማኝ ተመራማሪ (አጥኚ) የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነትና ሥልጣን ሊጠራጠር አይችልም።

(የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ለተጨማሪ ሳይንሳዊ መረጃዎች ፒተር ደብሊው ስቶነር «ሳይንስ ስፒክስ» (ይናገራል) በሚል ርዕስ የጻፈውን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ማንበብ ትችላለህ። ሙዲ ማተሚያ ቤት፥ 1969።)

## መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ይዘቱን በማጣት ተበላሽቶአልን?

አንዳንድ ጊዜ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍታቸውን አበላሽተዋል ይባላል። ቁርዓን፥ በዐረቢያ የነበሩ አንዳንድ አይሁዶች እውነትን ከመሐመድ ለመሰወር ሞክረው እንደነበር ይናገራል፤ (ሱረቱ 2፡75-79፤ 146፥ 159-160።) አንዳንዶችም የራሳቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት በመጻፍ ለራሳቸው ጥቅም ይሸጡት እንደነበር ተገልጧል (ሱረቱ 2፡79።) ነገር ግን ይህንን ያደረጉት ክርስቲያኖች ናቸው በማለት ቁርዓን ክርስቲያኖችን አይከሳቸውም።

ይህ አባባል እውነት ቢሆን ኖሮ የማይታረቁ ጠላቶች የሆኑት አይሁዶችና ክርስቲያኖች (ሱረቱ 2፡113) ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማበላሸት በስውር አሲረዋል ማለት ነበረበት። ይህ ጨርሶ ሊሆን የማይችል በዐረቢያ ሆኗል ብለን ብናስብ እንኳ በዓለማችን በተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎሙትና የተሰራጩት ቅዱሳት መጻሕፍትስ? ሁሉም በአንድነት

እንዴት ሊበላሹ ይችላሉ? ሙስሊሞች የሆኑ አይሁዶች ብቻ የመጀመሪያዎቹን የቅዱሳት መጻሕፍት ሊገልጡልን ደስተኞች ይሆናሉን?

የዚህ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜም የተመሠረተው ከቁርዓን ቢያንስ የሁለት መቶ ዓመታት ዕድሜ ቀደም ብለው ከነበሩት ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶ ከሆነ፥ የተበላሸው ከዚያ በፊት መሆን አለበት። ቁርዓንን የሚያምን ማንኛውም ሰው ይህንን ለመቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም ተበላሽቶ ቢሆን ኖሮ ቁርዓን የእስልምና አማኞችን በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲያምኑ አይነግራቸውም ነበር። (ሱረቱ 42፡14-15፤29፡46፤10፡94።) ቁርዓን እራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያለመበላሸቱን ይመሰክራል።

«የጌታህም ቃላት እውነተኛና ትክክለኛ ስትሆን ተፈጸመች፤ ለቃላቱ ለዋጭ የለም፤ ሰሚም ዐዋቂም እርሱ ነው፤» (ሱረቱ 6፡115።)

## የመጨረሻ ማረጋገጫ

ዳሩ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እንድናምን ቁርዓን ሊነግረን አያስፈልግም። ባልተዛባ አእምሮ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ማንኛውም ሰው እውነት መሆኑን ተረድቶ ይቀበላል። መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደሆነና በእርግጥ ለአንተ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የሚያረጋግጥልህ ጸሐፊዎቹን የነዳ (የመራ) የመጽሐፉ ደራሲ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ በጸሎት በምታነብበት ጊዜ ነው። በተከፈተ አእምሮ እያነበብክ እግዚአብሔር እውነትን ለማግኘት እንዲረዳህ ፍቀድ።

## ፈተና ቁጥር 4

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና በገጽ 83 ከተሰጡ መልሶች ጋር አወዳድር

1. መጽሐፍ ቅዱስን የምናምንበትን ሦስት ምክንያቶች ግለጽ

1፡1.............................................

1፡2.............................................

1፡3.............................................

2. አይሁዶች ስለ ኢየሱስ የሚክዱት ነገር ምንድነው?

2፡1.............................................

2፡2.............................................

## 5. እግዚአብሔር ስለ ራሱ እናውቀው ዘንድ የገለጠልን ነገሮች

እስካሁን ድረስ በተመለከትናቸው ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስን የምናምንበት በቂ ምክንያት እንዳለን በሚገባ ተገንዝበሃል። ስለዚህ ከአሁን ጀምረህ መጽሐፍ ቅዱስህን እንድታነብ እንጋብዝሃለን። መጽሐፍ ቅዱስን የማንበቢያ በርካታ መንገዶች አሉ። ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሐሳብን አሰባስቦ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ከዳር እስከዳር ማንበብ አንዱ መንገድ ነው። ይህንን መንገድ ከመረጥክ ብሉይ ኪዳንን በሚገባ ለመረዳት እንድትችል ስለሚረዳህ በመጀመሪያ አዲስ ኪዳንን በሙሉ አንብብ። ማንበብ ከመጀመርህ በፊት እንዲህ ብለህ በመጸለይ ከእግዚአብሔር ምሪትን መጠየቅ ትችላለህ፡-

«እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ መጽሐፍ የአንተ ቃል መሆኑን አሳየኝ። እውነትን ለማግኘትና ለመታዘዝም እርዳኝ።»

እግዚአብሔር ለሰዎች ጸሎት መልስን ስለሚሰጥ እውነትን ማግኘት እንድትችል ይረዳሃል። ሁለተኛው መጽሐፍ ቅዱስን የማንበቢያ መንገድ ደግሞ የተወሰኑ ዓላማዎችን መርጦ በመጽሐፍ ቅዱስ በሚገኙበት መንገድ ማጥናት ነው። በዚህ መጽሐፍ ጥናታችንም፥ በቀረው ክፍል የምናደርገው ይህንን ነው። ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ ማጥናትህን በመቀጠል የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ አንብብ። ይህን ስታደርግ ስለ እግዚአብሔርና ለዚህ ዓለም ስላለው ዕቅድ ያለህ መረዳት በከፍተኛ ሁኔታ ያድጋል።

### እግዚአብሔር እራሱን ይገልጣል

ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው ነገር ሁሉ በራእይ የተገለጠ ነው። እግዚአብሔር እራሱን በተለያዩ መንገዶች ይገልጥልናል፡-

- በፍጥረት ሥራው (ሮሜ 1፡20፤ መዝሙር 19፡1-4።)
- በሰው ኅሊና (ሮሜ 2፡14-15።)
- በታሪክ ሂደት ውስጥ (መዝሙር 78፡12-16።)
- በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16።)
- ሕያው ቃሉ በሆነው በኢየሱስ በኩል (ዮሐንስ 1፡1-4፥9-14፤ ዕብራውያን 1፡1-2፤ ሱረቱ 4፡171።)

### ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሁን

ለአንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነና የተዛባ አስተያየት አስቀድሞ ሳይኖረው መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይገባናል። ይህ አስተያየት አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ ያልሆነ ሰው ቁርዓንን ለማንበብ በሚሞክርበት ጊዜ እንደሚሰማው ዓይነት ስሜት ነው።

ነገር ግን አስቀድመን እርግጠኛ ልንሆንበት የሚገባን ጉዳይ የራሳችን ስብእዊ የተሳሳተ የቅድሚያ አስተያየት ትተን በእውነት እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ መሆናችንን

ነው። አንድ ጊዜ ኢየሱስ (ዒ.ሣ.) ስለዚህ ጉዳይ አይሁዶች እራሳቸውን በመመርመር ወደ አንድ ውሳኔ እንዲመጡ ጠይቆ ነበር።

«ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል፤» (ዮሐንስ 7፡17።)

እኔም ሆንኩ አንተ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግን እንደምንመርጥ እርግጠኛ ነኝ ስለዚህ በጸሎት መንፈስ ጥናታችንን በመቀጠል እርሱ ሊገልጥልን ያለውን ነገር እንይ።

## መጽሐፍ ቅዱስ የገለጣቸው የእግዚአብሔር ተፈጥሮአዊ ባሕርያት

«የእግዚአብሔር ዘጠና ዘጠኙ ስሞች» የተባለውን ነገር የምታውቅ ከሆነ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ነገሮች አብዛኞዎቹን ታውቃቸው ይሆናል። ልትመለከታቸው ትፈልግ እንደሆነ ተፈጥሮአዊ ባሕርይውን የሚገልጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተሰጥተዋል። እያንዳንዱ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ትርጉምና የሚሰጡትን መልእክት አሰላስል።

- እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው

ዘፍጥረት 1፡1፤ መዝሙር8፤ የሐዋርያት ሥራ 17፡24-27፤ ቆላስይስ 1፡15-17፤ ዕብራውያን 1፡3።

- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው

ዘፍጥረት 17፡1፤ ዘጸአት 6፡3፤ ዘኁልቁ 24፡4፤ መዝሙር 91፡1፤ ኢሳይያስ 13፡6፤ ራእይ 1፡8፥4፡8፥11፡7።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው

ኢሳይያስ 6፡3፤ ዘሌዋውያን 11፡44፤ ኢያሱ 24፤19፤ 1ኛጴጥሮስ 1፡15-16፤ ራዕይ 15፤4፥4፡8

- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው

1ኛ ሳሙኤል 16፡7፤ መዝሙር 139፡1-4፥23-24፥ ኤርምያስ 17፡10፥ ማቴዎስ 6፡8፥18።32፥10፡30፤ ዮሐንስ 1፡48-49፥2፡25፥6፡64

- እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ ነው

መዝሙር 139፡5፡12፤ ማቴዎስ 18፡20፤ 28፡20።

- እግዚአብሔር ጻድቅና ሐቀኛ ነው

ዘፍጥረት 6፡5-7፤ ዘጸአት 34፡7፤ ዘዳግም 10፡17-18፤ 32፡4፤ መዝሙር 11፡7፤ ሮሜ 2፡4-11፤ ዕብራውያን 10፡30፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡17።

-እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው

ዘፍጥረት 21፡33፤ መዝሙር 90፡1-2፥ 102፡27-28፤ ኢሳይያስ 40፡28፤ 51፡6።

- እግዚአብሔር መንፈስ ነው

ዮሐንስ 4፡24፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡17።

- እግዚአብሔር የተከበረ (ግርማ ሞገስ ያለው) ነው

ዘሌዋ 14፡21፤ ዘዳግም 10፤ 17፥ 28፡58፤ መዝሙር 8፡1፥ 104፡1፤ ኢሳይያስ 6፡1-3፥ 57፡15፤ ማቴዎስ 16፡27፤ ዮሐንስ 1፡14፤ 17፡5፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡14-16፤ ራእይ 4፡11።

- እግዚአብሔር ፈራጅ ነው

ዘፍጥረት 18፡25፤ መዝሙር 7፡11፤ ዮሐንስ 5፡22-27፤ የሐዋርያት ሥራ 10፡42-43።

- እግዚአብሔር ምሕረትን የተሞላ (መሐሪ) ነው።

ዘጸአት 34፡6፤ መዝሙር103፡8-13፤ ሚክያስ 7፡18፤ ዮሐንስ 3፡16-18፤ ቲቶ 2፡11-12።

- እግዚአብሔር የማይመረመር ነው

ሮሜ 11፡33-34፤ 1ኛቆሮንቶስ 2፡6-7፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡16።

- እግዚአብሔር እራሱን ስለገለጠ ልንረዳው የምንችለው ነው

ሮሜ 1፡19-20፤ 2፡14-15፤ የሐዋርያት ሥራ 14፡17፤ 17፡26-27።

- እግዚአብሔር የማይታይ ነው

ዘጸአት 30፡20-23፤ ዮሐንስ 1፡18፤ ቆላስይስ 1፡15፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡17፥ 6፡16፤ 1ኛ ዮሐንስ 4፡12፥ 20።

- እግዚአብሔር አዳኝ ነው

መዝሙር 106፡21፤ ኢሳይያስ 44፡6፤ 45፡21፤ 63፡7-10፤ ቲቶ 2፡11-14፤ ይሁዳ 25፤ ዮሐንስ 3፡16-18።

- እግዚአብሔር ደግ ነው

መዝሙር 118፡1፤ 136፤ 1፡17፤ 36፡7-9፤ 63፡3-4፤ 34፡8፤ 31፡19።

- እግዚአብሔር ታማኝ ነው

ዘዳግም 7፡9፤ 32፡4፤ ኢያሱ 23፡14-16፤ ቲቶ 1፡2፤ መዝሙር 117፤ 118፡1-4፤ ዘጸአት 34፡6፥ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡9።

- እግዚአብሔር ታጋሽ ነው

ዘሌዋ 14፡18፤ ነህምያ 9፡16-21፤ መዝሙር 103፡8፤ ሉቃስ 13፡6-9፤ ሮሜ 9፡22-23፤ 2ኛ ጴጥሮስ3፡9

- እግዚአብሔር ያዘጋጃል ይጠብቃልም

ማቴዎስ 6፡25-34፤ ዘዳግም 29፡2-6፤ ዘጸአት 16፡13-15፤ መዝሙር 41፡1-3፤ 67፡6-7፤ 104፡27-28፤ 145፡15-21፤ 147፡7-9።

- እግዚአብሔር ያስተምራል ይመራልም

መዝሙር 25፡4-5፤ ዮሐንስ 6፡45፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡13፤ ዘጸአት 4፡15፤ ኢዮብ 36፡22፤ መዝሙር 94፡12፤ ሉቃስ 12፡12፤ ዮሐንስ 14፡26

- እግዚአብሔር ረዳታችን ነው

ዕብራውያን 13፡6፤ መዝሙር 33፡20፤ 46፡1-3፤ 124፡8፤ የሐዋርያት ሥራ 26፡19-23፤ ሮሜ 8፡26።

- እግዚአብሔር ሕያው ነው

ዘፍጥረት 16፡14፤ መዝሙር 42፡2፤ ኤርምያስ 17፡13፤ ዮሐንስ 5፡26፤ ዘፍጥረት 15፡45፤ ራእይ 1፡18

ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ባሕርዮች ልዩ ትኩረት በመስጠት ተመልከታቸው፤ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም የማታውቃቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከተጠቀሱት ጥቅሶች መካከል አንዳንዶቹንም ተመልከት!

- እግዚአብሔር የአማኞች ሁሉ አባት ነው

ኢሳይያስ 9፡6፤ ኤርምያስ 31፡9፤ ማቴዎስ 5፡16፥45፥48፤ 6፡8-9፥32፤ ዮሐንስ 8፡41፤ 14፡6፥ 15፤ 16፤ ሮሜ 8፡15፤ ገላትያ 4፡6፤ ኤፌሶን 4፡6፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡3፤ 2፡1፥ 2፡23።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው

ራእይ 1፡2፤ ኢሳይያስ 62፡5፤ ኤር.31፡3፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡2፤ ኤፌሶን 3፡19፤ 1ኛ ዮሐንስ 4፡7፥8።

- እግዚአብሔር ሰላም ነው

ኤፌሶን 2፡14፤ 1ኛቆሮንቶስ 14፡33፤ ሮሜ 15፡33፤ 16፡20፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡11፤ ፊልጵስዩስ 4፡9፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡23፤ ዕብራውያን 13፡20።

- እግዚአብሔር ቸር ነው

ቲቶ 3፡4-5፤ ነህምያ 9፡17፤ ሮሜ 2፡4፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡3።

ከተሰጡት ጥቅሶች አንዳንዶቹን እንደተመለከትካቸው ተስፋ አደርጋለሁ። ያልተመለከትካቸው ከሆኑ ግን እባክህን ወደኋላ ተመለስና ተመልከታቸው፤ ታላቅ በረከት ይሆኑልሃል። በእርግጥ እግዚአብሔር አስደናቂ አምላክ ነው።

## ፈተና ቁጥር 5

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና መልሶችህን በገጽ 83 ከተሰጡ መልሶች ጋር አወዳድራቸው።

1. እግዚአብሔር እራሱን የገለጠባቸውን አምስት መንገዶች ዘርዝር:-

1:1..................................................

1:2..................................................

1:3..................................................

1:4..................................................

1:5..................................................

## 6. እግዚአብሔር ስለ ሰው የገለጠው ነገር

የአንድ የታወቀ ምድጃ ሠሪ መምሪያ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- «ሁሉም ነገር አልሠራም ቢልህ የሠራው ድርጅት የሰጠህን መምሪያ አንብብ»። በዓላማችን ዙሪያ ያለውን ጥላቻ፥ ጦርነት፥ መከራና የፍርድ መዛባት ስናይ ተስፋ ወደ መቁረጥ እናዘነብላለን። ሰው ሁሉ ከፍቅር ይልቅ ግላዊ ፍላጎት የበለጠ ደስ የሚያሰኘው ለምንድነው? በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ስስታምነት የሚታየው ለምንድንነው? እራሳችን መረዳት የምንጀምረው የሠሪውን ትዕዛዝ ማንበብ ስንጀምር ብቻ ነው። ይህን ስናደርግ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ዕቅድና በአሁን ጊዜ በብዛት የምናያቸው አሳዛኝ ነገሮች የተፈጠሩት በምን ምክንያት እንደሆነ እንረዳለን። ነገር ግን በተጨማሪ ይህንን አሳዛኝ የሆነ ጉዳይ ለማስተካከል የእግዚአብሔር መንገድ ምን እንደሆነም እንገነዘባለን።

### እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ፈቃድ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር እንደሚናገር ሁሉ ቁርዓንም ይናገራል፡- «ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ወይም ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠረ ነው፥» (ሱረቱ 15፡26።)

«በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ፥ በጣም አዛኝ በሆነው አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም) እውጅ!» (ሱረቱ 96፡1-2።) ከዚህ ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ዓላማ በግልፅ ይናገራል። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ያለ ዓላማ አይደለም። ፍጥረታት በሙሉ የሚመሰክሩት ይህንኑ ነው። የአንድ ጽሑፍ ዕቅድ እውነተኛ ዓላማና ትርጉም ከማንም በተሻለ ሁኔታ ሊገልጥ የሚችለው ዕቅዱን ያወጣውና የሠራው ሰው ነው። በሰውም ጉዳይ የእግዚአብሔር ሚና እንደዚሁ ነው።

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ፍቅሩን ይገልጥለት ዘንድ ነበር።

ዘፍጥረት 1፡26-28 አንብብ።

ሰው የተፈጠረው በማን አምሳያ ነበር? (ቁጥር 27።)..................

ይህ ሁኔታ የሚመለከተው ወንዶችን ብቻ ነውን? (ቁጥር 27።)............

በቁጥር 28 በእግዚአብሔር የተሰጡትን ሦስት ትዕዛዛት ጻፍ።

ሀ)..................................................

ለ)..................................................

ሐ)..................................................

መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሣል ነው ሲል እግዚአብሔር ሰውን ይመስላል ማለቱ አይደለም። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ (ዮሐንስ 4፡24) የሚታይ አካላዊ ሕልውና ካለው ነገር ጋር ልናወዳድረው አንችልም። እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ሁለቱንም ፍጥረታት የፈጠረው ልዩ በሆነ መንገድ ነው! (ዘፍጥረት

2:7፣ 20-25)። ሁሉቱም በእግዚአብሔር አምሣያ፡ በእውነተኛ ዕውቀት፣ (ቆላስይስ 3:9-10) በቅድስናና በጽድቅ ተሠርተዋል፤( ኤፌ.4:22-25።)

## እግዚአብሔርን እንድንታዘዝ ይጠብቅብናል

የመጀመሪያዎቹ ሰዎች እግዚአብሔርን ሲታዘዙ የእግዚአብሔር አምሣያ በውስጣቸው ይታይ ነበር። ታማኝ እንዲሆኑና ምድርን እንዲሞሉአት፣ በውስጧ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ እንዲገዙና እንዲያስተዳድሩ ታዘው ነበር (ዘፍጥረት 1:28፤ መዝሙር8:5-8።) ከእነዚህ ሁሉ ትዕዛዛት በተጨማሪ አንድ ሌላ የተከለከለ ትዕዛዝ ነበር።

ዘፍጥረት 2:15-17 አንብብ።

ያ የተከለከለ ነገር ምን ነበር? ..............................................

ለምን? ..............................................

በእዚህ የመጨረሻ ትዕዛዝ የሰው ልጅ ታዛዥነት ተፈትኗል። ትዕዛዙን መፈጸም የነበረባቸው የታዘዙበትን ምክንያት ስለተረዱ ሳይሆን እግዚአብሔር ስላዘዘ ብቻ ነበር።

አዳምና ሔዋን በሚያደርጉት ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር አምሣል መሆን ነበረባቸው በራሳቸው መንገድ መሄድ ሳይሆን በሚያደርጉት ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን መታዘዝ ነበረባቸው።

ሰው ለእግዚአብሔር ፍቅር በፍቅርና በመታዘዝ ምላሽ ሲሰጥ ንጹሕ ደስታን ይለማመዳል። የሚያሳዝነው ነገር ግን ዛሬም ቢሆን ደስታን እያጠፋ ያለው አስቸጋሪ ነገር ተከሰተ።

## የሰው ያለመታዘዝ

ዘፍጥረት 3:1-24ን አንብብ።

አዳምና ሔዋን ያላከበሩት የትኛውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ነበር? ..........

..............................................

በባዶ ቦታ ሙላ፡- መልካሙንና ክፉን የሚያውቁ እንዲሆኑ እንደ............

ለመምሰል ፈለጉ።

ለእግዚአብሔር የነበራቸው ፍቅር ምን ሆነ? (ቁጥር 8።)................

አዳም ስለ ሠራው ኃጢአት ጥፋተኛ መሆኑን አምኖ ነበር ወይ? (ቁጥር 12።)....

..............................................

ሔዋንስ? (ቁ.13።)..............................................

በዚህ አስጨናቂ ቀን በመጀመሪያው ሰውና በሚስቱ ያለመታዘዝ ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ።

ፍጥረታትም ሁሉ በኃጢአት ተበከሉ፤ ኃጢአት ሁሌጊዜ መለያየትን ያመጣል።

- በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መለያየትን አመጣ (ቁጥር 8፤)

- በሰውና በሚስቱ መካከል መለያየትን አመጣ (ቁጥር 7፥12፤)

- በሰውና በሌሎች ፍጥረታት መካከል መለያየትን አመጣ (ቁጥር 14-19፤)

- በሰውና በድካሙ መካከል መለያየትን አመጣ።(ቁጥር 17፥19።)

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ይህ ኃጢአት የአመጣው ችግር የሚነካቸው ሆነ። የአዳምና የሔዋን የመጀመሪያ ልጅ የመጀመሪያው ነፍሰገዳይ ሆነ፤ (ዘፍጥረት4፡1-16)። እርሱና ዘሮቹ በሙሉ የወላጆቻቸውን ኃጢአት ወረሱ። አንተ እራስህ የዚህ ነገር ምስክር መሆን ትችላለህ። «በተፈጥሮህ» ኃጢአትን እንድትሠራ የሚያደፋፍር ነገር አለህ። ይህም መልካም ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ነገር ሲሆንብህ ታየዋለህ። ክርስቲያኖች ይህ አብሮ የተፈጠረን ውስጣዊ መመሪያ «የተፈጥሮ ኃጢአት» በማለት ይጠሩታል። (ከሉሬቁ12፡53) አወዳድር።

ዓመፀኛ እንደሆነ ጎረምሳ ልጅ፥ ሰው ከእግዚአብሔር መለያየትን መረጠ፤ አውቆም ይሁን ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ፍቅር በመጠራጠር እግዚአብሔር ከሚፈልገው ኅብረት ወጣ። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ኅብረት ስላቋረጠ የሚያደርገውን «መልካም» ነገር ሁሉ ለማድረግ የሚያነሣሣው የራስን ጽድቅ የማቆም ጉዳይ ነው። ይህም እግዚአብሔርን በተዘዋዋሪ መንገድ መቃወም ነው። ከዚህ ዓለም አጠቃላይ የመመዘኛ ደረጃ ጋር ሲታይ «ጥሩ» ሕይወትን ለመምራት ጥረት ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን ከኃጢአቱ ተመልሶ ከእግዚአብሔር ጋር መንገዱን ለማስተካከል ፈቃደኛ እስካልሆነ ድረስ የእግዚአብሔርን ይቅርታ አገኛለሁ ብሎ ሊጠብቅ አይችልም።

አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር መንግሥት ሥፍራ ያገኙ ዘንድ ሃይማኖታዊ ወይም ጥሩ ሥነምግባር መፈጸምን ለእግዚአብሔር እንደሚሰጥ ጉቦ አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ ቅድስና ሙሉ ፍጹምነት የሚጠይቅ መሆኑን ባለማስተዋል የእግዚአብሔርን ችሮታ ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ ነው።

እግዚአብሔር ስለ ሰው የሚናገረውን ነገር ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ክፍሎች አንብብ፡-

ዘፍጥረት 6፡5-6፤ መዝሙር 14፡1-3፤ ሮሜ 3፡10-18፤ ሮሜ 1፡29-32፤ ገላትያ 5፡19-21።

## እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ፍቅርና ምሕረት

እግዚአብሔር ሰውን ጠልቶ ፊቱን ከሰው እንዳልመለሰ መገንዘብ እጅግ የሚያስደስት ነገር ነው። እግዚአብሔር ሰውን አላጠፋም፤ በአለመታዘዝና በዓመፅ ይንከራተትም ዘንድ አልተወውም። የእግዚአብሔር ፍቅር ከሰው ልጅ ፍቅር ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ (1ኛ ዮሐ 4፡8፥16) ፍቅሩ በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አይደለም። እርሱ ሁሌጊዜ እውነተኛ ሆኖ ይኖራል። እስከ አሁንም ድረስ ጠላቶቹ የሆኑትን እንኳ ይወዳል፤ (ሮሜ5፡6-10።)

እግዚአብሔር በዘለዓለማዊ ፍቅሩ ዓመፀኛውን የሰውን ልጅ ይፈልጋል፤(ዘፍጥረት 3፡9።) ደጋግሞ ደጋግሞ ስለ ንስሐና ስለ ይቅርታ ይናገራል (ኤርምያስ 3፡12-13፤19-20፤ኢሳይያስ 1፡18፤ማቴዎስ 11፡28)። ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር ልዩ ቃል ኪዳን እንዲያደርጉ ይጋብዛል፤ (ዘፍጥረት 17፡7፤ዘሌዋውያን 26፡12፤ዘፀአት 29፡45፤2ኛ ቆሮንቶስ 6፡16፤ራዕይ 21፡3-7፤ ዕብራውያን 8፡10፤ኤርምያስ 7፡23፤11፡4)። እግዚአብሔር የሰጠውን የፍርድና የበረከት፥ የተስፋ ቃል ለመጠበቅ ታማኝ ነው።

2ኛ ጢሞቴዎስ2፡13 እንብበህ በተሰጠው ክፍት ቦታ የጎደሉትን ቃላት ሙላ፡-

«ባናምነው እርሱ........................ራሱን ሊክድ አይችልምና።» የእግዚአብሔር ፍቅር በሰው ያለመታዘዝ ምክንያት አልተለወጠም። ከመጽሐፍ ቅዱሳችን እንደምናነበው እርሱ ሁልጊዜ ይቅር ሊለን ዝግጁ ነው። ደግሞም እርሱ ጻድቅና ቅዱስም ነው። ኃጢአት መቀጣት አለበት። በ(ሮሜ 3፡21-26) እንደምናየው እግዚአብሔር ለይቅርታና ለዋስትና አዲስ መንገድ ያዘጋጀበት ምክንያት ይህ ነው።

## ፈተና ቁጥር 6

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና መልስህን በገጽ 83 ከተሰጡ መልሶች ጋር አወዳድር

1. ሰው የተፈጠረው በማን አምሳል ነው?.........................

2. አዳም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ምን እንዲያደርግ ይጠበቅበት ነበር?......

.........................................

3. የሚከተለውን አሟላ፡- ኃጢአት መለያየት ያስከትል

3፡1.........................................

3፡2.........................................

3፡3.........................................

4. የእግዚአብሔር ፍቅር ለሰው ያለመታዘዝ የሚደርስበት ተጽዕኖ ምንድነው?

.........................................

## 7. እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት የገለጠው ነገር

እስካሁን ድረስ በዓለም ውስጥ ያሉት ኃጢአት፥ ኃዘንና በሽታ ከየት እንደመጡ መመልከት ጀምረናል። በሮሜ 5፡12 እንደምንመለከተው የአዳም ያለመታዘዝ ሁላችንንም የሚጠላ ነገር ሆኗል። «በዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፥ በኃጢአትም ሞት። እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።»

ሁላችንም የኃጢአት ችግር አለብን። ቀጥለን ኃጢአት ምን እንደሆነ እንመለከታለን።

### የኃጢአት ተፈጥሮ

የእግዚአብሔር ሕግ በመለኮታዊ መመዘኛዎች ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሕግ ሰው የእግዚአብሔር የሥነምግባር «አምሣያ» እንዲሆን ይፈልጋል። ከፍፁምነት የጎደለ ማንኛውም ነገር ኃጢአት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

«ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፤ ኃጢአትም ዓመፅ ነው፤ (1ኛ ዮሐንስ 3፡4።)

«ዓመፅ ሁሉ ኃጢአት ነው፤ (1ኛ ዮሐንስ5፡17።)

«እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው፤ (ያዕቆብ 4፡17።)

ኃጢአት ወደከፉ ሥራ ወይም መልካም ሥራዎችን ወደመተው የሚመራ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ብቻ አይደለም። «ከክፉ ልብ» ከሚወጣ «ክፉ ሐሳቦች» የሚጀምር ነው።

ኢየሱስም እንዲህ ብሏል፡-

«ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሐሳብ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጎምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸው፤ (ማርቆስ7፡20-23፤ ማቴዎስ15፡19)።

ኃጢአቶች ከእግዚአብሔር የተለየ ሰው በሕይወቱ የሚያፈራቸው ፍሬ ናቸው፤ (ገላትያ5፡19-21።) ለእግዚአብሔር ፍቅር እንደሌለንና እርሱንም እንደማንፈራ የሚታወቀው ለእርሱና ለፈቃዱ አክብሮትን ስናጣ ነው። እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ኃጢአተኛ ልብን ይዞ ነው፤ (መዝሙር51፡5)። ሁላችንም ብንሆን ኃጢአትን ለማድረግ የምንገደደው ለዚህ ነው።

«በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንና የልቦናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን፤ እንደሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን፤» (ኤፌሶን 2፡3)። ወደንም ሆነ ተገደን የምንሠራቸው ኃጢአቶች ሁሉ የኃጢአተኛ ልብ ውጤቶች ናቸው። ስለዚህ ሁሉም ተመሳሳይ ነገርን ያስከትላሉ።

## የኃጢአት ሁሉ ሥር

የኃጢአቶች ሁሉ መሠረት እግዚአብሔርን ከመውደድና ከመታዘዝ ይልቅ እራስን ምውደድና ስስታምነት ነው። ኃጢአት የሰው ልጅ ከፍተኛው የግላዊነት ምርጫ፥ እራስን መውደድ፥ የግል ፈቃድና የግል ፍላጎት ነው።

ስለዚህ አንድ ሰው «በመልካም ሥራ» ውስጥ እንኳ ኃጢአትን ማድረግ ይችላል። በርካታ «መልካም ሥራዎች» እራስን ከመውደድ የመነጩ ናቸው። ስለዚህ ዓላማቸው የአንድን ሰው መልካምነት ለማሳየት ይሆናል። ኢየሱስ በዚህ ዓይነት የሚሠሩ መልካም ሥራዎች ዋጋ እንደሌላቸው ተናግሯል፤ (ማቴዎስ 6፡1-8)። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን ሁሉ እንደመርገም ጨርቅ ነው፤ (ኢሳይያስ 64፡6)። ስለዚህ «መልካም ሥራዎቻችን» እንኳ እንደ ኃጢአት ሊቆጠሩብን ይችላሉ፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያለመደገፋችን ሳናውቀው የምናውጅባቸው መንገዶች ይሆናሉና፤ ይቅር መባል መብታችን ስለሆነ የእግዚአብሔር ምሕረት እንደማያስፈልገን አድርገን እናስባለን።

እግዚአብሔር በሙሉ ልባችን፥ በሙሉ ነፍሳችንና በሙሉ አስተሳሰባችን መውደድ በምንጀምርበት ጊዜ ብቻ (ማቴዎስ 22፤37፤ዘዳግም6፡5)፥ እራስን መውደድ፥ የእራስን ፈቃድ ማድረግ፥የራስን ፍላጎት ማሟላትና በራስ ብቁ እንደሆኑ ማሰብ እየቀነሰ ይመጣና የኃጢአት አስገዳጅነትም ይገታል።

« ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍፃሜ ነው፤ » (ሮሜ13፡8-10፤ በተጨማሪም ገላትያ 5፡14፤ዮሐንስ 7፡18፤2ኛ ቆሮንቶስ 5፡15፤ገላትያ 2፡20-21 ተመልከት)።

«ኃጢአት ከእግዚአብሔር ይልቅ እራስን የማስቀደም ወይም በአሉታዊ መልክ የመምረጥ መሠረታዊ ነገር ነው።.........ኃጢአተኛ በምንም ነገር ላይ ባልተመሠረተ ቅድመ ሁኔታ እራስን ለእግዚአብሔር ከመስጠትና እግዚአብሔርን የሕይወት ማዕከል ከማድረግ ይልቅ እራሱን የሕይወቱ ማዕከል በማድረግ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር በተቃውሞ ውስጥ ይመድባል፤ ደግሞም የራሱን የግል ፍላጎት ዋነኛ ውስጣዊ ዓላማ፥የራሱን የግል ፈቃድ ቀና ሕግ ያደርጋል።»

(ኤ.ኤች. ስትሮንግ «በሚገባ የተደራጀ የሥነመለኮት ትምህርት» ገጽ 572።)

## ኃጢአት ዓለም አቀፋዊ ነው

ኃጢአት ዓለም አቀፋዊ ነውና እያንዳንዱ ሰው «ከኃጢአት በታች» ነው። (ገላትያ 3፡22)።

አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች የበለጠ ግልጽና ከፉ በሆነ መንገድ ኃጢአትን ያደርጋሉ። ኃጢአት እንደገኘ መመሪያ ማድረግ ግን ሁሉንም ሰው የሚበክል ማንንም የማይተው ነው።

«የማይበድል ሰው የለምና፤» (1ኛ ነገሥት 8፡46)።

«ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለምና፤» (መዝሙር 143፡2)።

«ልቤን አነፃሁ ከኃጢአትም ጠራሁ የሚል ማን ነው?» (ምሳሌ 20፡9።)

«ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር ጎድሎአቸዋል» (ሮሜ 3፡23)

«ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም!»

(1ኛ ዮሐንስ 1፡8።)

የመጀመሪያው ሰው አዳም ኃጢአትን አድርጓል! (ዘፍጥረት 3፡16-19፤ሱረቱ 2፡36፤7፡22-23።)

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርዓን ነቢያትን እንኳ ኃጢአትን እንዳደረጉ ይናገራሉ፡-

- አብርሃም ኃጢአት አድርጓል! (ዘፍጥረት 12፡9-20፤ 20፡1-10፤ ሱረቱ 26፡82)።

- ሙሴ ኃጢአት አድርጓል! (ዘጸአት 2፡12፤ ዘዳግም 32፡51፤ሱረቱ 28፡15-16)።

- ዮናስ ኃጢአት አድርጓል! (ዮናስ 1፡1-12፤ ሱረቱ 37፡142)።

- ዳዊት ኃጢአት አድርጓል! (2ኛ ሳሙኤል 11፡1-27፤ሱረቱ 38፡24-25)።

በቁርዓን ትምህርት መሠረት መሐመድ እንኳ ይቅርታን እንዲጠይቅ ታዟል (ሱረቱ 47፡19፤48፡1-2)። ኃጢአትን ያላደረገ አንድ ብቻ ሲሆን እርሱ ኢየሱስ ነው።

እርሱ ኃጢአትን ጨርሶ አላወቀም! (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

እርሱ ኃጢአትን አላደረገም! (1ኛ ጴጥሮስ2፡22)።

እርሱ ያለ ኃጢአት ነበር (ዕብራውያን 4፡15)።

በተጨማሪም ከቁርዓን፥ ሱረቱ 19፡19 ተመልከት።

## የኃጢአት ምንጭ

ሰው በመጀመሪያ ኃጢአትን ያደረገው «እባቢቱ» ስለአባበለችውና ስለአታለለችው ነበር። በእባቢቱ የተመሠለው ሰይጣን፥ዲያብሎስ፥ሽይጣን ወይም ኢብሊስ ነው። ሰው ሰይጣንን ለመስማትና የማዳመጫ አካሉን ለመስጠትና ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰይጣንን ቃል ለመስማት ፈቃደኛ ነበር። ኢየሱስ ስለ ሰይጣን የሚከተለውን ይናገራል፡-

«እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ! እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል! ሐሰተኛ፥ የሐሰትም አባት ነውና!» (ዮሐንስ8፡44)።

ኢየሱስ ይህንን ዐረፍተ ነገር ከመናገሩ በፊት ለማይታዘዙ አይሁዶች እንዲህ ብሏል፡-

«እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።»

እያንዳንዱ ኃጢአተኛ የሰይጣን ባሪያ ነው፤ (ሮሜ6፡16።» ነገር ግን መርሳት የሌለብን ነገር ዲያብሎስ በራሳችን የተበላሸ አእምሮ የጦርነት ተባባሪ ጓድ እንደሆነ ነው፡-

> «ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና። እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች። ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፤» (ያዕቆብ1፡13-15)።

## ኃጢአት የሚያስከትላቸው ነገሮች

- ኃጢአት ከእግዚአብሔር ይለያል፤ (ኢሳይያስ 59፡2)።

- ኃጢአት ጸሎትን ዋጋ ያሳጣል፤ (ሚክያስ 3፡4፤ ኢሳይያስ 1፡15፤ 59፡2-3)።

- ኃጢአት በአካልም ሆነ በመንፈስ ይገድላል፤ (ሮሜ 6፡23፤ ኤፌሶን2፡1-4፤ ሉቃስ 15፡24፤32)።

ኃጢአት ከመንግሥተ ሰማያት ያስቀራል፤ (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9-10፤ ገላትያ 5፡19-21፤ ኤፌ.5፡5፤ ራዕይ 21፡27)።

ከዚህ ሌላ የሰውን ክብር በመቀነስ ለስስታምነት፣ ኃጢአትን ለተሞሉ ፍላጎቶችና ለግለኝነት ባሪያ ያደርጋል ንጹሕ ኅሊናን ስለሚሰርቅ ደስታንና እርካታን ያሳጣል። ባጭሩ ሕይወትን በሙሉ የሚያበላሽ የሕይወት ሌባ ነው።

## ፈተና ቁጥር 7

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጥ። የሰጠኸው መልስ በገጽ 83 ከተሰጡ መልሶች ጋር አመሳክር።

1. እግዚአብሔርን መልካም ነገሮች በማድረግ ወደራሳችን ልንስበው እንችላለን ..............................

2. ኃጢአት የሚመነጨው ካለመታዘዝ ነው..............................

3. ከኢየሱስ በስተቀር ነቢያት ሁሉ ኃጢአትን አድርገዋል...............

4. እግዚአብሔር ኃጢአትን እንድናደርግ ምክንያት ይሆናል..............

5. ኃጢአት ከእግዚአብሔር ይለየናል ......................

# 8. የእግዚአብሔር ሕግ

ኃጢአት፥ በፍጥረት ሁሉ ላይ ያመጣውን ጥፋት በምንመለከትበት ጊዜ (ዘፍጥረት 3፡17-19)፥ ኃጢአት ምን እንደሆነ መረዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንገነዘባለን። ክፉና ደጉን መለየት እንችል ዘንድ እግዚአብሔር ሕጉን ሰጥቶናል።

ሕግ የባሕርይ ቋሚ መመዘኛ ነው። ዓለምን ሁሉ የሚቆጣጠሩ ሕጎች አሉ። የከዋክብትና የሌሎች ሕዋዎች እንቅስቃሴ፥ሳይንስና ሒሳብ፥ የሥነ ሕይወት ትምህርትና ሌሎች የፍጥረት ገፅታዎች ሁሉ በሕግ የተገዙ ናቸው። እነዚህ ሕጎች በሙሉ የእግዚአብሔር ፍጥረት አካል ናቸው። የሠለጠኑም ሆኑ ኋላቀር የሆኑ በዓለም ላይ የሚገኙ ሕዝቦች በሙሉ ጉዳዮቻቸውን ሁሉ ለመቆጣጠር የአኗኗር ሕጎችን ያበጃሉ።

አንድ ገበሬ መንጋውን ለመጠበቅ አደገኛ በሚመስለው አቅጣጫ በሙሉ አጥርን እንደሚያበጅ ሁሉ እግዚአብሔርም ለሰው ልጅ ሕግን የሰጠው እርሱን ለመጠበቅ እንጂ እገዳ ለማድረግ አይደለም። የእግዚአብሔርን ሕግ ለሚጠብቁ የሰው ልጆች ሁሉ እኩል መብትን ያረጋግጥላቸዋል።

## እግዚአብሔር ፈቃዱን ገልጧል

የእግዚአብሔር ፈቃድ የተገለጠው በሁለት መንገዶች ነው፡-

1. በሰው ኅሊና

> «አሕዛብ (አይሁድ ያልሆኑ ሁሉ) ..... ኅሊናቸው ሲመሰክርላቸው እርስ በእርሳቸው ሲካሰሱ ወይም ሲያመካኙ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያያሉ» (ሮሜ 2፡15። በተጨማሪ ቲቶ1፡15፤ ተመልከት)

2. በመጽሐፍ ቅዱስ

ሕግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «የእግዚአብሔር ሕግ»፥ «የጌታ ሕግ» በመባል ሲጠራ ሕጉ የተገለጠው በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ ስለነበር (ዘጸአት 20) «የሙሴ ሕግ» በመባልም ይታወቃል።

የሕጉ መንፈስ፥ ኢየሱስ በሰጠው በተራራው ስብከት ተጠናክሮ ተነግሯል ተተርጉሟልም፤ (ማቴዎስ 5-7)።

በአሥርቱ ሕግጋት ተጠቃሎ የቀረበው የእግዚአብሔር ሕግ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ደግሞም በሰውና በሰው መካከል ያሉ ጉዳዮችንም ሁሉ የሚሸፍን ነው።

## አሥርቱ ትዕዛዛት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ ሕጎችን እናገኛለን። የሥነ ምግባር ሕግ ለሰው ልጅ በሙሉ የሚሆን ሚዛናዊ የእግዚአብሔር ቋሚና ዘላለማዊ ፈቃድ ነው። ከዚህ ሌላ መሥዋዕት የሚቀርብበት መንገድ የሚደነግጉ የሥርዓት ሕጎች (ለምሳሌ ዘሌዋውያን 1-7)ና በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ላይ ትክክል ያልሆነውን ነገር የሚለዩ የልማድ ሕጎች የሚገልፁ ናቸው (ለምሳሌ ዘጸአት 2 ተመልከት)።

የሥነ ምግባር ሕጎች በሙሉ በአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ተጠቃለዋል:-

«ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ።

1. «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ»።

2. «በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸውም አታምልካቸውም ...

3. «የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ። እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና»።

4. «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። እስከ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው። አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ ...

5. «አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም»

6. «አትግደል»።

7. «አታመንዝር»።

8. «አትስረቅ»።

9. «በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር»።

10. የባልንጀራህን ቤት አትመኝ። የባልንጀራህን ሚስት፥ ሎሌውንም፥ ገረዱንም፥ በሬውንም፥ አህያውንም፥ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ፤» (ዘጸአት20፥2-17።)

ኢየሱስ እነዚህን ትዕዛዛት በሁለት ትዕዛዛት አጠቃሎአቸዋል:-

1. «ጌታ አምላክህን በፍፁም ልብህ፤ በፍፁም ነፍስህም፥ በፍፁም ሐሳብህም ውደድ።» ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ይህች ናት።

2. «ሁለተኛይቱ ይህችን ትመስላለች:-ሀባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድሀ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትዕዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል» (ማቴዎስ 22፥37-40)።

## ሕጉን ብንተላለፍ

አንድ ሰው አሥርቱ ሕግጋትን አሥር መገጣጠሚያ ካለው ሰንሰለት ጋር በማመሣሠል ከመጀመሪያው የላይ የሰንሰለቱ ጫፍ እግዚአብሔር አጥብቆ እንደ የያዘው ሲሆን ከታችኛው ጫፍ ላይ ደግሞ እኛ እንደ ተንጠለጠልን ተናገረ።

ለመውደቅ ስንት የሰንሰለት መገጣጠሚያ መበጠስ ይበቃል? አንድ ብቻ!

ለመውደቅ መበጠስ ያለበትስስንት ጊዜ ነው? አንድ ጊዜ!

ይህ መገለጫ በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ተረጋግጧል:-

> «ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል!» (ያዕቆብ2:10)።

ሕግ የተሰጠው ጻድቅ ፍርድን ለማስተላለፍ መመዘኛ ይሆን ዘንድ ነበር። ከዚያ በላይም ሆነ በታች አይደለም። ሕግ ይቅርታ አያደርግም፤ ፍርድንም አይሰጥም። ይህ የሚሆነው በሕጉ መሠረት በፈራጅ ነው። ስለዚህ ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በሕግ ይታረቅ ዘንድ ተስፋ ማድረግ አይችልም።

> «ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና!» (ሮሜ 3:20)።

> «.....በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበርና....» (ሮሜ 7:7)

ሕግ በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛው ነገር ምን እንደሆነ ያሳውቀናል። በእውነት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖረን የምንፈልግ ከሆነ መጀመሪያ ማድረግ ያለብን ነገር ሕግን ለመጠበቅ መሞከር ነው። ይቅር ያልተባሉ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ የመዘንጋት ዝንባሌ አለን። ለመሆኑ በእግዚአብሔር ፍፁም መመዘኛ መሠረት ሕግን መጠበቅ ይችላልን?

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

> «ሕግ መንፈሳዊ እንደሆነ እናውቃለንና እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ ሥጋ ነኝ። የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አደርጋለሁና፤ ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም። የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንኩ ሕግ መልካም እንደሆነ እመሰክራለሁ። እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ። በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም!» (ሮሜ7:14-19)።

## ሕግን የሚቃረን ሕግ

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ እየገፋህ በሄድክ ቁጥር የዚህ አሳዛኝ ደረጃ ምክንያት ምን እንደሆነ ትገነዘባለህ።

ሮሜ 7:21-23 አንብብና የጎደሉትን ቃሎች ሙላ

> «እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ። በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና። ነገር ግን በብልቶቼ...................ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ ....... ................የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ።»

በሰው ሁሉ ውስጥ ያለውን ይህን «የኃጢአት ሕግ» የሚያነሣሣና የሚቆጣጠር ዲያብሎስ ነው። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚፈልገውን «የአእምሮን ሕግ» እንኳ የሚቃወመው ኃጢአትን እንዳደርግ የሚገፋፋኝ ያ ኃይል ነው። እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ከዚህ የኃጢአት ተፈጥሮ ጋር ነው።

«ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም፤» (ገላትያ 5፡17)።

## ታዲያ ይህ ተስፋ የሌለው ጉዳይ ነውን?

የእግዚአብሔርን ሕግ ከተቀደሰ መመዘኛው ጋር ለመጠበቅ ከመሞከር የሚበልጥ ተስፋ አስቆራጭ ነገር የለም። ኢየሱስ ደግሞ ሲናገር እግዚአብሔር የሚመለከተው ሥራችንን ብቻ አይደለም። እርሱ አስተሳሰባችንን ሳይቀር በመመዘን እንኳ ይፈርድብናል ብሏል።

«(አታመንዝር)» እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፤» (ማቴዎስ 5፡27-28)።

ወደፊት የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጠበቅ ምንም ያህል ብንጥርም እንኳ ከዚህ ቀደም ግን ተላልፈነዋል። በኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ምክንያት ወደፊትም እንተላለፋዋለን። ይህ ነገር እግዚአብሔር በመልካምነቱ ወደሚያረጋግጠው ሕይወት የመድረሳችንን ዕድል ሙሉ በሙሉ ያጨልመዋል። እኛም እንደማንኛውም ሰው ከፍርድና ከኩነኔ በታች ነን። ከፍተኛ የሥነ ምግባር ባለቤት እንደነበረው እንደ ጳውሎስ፡-

«እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» (ሮሜ 7፡24) በማለት ልንጮህ ይገባል።

ነገር ግን ደስ የሚያሰኘው እግዚአብሔር የዚህን ጉዳይ መልስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠው መሆኑ ነው።

## ፈተና ቁጥር 8

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና መልስህን በገጽ 83 ካለው ጋር አወዳድር

1. እግዚአብሔር ሕጉን ለእኛ የሰጠባቸውን ሁለት ምክንያቶች ስጥ

1.1.............................................

1.2.............................................

2. የሕግ ተላላፊ ለመሆን ስንት ሕግን መተላለፍ ያስፈልጋል? ............

3. የእግዚአብሔርን ሕግ በራሳችን ኃይል መጠበቅ እንችላለንን? ............

4. ኃጢአታዊ ተፈጥሮአችን ያስከተለው ነገር ምንድነው? ..............

5. ክፍት ቦታውን ሙሉ፡-

እግዚአብሔር በሥራችን፥ በቃላችንና በ ............ ይፈርድብናል።

# 9. የኢየሱስ ሕይወት

አሁን ደግሞ የእያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ሕይወት ከማያምኑ ሰዎች ሕይወት ይልቅ የተለየ የሚያደርገውን ኢየሱስን ልናስተዋውቅህ እንወዳለን። የክርስትናን መንገድ አስተሳሰብ የበለጠ መረዳት እንድትችል ከወንጌላት መካከል አንዱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እንድታነብ እናበረታታሃለን። በመጀመሪያ የሉቃስን ወንጌል በማንበብ መጀመር ጥሩ ነው።

በእርግጥ እውነትን የምትፈልግ ከሆነ መጽሐፉን ማንበብ ከመጀመርህ በፊት የሚከተለውን ጸሎት ከልብህ ጸልይ፡-

> «እግዚአብሔር ሆይ፥ ይህንን መጽሐፍ በተከፈተ አእምሮ ለማንበብ እንድችል እርዳኝ፤ እውነትንም እንዳገኝና የኢየሱስንም ማንነት በትክክል እረዳ ዘንድ አስበኝ፤ አሜን።»

እንዲህ ብለህ ጸለይህ? በጣም ጥሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስን የበለጠ እየተረዳኸው ስትሄድ በምድር ላይ ከኖሩ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ልዩ ሰው እንደነበር ትረዳለህ። ከዚህ ቀጥለን ስለ እርሱ ሕይወት ከተጠቀሱ እውነታዎች ጥቂቶቹን ብቻ እስኪ እንመልከት።

## የልጅነቱ ወራት

ሙስሊም እንደ መሆንህ መጠን በእስልምና ትምህርትም ቀደም ብለህ እንደምታውቀው፥ ኢየሱስ የተወለደው ከድንግል ማርያም ነበር፤ (ማቴዎስ 1፡18-25፤ሱረቱ 19፡16-35)። በዚያን ጊዜ በእየሩሳሌም ገዥ የነበረው ንጉሥ ሄሮድስ «የአይሁድ ንጉሥ» መወለዱን ሰማ፤ (ማቴዎስ 2፡1-12)። እግዚአብሔርም በመልአኩ በኩል የማርያም ባል የነበረው ዮሴፍን፥ ማርያምንና ኢየሱስን ይዞ ወደ ግብፅ እንዲሸሽና ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ እንዲቆይ ነገረው፤ (ማቴዎስ 2፡13-23)።

ቀጥሎ የዮሴፍ የትውልድ ሥፍራ ወደ ነበረው ወደ ናዝሬት መመለሳቸውን ከሚናገረው ክፍል ሌላ (ሉቃስ 2፡38-40፥ 51-52)፥ ስለ ኢየሱስ እንደገና የምናነበው የ12 ዓመት ልጅ በነበረ ጊዜ ስለተፈጸመው ነገር ነው። ቤተሰቡ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ነበር። በዚያም በቤተመቅደስ በነበሩ ጊዜ ኢየሱስ፥በዕውቀቱ የተማሩትን ፈሪሳውያንን እንዳስደነቀ እንመለከታለን፤ (ሉቃስ 2፡41-50)።

## ኢየሱስ አገልግሎቱን ጀመረ

ኢየሱስ 30 ዓመት በሞላው ጊዜ «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ከሚሰብከው ከመጥምቁ ዮሐንስ (ያሕያ) ጋር ተገናኘ። መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን በተመለከተ ጊዜ ለሕዝቡ ወደ እርሱ እያመለከታቸው። «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐንስ 1፡29) አላቸው። መጥምቁ ዮሐንስም ይህንን በሚልበት ጊዜ ኢየሱስ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም በይስሐቅ ምትክ ይሠዋው ዘንድ እንደሰጠው በግ (ዘፍጥረት22፡13) ወይም ለኃጢአት መሥዋዕት ይሆኑ ዘንድ እንደሚሠዉት በጎች (ዘጸአት12፡1-13) መሆኑ ነበር።

ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ፣ በዲያብሎስ ወደ ተፈተነበት ወደ ምድረ በዳ መርቶታል። ዲያብሎስም በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ኢየሱስን ፈትኖታል። እነዚህም:- ለሰውነቱ ያስፈልግ በነበረው (ኢየሱስም በዚያ ሰዓት ይፈልገው በነበረ) በምግብ፥ በትዕቢት፥ ለሥልጣንና ለሐብት በሆነ ምኞት (ማቴዎስ 4:1-11፤ ዘፍጥረት 3:6፤ 1ኛዮሐንስ 2:16) ነበር።

ማቴዎስ 4:4፥7ና10 አንብብ።

ኢየሱስ ፈተናውን ያሸንፍ ዘንድ የረዳው ነገር ምን ነበር? ..................

..........................................................................

## ኢየሱስና በምድር ላይ የሠራቸው ሥራዎች

ኢየሱስ፥እስከሚገደልበት ጊዜ ድረስ በሕዝቡ መካከል የሰጠው አገልግሎት በሦስት ዋና ዋና የአገልግሎት መስኮች ላይ ያተኮረ ነበር:-

### 1. ማስተማር

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የተለወጠ ሕይወት ውጤት ስለሆነው፥ ሕያው እምነትንና ወደ ተግባር የሚተረጎሙበትን መመሪያ አስተማራቸው። በዚያን ዘመን፥ ሃይማኖት በአብዛኛው ውጫዊና ሥርዓታዊ ብቻ ነበር። ኢየሱስም እግዚአብሔር የሚፈልገው ውጫዊውን ነገር ሳይሆን ውስጣዊ አስተሳሰብንና ዝንባሌን እንደሆነ ገለጠ። (ለምሳሌ:- ማቴዎስ5:1-7፤ 7:27 አንብብ)።

ኢየሱስ አብዛኛውን ጊዜውን ከሥፍራ ወደ ሥፍራ በመዘዋወር ግለሰቦችን በተናጠል ብሎ ሕዝብን ደግሞ በአንድነት (ሉቃስ 4:42-53 ወዘተ) በማስተማር (ዮሐንስ 3:1-21፥4:7-30 ወዘተ) ያሳልፍ ነበር።

አሁን ማቴዎስ 7:28-29 አንብብ

የተሰበሰቡት ሕዝብ ለኢየሱስ ትምህርት የሰጡት ምላሽ ምን ነበር?

ለምን?

### 2. ተአምራትን ማድረግ

ኢየሱስ ያገለግለው ለነበረው ሕዝብ ከመራራቱ የተነሣ ሙታንን እስከ ማስነሣት ድረስ በርካታ የፈውስ ተአምራትን አድርጓል፤ (ማርቆስ 5:35-42፤ሉቃስ7:11-17፤ ዮሐንስ 11:38-44)። እነዚህ ተአምራት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዳግመኛ መምጣት የሚገልጡ ምልክቶች ነበሩ፤ (ማቴዎስ12:28)።

ከአንድ ጊዜ በላይ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ተአምራትን በማድረግ መግቧል፤ (ማርቆስ6:30-46፤8:1-10)። ማዕበሉን በማዘዝ ባሕሩ ፀጥ እንዲል አድርጓል፤ (ማቴ8:24-27)። በውኃውም ላይ እንኳ ተራምዷል፤ (ማቴዎስ14:22-33)። በዚህ ዓይነት ተከታዮቹ ቀስ በቀስ ኢየሱስ ተራ ሰው እንዳልሆነ የሚረዱበትን የብርሃን ውጋጋን እንዲያገኙ አደረገ።

# <u>የትምህርቱ አጠቃላይ ፈተና</u>

እባክህን መልስህን ጎላ ብለው በሚነበቡ ፊደላት ጻፍ

ሙሉ ስም.................................................

የልደት ዘመን..............................................

የፖስታ አድራሻ............................................

## ፈተናውን የመውሰጃ ትዕዛዝ

1. በተሰጠህ ሥፍራ ስምህንና አድራሻህን በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ጻፍ።
2. የጥያቄዎቹን መልሶች በዚህ የጥናት መጽሐፍ ውስጥና በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ታገኛለህ፤ ስለዚህ መልሶቹን ለማግኘት መጽሐፉንና መጽሐፍ ቅዱስህን ተጠቀም።
3. ፈተናውን በምትሠራበት ጊዜ እያንዳንዱ ጥያቄ በጥንቃቄ በማንበብና በግልጽ እስኪትረዳ ድረስ አስበህ ለመሥራት የምትችለውን ሁሉ ሞክር። ገጾቹን ትምህርቶቹን አንብበህ ከመጨረስህ በፊት መልስ ለመስጠት አትሞክር። ደግሞም ግምታዊ መልስ አትስጥ።
4. የጥያቄዎቹን መልሶች ከሌላ ሰው አትገልብጥ። የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስህን እራስህ ለማጥናትና ለመረዳት መቻልህ ላይ ነው እንጂ ከምትቀበለው ሰርተፊኬት (የምስክር ወረቀት) ላይ አይደለም።
5. ፈተናውን ካለፍክ የምስክር ወረቀት ይሰጥሃል። ይህ የምስክር ወረቀት ግን ትምህርቱን በትጋት እንድትከታተል የሚረዳ እንጂ በቤ.ክያን ውስጥ ሥራ የሚያሰጥ ወይም ለሌላ ጉዳይ የሚጠቅም አይደለም።
6. ፈተናውን ሠርተህ ስትጨርስ በፖስታ ቤት በሚከተለው አድራሻ ላከው፡- የሕይወት በር ድርጅት የፖ.ሣ.ቁ. 4937 አዲስ አበባ

## ለፈተናው ቢሮ አገልግሎት ብቻ የሚውል

## የፈታኙ ስም .................... ተማሪው ያገኘው ውጤት
## ምልክት

<u>የምልክቶቹ ትርጉም</u>

- እጅግ በጣም ጥሩ ውጤት (ከ95% በላይ)
- ጥሩ ውጤት (ከ80% በላይ)
- በቂ ውጤት (ይህንን ውጤት ያገኘ ተማሪ በሚገባ ያልተረዳውን ትምህርቶች ሊከልስ ወይም እንደገና ሊያጠና ይገባዋል።)
- የማለፊያ ውጤት (ይህንን ውጤት ያገኘ ተማሪ ግን ትምህርቱን በሙሉ መከለስ ያስፈልገዋል።

## ክፍል 1. እውነት ወይም ሐሰት ጥያቄዎች

ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች አንዳንዶቹ እውነት ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ሐሰት ናቸው። ስለዚህ በዐረፍተ ነገሮቹ አጠገብ እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጥ።

ለምሳሌ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምራል፤ እውነት።

በዚህ ምሳሌ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1፡1 መጽሐፍ ቅዱስ 60 የተለያዩ መጻሕፍት የያዘ መጽሐፍ ነው።...............

1:2 መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት መጽሐፍ ነው።.................................................................................

1:3 እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻለው እርሱ እራሱን ከገለጠ ብቻ ነው።..................

1:4 እግዚአብሔር የሚወደው የሚታዘዙትን ሰዎች ብቻ ነው።..............................

1:5 በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው።..............................

1:6 ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን አድርጓል።...................................................

1:7 በክርስቶስ ምትክ የተሰቀለው ሌላ ሰው ነበር።.........................................

1:8 ክርስቲያኖች የሚያመልኩት ሦስት አማልክትን ነው።..................................

1:9 መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።........................................................

1:10 ኃጢአትህን ይቅር እንደተባለ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ።...............................

## ክፍል 2. ትክክለኛውን ሐረግ በመምረጥ ዐረፍተ ነገሩን ማሟላት።

ከዚህ በታች በተሰጡት ዐረፍተ ነገሮች የጎደለውን ዐረፍተ ነገር ሊያሟሉ የሚችሉ ሁለት ወይም ሦስት ሐረጎች ቀርበዋል። ከእነዚህ ሐረጎች መካከል አንዱ ብቻ ትክክለኛ ነው። በጥያቄው ትይዩ በተሰጠህ ባዶ ማኅን ውስጥ የትክክለኛውን ሐረግ ፊደል ብቻ ጻፍ። ጠቅላላ ዐረፍተ ነገሩን ለመጻፍ ግን አትሞክር።

### ለምሳሌ

### የዚህ ትምህርት (ጥናት) ዓላማ

ሀ. አንድ ሰው ዐረብኛ ቋንቋ እንዲማር ለማድረግ ነው።

(ለ.) አንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እምነት እንዲገባው ለመርዳት ነው።

ሐ. የመሐመድን የሕይወት ታሪክ ለመንገር ነው።

### በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ለጥያቄዎቹ መልስን ስጥ።

### 2:1 በመጽሐፍ ቅዱስ የምንመለከተው እግዚአብሔር:-

ሀ. ከብዙ አማልክት ተብለው ከሚጠሩ ማእቶች አንዱ ነው።

ለ. ሕያውና ብቸኛ አምላክ ነው።

ሐ. አሳባዊ (ግምታዊ) መገለጫ ነው።

### 2:2 መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው:-

ሀ. ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ነው።

ለ. እውነትን ለራሳቸው በሚስማማ መንገድ በማጣመም ነው።

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ ከኖረ ከረጅም ጊዜ በኋላ በኖሩ ሰዎች ነው።

### 2:3 መጽሐፍ ቅዱስ የሚታመን መጽሐፍ የሆነው:-

ሀ. ክርስቲያኖች ሁሉ ስለሚያምኑበት ነው።

ለ. አንዳንድ ክርስቲያኖች ብቻ ስለሚያምኑበት ነው።

ሐ. በውስጡ የተነገሩት ትንቢቶች በዝርዝር ስለተፈጸሙ ነው።

2:4 እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው:-

ሀ. ሰው እንደፈለገው እንዲኖር ነው።

ለ. እግዚአብሔርን እንዲወድና እንዲታዘዝ ነው።

2:5 ኃጢአትህ ይቅር የሚባለው

ሀ. የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጠበቅ ስትሞክር ነው።

ለ. በርካታ መልካም ነገሮችን ስታደርግ ነው።

ሐ. በነቢያት ሁሉ ስታምን ነው።

መ. በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምን ነው።

2:6 ኢየሱስ ከሌሎች ነቢያት ሁሉ የተለየው:-

ሀ. ተአምራትን ስላደረገ ነው።

ለ. በሥልጣን ስላስተማረ ነው

ሐ. አንድም ኃጢአት ስላላደረገ ነው።

2:7 ኢየሱስ በአይሁዶች የሞት ፍርድ የተፈረደበት:-

ሀ. እግዚአብሔር ነኝ ስላለ ነው።

ለ. አብዮታዊ መሪ ስለነበረ ነው።

ሐ. ነቢይ ስለነበረ ነው።

2:8 ኢየሱስ የስሙ ትርጉም:-

ሀ. መሲሕ ማለት ነው።

ለ. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው።

ሐ. አዳኝ ማለት ነው።

2:9 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የምትችለው:-

ሀ. ዳግም ከተወለድክ ብቻ ነው።

ለ. በየዕለቱ ከጸለይክ ነው።

ሐ. ከተጠመቅክ ነው።

መ. የእግዚአብሔርን ሕግ ከጠበቅህ ነው።

2:10 መንፈስ ቅዱስ:-

ሀ. ኢየሱስ ከሞተ በኋላ የሚመጣ ነቢይ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ነው።

ሐ. እግዚአብሔርን የማገልገል ፍላጎት ነው።

2:11 እውነተኞች ክርስቲያኖች:-

ሀ. እራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው።

ለ. ክርስቶስን እንደአዳኝና ጌታ በግል የተቀበሉ ሰዎች ሁሉ ናቸው።

ሐ. እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚሞክሩ ሰዎች ናቸው።

መ. የቤ.ክያን አባል የሆኑ ሰዎች ሁሉ ናቸው።

ሠ. መልካም ሥራን መሥራት የሚወዱ ሰዎች ሁሉ ናቸው።

## 2:12 በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በፍርድ ቀን፡-

ሀ. ሁለተኛ የመዳን ዕድል ይሰጣቸዋል።

ለ. ይኮነናሉ።

ሐ. አይኮነኑም።

መ. አይፈረድባቸውም።

## ክፍል ሦስት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልሶች የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች

የሚከተሉት ጥያቄዎች ነጥብ የሚያስገኙ አይደሉም። በታማኝነት እውነተኛውን መልስ መስጠት ግን እንድንረዳህ ያስችሉናል።

3:1 ክርስቶስን እንደ አዳኝና ጌታ በግልህ ተቀብለኸዋል?.......................

3:2 የቤ.ክያን አባል ነህን?..........................................

3:3 አንድ ክርስቲያን እንዲጎበኝህ ትፈልጋለህን? (የምትፈልግ ከሆነ የስልክ ቁጥርህን ጻፍልን)...........................................

ያልተረዳኸው (ያልገባህ) ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ቢኖር ወይም እንዲመለስልህ የምትፈልገው ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ቢኖር ጻፍልን የጥያቄህን መልሶች በጽሑፍ እንልክልሃለን።

ሙሉ ስምህና አድራሻህ...............................

...............................

...............................

...............................

አባክህን! ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጠቃሚ ሆኖልህ ከሆነ ስላገኘኸው ጥቅም ጻፍልን።

..............................................

..............................................

..............................................

..............................................

ማቴዎስ 7፡28-29 አንብብና የጎደሉትን ቃላት ሙላ፡-

ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ.....................ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?

3. ሥልጠና

ኢየሱስ ሰዎችን የእርሱ ደቀመዛሙርት (ተማሪዎች) ይሆኑ ዘንድ ጠርቷቸዋል። ከእነዚህ መካከል አሥራ ሁለት ሰዎች በአንድ አነስተኛ ቡድን ሊያሰለጥናቸው ለያቸው፤ (ማርቆስ 3፡13-19፤ ማቴዎስ10፡1-3)። በኋላም እነዚህ ሰዎች መልእክቱን ለዓለም ሁሉ የሚያዳርሱ የእርሱ ሐዋርያት ሆኑ፤ (ዮሐንስ 20፡19-21፤ ማቴዎስ 28፡18-20፤ ማርቆስ16፡15-16፤ የሐዋርያት ሥራ1፡8)። ሐዋርያ ማለት የተላከ ማለት ነው።

ማርቆስ 3፤ 14 አንብብ። ኢየሱስ ሐዋርያቱን ያሰለጠነባቸው ሁለት መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ.......................

ለ.......................

ወዳጆቹና ጠላቶቹ

ኢየሱስ በሕዝቡ ዘንድ እጅግ የተወደደ ሰው ሲሆን የአይሁድ መሪዎች ግን እጅግ ይጠሉት ነበር። የኃጢአተኞችና ከኅብረተሰቡ የተገለሉ ሰዎች ወዳጅ ነበር፤ (ማቴዎስ 9፡9-13)። ቀራጮች በአይሁድ የሃይማኖት ሰዎች ዘንድ እጅግ የተጠሉ ነበሩ፤ ምክንያቱም በዝባዥና ጨቋኝ ለሆነው የሮም መንግሥት ይሠሩ ነበርና። ነገር ግን ከእነዚህ ቀራጮች አብዛኛዎቹ ጉድለታቸውን የተረዱና መንፈሳዊ ረሃብ የነበራቸው ናቸው፤ (ሉቃስ18፡9-14)።

በሌላ በኩል፥ ፈሪሳውያንና ሌሎች የሃይማኖት መሪዎች ግን ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንና ግዴታቸውን እጅግ በጥንቃቄ በመፈጸም በልባቸው ስለ ስኬታማነታቸው ይታበዩ ነበር። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ስለሚቃወም (ያዕቆብ 4፡6)፥ ልባቸው ከእግዚአብሔር እሩቅ ነበር። ዕለታዊ ግዴታቸውን፥ ሰው ሠራሽ ሥርዓትን ለመፈጸምና በሰው ለመታየት ብቻ ይፈጽሙ ነበር፤ (ማቴዎስ 6፡1-6፤ ማርቆስ 7፡6-9)።

እራሳቸውን ጻድቃን አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ማግኘት እንዳለባቸው አይገነዘቡም። የፈሪሳዊውና የቀራጩ ምሳሌ ለዚህ ጉዳይ የተሰጠ ሥዕላዊ መግለጫ ነው።

ሉቃስ 5፡31-32 በማንበብ የጎደሉ ቃላትን ሙላ፡-

«ኢየሱስም መልሶ .......... እንጂ ........ ባለመድኃኒት አያስፈልጋቸውም

............. ወደ ንስሐ እንጂ .......... ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።»

እነዚህ አባባሎች፥ ውጫዊና በሰው መልካም ምግባር የተገነባ ሃይማኖት እግዚአብሔርን ለማስደሰት ብቁ ነው፤ ከሚሉት ከአይሁድ መሪዎች ጋር ተቃውሞን እንዳስነሡ በደንብ ልትረዳ ትችላለህ።

## ያለኃጢአት የነበረው ፍጹም ሕይወቱ

ከዚህ ቀደም እንደተረዳኸው ከኢየሱስ በስተቀር ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው። ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ንጹህ በሆነ ሕይወት ተመላልሷል። ለዚህ ነው ለጠላቶቹ ሁሉ

«ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? (ዮሐንስ 8፡46) ለማለት የቻለው።

ማንም ሰው ይህንን ለማለት አልቻለም። በዕብራውያን መልእክት ስለ ኢየሱስ የሚከተለውን ነገር እናነባለን፡-

«ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም፤» (ዕብራውያን 4፡15)።

ይህ እጅግ አስፈላጊ የሆነ እውነታ ነው። ምክንያቱም የትኛውም ኃጢአተኛ የሌሎች ኃጢአተኞችን ዋጋ መክፈል አይችልም። ኢየሱስ በራሱ ምንም ኃጢአት አልነበረበትም። በዚህም ምክንያት ቀጥሎ የምንመለከታቸውን ሊፈጽም የመጣባቸውን ዓላማዎች ሁሉ ለማድረግ ቻለ።

## ፈተና ቁጥር 9

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና መልሶችህን በገጽ 83 ከተሰጡት ትክክለኛ መልሶች ጋር አወዳድር

1. መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ማን ብሎ ጠራው?

2. ኢየሱስ ለሦስት ዓመታት ሕዝቡን ባገለገለበት ጊዜ የአገልግሎቱ ዋና ዋና ክፍሎች የነበሩ ሦስት ነገሮችን ጥቀስ

2፡1..........................................................

2፡2..........................................................

2፡3..........................................................

3. ኢየሱስ፥ከሌሎች ሃይማኖታዊ መሪዎች ሁሉ የሚለየው እንዴት ነው?

..........................................................

# 10. የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ

ኢየሱስ የመጣው ለማስተማር፣ ለመፈወስና ደቀመዛሙርትን ለማሠልጠን ብቻ አልነበረም። ወደ ምድር የመጣበት ዋና ዓላማ በመስቀል ላይ በመሞት ለሰዎች ሁሉ የይቅርታን በር ለመክፈት ነበር። ምናልባት ይህን ለመረዳት አስቸጋሪ ሆኖ ልታገኘው ትችላለህ። ደቀመዛሙርቱም ይህን ለመረዳት ተቸግረው ነበር።

ሉቃስ18፡31-34 አንብብ።

ኢየሱስ መሞት ያስፈለገው ለምን ነበር? (ቁ.31)......................

እንዴት መሞት ነበረበት? (ቁ.32)..........................

ከዚያ በኋላ ምን ሆነ? (ቁ.33)..............................

ደቀመዛሙርቱ ለዚህ አባባል የሰጡት ምላሽ ምን ነበር?.................

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ምን ሊሆን እንዳለ ቢያንስ በሦስት የተለያዩ ጊዜያት ገልጾላቸው ነበር። ይህ ነገር የገባቸው ግን በኋላ በጣም ዘግይቶ ነበር። ነገሮቹ ሁሉ ግን ስለ እርሱ ከተናገሩ ትንቢቶች ጋር ፍጹም የሚስማሙ ነበሩ። [ኢየሱስ ከመወለዱ 700 ዓመታት በፊት የተነገረውን ትንቢት ከኢሳይያስ ምዕ.53 አንብብ]።

ስለዚህ 1/3 ኛው የወንጌሉ ዘገባ ለመጨረሻ ሳምንት ሕይወቱ ማለት ለሞተባት ሳምንት የተመደበው ባጋጣሚ አይደለም። ከጥንት ታሪኮች መካከል በአስገራሚ መረጃ ከተደገፉ ታሪኮች አንዱ ይህ ነው። ይህ ታሪክ በዓለምና በአስተሳሰቧ ላይ ከየትኛውም ታሪክ ይልቅ ተፅዕኖ ያደረገ ነው። በተጨማሪ ይህ በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የተደረገው ታሪካዊ ክንውን በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአማኞችን ሕይወት ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ በመለወጥ ላይ ይገኛል። ወደፊትም እንዲሁ ይቀጥላል።

## በኢየሱስ ላይ የተጠነሰሰ ሴራ

ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ በብዙ የተነገረለት ቢሆንም አብዛኞዎቹ የሃይማኖት መሪዎች ስለ መሢሑ ካላቸው ፅንሰ ሐሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ አላገኙትም። ለእነርሱ ኢየሱስ አስመሳይና የእግዚአብሔርን ስም የሚያሰድብ ነበር። የሠራውን ተአምራት አይተው ነበር። ነገር ግን ከሥራዎቹ በከፊል የተደረገው በሰይጣን ኃይል ነው ብለውታል፤ [ማቴዎስ12፡15-24]።

እነርሱ ሲጠብቁ የነበሩት ከሮም መንግሥት ጭቆና ነፃ የሚያወጣቸውን ፖለቲካዊ መሢህ ነበር። እነዚህ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች በኢየሱስ ላይ እጅግ ቀንተው ነበር። ይህም የሆነው በርካታ አይሁዶች ይከተሉት ስለነበረ ነው። ደግሞም እስራኤላውያን ብዙ ጊዜ የሚመሩት በካህናትና በሃይማኖት መሪዎች ስለነበር ኢየሱስን በቲዎክራሲ (በእግዚአብሔር አገዛዝ) ላይ የተነሣ ፈተና አድርገው ቆጥረውት ነበር። የሕዝቡ የወደፊት ነገርም አደጋ ላይ እንደሆነ ተሰምቶአቸው ነበር። ኢየሱስ አልአዛርን ከሞት ካስነሣ በኋላ በመጨረሻ ሊገሉት ያሴሩ ጀመር።

ዮሐንስ 11፡45-53 አንብብ።

አንዳንድ አይሁዶች በኢየሱስ ያመኑት ለምን ነበር? ...............

መሪዎቹ ኢየሱስን እንደ አደጋ (ፈተና) ያዩት ለምን ነበር?

(ቁጥር 48።)...............................................

ኢየሱስ መሞት የነበረበት ለምንድነው? (ቁጥር 51-52።)...............

..........................................................

## የፋሲካ በዓል

ከእስራኤላውያን ዋና ዋና ሃይማኖታዊ በዓላት አንዱ ፋሲካ ነበር። ይህ በዓል አይሁዳውያን በሙሴ መሪነት ከግብፅ ነጻ የመውጣታቸውን መታሰቢያ ነበር። ፈርኦን እስራኤላውያንን እንዲለቅ እግዚአብሔር በግብፅ ላይ የተለያዩ መቅሠፍቶችን ልኮ ነበር፤ (ዘጸአት7-11)። የመጨረሻው መቅሠፍት በኩር የሆኑ ሰዎችና እንስሳት ሞት ነበር። የጠቦት ደም በቤታቸው በሮች መቃን ላይ የቀቡ ቤተሰቦች ብቻ ከዚህ የሞት መቅሠፍት ያመለጡ ሲሆን ሌሎች ቤተሰቦች በሙሉ በመቅሠፍት ተመቱ፤ (ዘጸአት12፡1-6)።

ስለዚህ በዓሉ «የማለፍ በዓል (ፋሲካ)» ተብሎ ተጠራ። ይህም በዓል በየዓመቱ ይከበር ጀመር፤ (ዘጸአት12፡25-27፤ ዘሌዋውያን 23፡5-8)።

ይህ በዓል ከዚህ የጠለቀ ትርጉምም ነበረው። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ በዓል ቀን መገደሉ አጋጣሚ አልነበረም። «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» (1ኛ ቆሮንቶስ5፡7)። በመዝጊያው መቃን ላይ የተቀባው የጠቦት ደም እስራኤላውያንን በዚህ መቅሠፍት ከመመታት እንዲታለፉ እንዳደረገ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም የእግዚአብሔር ፍርድ በእርሱ ከሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ላይ እንዲያልፍ ያደርጋል። በዚያን ጊዜ በመቃን ላይ ደም መቀባት እንዴትና ለምን ከዚህ መቅሠፍት ሊጠብቅ ይችላል ብለው ሳይጠይቁና ሳይጠራጠሩ በእግዚአብሔር ታምነው በማድረጋቸው ከፍርድ እንዳመለጡ፥ ዛሬም እምነት የሚሠራው እንደዚህ ነው።

## የመጨረሻው እራት

ኢየሱስ በጠላቶቹ እጅ ከመያዙ ጥቂት ቀደም ብሎ የፋሲካን እራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር በመብላት አከበረ። ከደቀመዘሙርቱ አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ምልክትን በመስጠት ብቻ (ሳይታወቅበት) ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት አስቀድሞ ተነጋግሮ ነበር። ኢየሱስ ግን ይህንን አውቆ ስለነበር አስቀድሞ እንደነገረው እናያለን፤ (ማቴዎስ26፡25)።

በዚያን ጊዜ የአይሁድ በዓላት በልምድ የሚከበሩ ሆነው ነበር። በበዓሉም ወቅት የተወሰኑ ቃላት በተወሰኑ ሰዎች ብቻ ተደጋግመው በየዓመቱ ይቀርቡ ነበር። በዚህ በዓል ግን ኢየሱስ ከተለመደው አካሄድ የተለየ ነገርን አደረገ።

ሉቃስ 22፡15-20 በማንበብ የጎደሉትን ቃሎች ሙላ፡-

« .............. የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው። ይህ ጽዋ .......... በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።»

ይህ አዲስ ቃል ኪዳን ወይም አዲስ ኪዳን ማለት ከእንግዲህ በኃጢአት ላይ ተስፋ ልንቆርጥና ከሞት በኋላ ያለውን ፍርድ ልንፈራ አይገባም ማለት ነው። እራሳችንን ለእርሱ ሙሉ በሙሉ አሳልፈን ስንሰጥና በእርሱ የተሰጠንን ይቅርታ በታላቅ አክብሮት ስንቀበል ሥጋው ለእኛ እንደተቆረሰና ደሙ ለእኛ እንደፈሰሰ እንገነዘባለን። ክርስቲያኖች ይህንን ምልክታዊ የሆነውን ሥርዓት፥ በየጊዜው በሚያካሂዱበት ቋሚ በሆኑ የአምልኮ ፕሮግራሞቻቸውና ከኃጢአታቸው ንስሐ በመግባት አዲስ ቃል ኪዳን በሚሰጣቸው የተሟላ ይቅርታ ሐሴት በሚያደርጉበት ጊዜ ሁሉ ያስታውሱታል፤ (ዕብራውያን 9፡16-28፤8፡6-13)። (አዲሱ ቃል ኪዳን መሥዋዕታቸው ወደ እግዚአብሔር ታላቅና የመጨረሻ መሥዋዕት ወደሆነው ወደ ኢየሱስ የሚያመለክት የነበረውን አሮጌውን ኪዳን ተክቷል።)

## የኢየሱስ ለፍርድ መቅረብና ሞቱ

በዚያው ምሽት ኢየሱስ ጌቴሰማኒ በተባለው የአትክልት ሥፍራ ተያዘ። በምሽትም ከአይሁድ ሕግ በተፃራሪ በሊቀካህኑና፥ በካህናት አለቆችና በሽማግሌዎች ሸንጎ ፊትም ቀረበ።

ማቴዎስ 26፡59-66 አንብብ።

የካህናት አለቆችና የሽማግሌዎች ሸንጎ ትክክለኛ የሆነ ፍርድን ያልፈለገው ለምን ነበር?

..........................................................

ኢየሱስ ከተከሰሰባቸው ነገሮች የተቀበለው የትኛውን ነበር? (ቁጥር 63።)

..........................................................

ኢየሱስ በተጨማሪ እራሱን ምን ብሎ ጠራ? (ቁጥር 64)።

..........................................................

የካህናት አለቃው ለዚህ ጉዳይ የሰጠው መልስ ምን ነበር? (ቁጥር 65)።

..........................................................

የተሰጠው ፍርድስ ምን ነበር? (ቁጥር 66)።

..........................................................

አይሁዶች፥ ኢየሱስ እራሱን «የሰው ልጅ» ብሎ በመጥራቱ እግዚአብሔርን ተሳድቦአል አሉ። ምክንያቱም የእርሱን እውነተና ማንነት ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም። «የሰው ልጅ» የሚለው ሐረግ የሚሰጠውን ትርጉም ከዳንኤል 7፡13-14 ላይ ያውቁ ነበር።

> « በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፤ በዘመናት ወደሸመገለውም ደረሰ፤ ወደፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።»

የአይሁድ ባለሥልጣናት የሞት ፍርድ የማስተላለፍ መብት አልነበራቸውም። ይህ ሊደረግ የሚችለው ምድሪቱን ይገዙ በነበሩ በሮማውያን ብቻ ነበር። ስለዚህ አይሁዶች በመጀመሪያ ወደ አገረ ገዥው ወደ ጲንጤናዊው ጲላጦስ ዘንድ አቀረቡት።

የሐንስ 18፡28-19፡25 አንብብ።

አይሁዶች ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ ዘንድ ያቀረቡት ለምን ነበር? (ቁ. 31።)

..........................................................

የጲላጦስ ፍርድ ምን ነበር? (ቁጥር 38፥4፥6።) ..................

ኢየሱስ የተሰቀለው ለምን ነበር? (ቁጥር 12፥16።) ..................

ስለዚህ ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ያህል ከፍርድ ቤት ቀርቦ ሕግ ምንም ጥፋት ያልተገኘበት ቢሆንም እንኳ እንዲሞት ተፈረደበት።

ኢየሱስ የተፈረደበት የሞት ፍርድ እንዴት እንደተፈጸመ ከዮሐንስ 9፡17-37 አንብብ

..........................................................

ጠላቶቹ በመስቀል ላይ ሰቅለው የገደሉት ኢየሱስ፥እራሱ መሆኑን በምን እናውቃለን?

ኢየሱስ፥ እውነተኛ የሥጋ ሞት መሞቱንስ በምን እናውቃለን?

..........................................................

## ኢየሱስ ተነሥቷል!

በዚያን ዘመን ብዙ ሰዎች በስቅላት ይቀጡ ነበር። ኢየሱስ ሞቶ ቢቀር ኖሮ በዝርዝር የተፈጸመ ስለ እርሱ ጉዳይ የተነገሩ ትንቢቶች ቢኖሩም እንኳ እንደሌሎቹ፥ በሞት እንደተቀጡ ሰዎች እርሱም አስመሳይ ነው ሊባል ይችል ነበር። ጠላቶቹ ምንም ዓይነት ጥንቃቄ ቢያደርጉም እንኳን ኢየሱስ ግን በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ።

ማቴዎስ 27፡57-65 አንብብ።

ዮሴፍ የኢየሱስን መቃብር ያተመው እንዴት ነበር? ..................

ሊቀ ካህናቱ የኢየሱስን መቃብር ያተሙት እንዴት ነበር? ..............

..........................................................

ይህንና በሌሎች ወንጌላት የተመዘገቡትን ድርጊቶች ስንመለከት ኢየሱስ ገና በሕይወት ይገኝ ዘንድ ጨርሶ የማይቻል እንደነበረ እንመለከታለን። ደቀመዛሙርቱም ሬሳውን ሊሰርቁ የሚችሉበት ሁኔታ ጨርሶ አልነበረም። ሊቀ ካህናቱና ፈሪሳውያን ሰርቀውት ቢሆን ኖሮ ደግሞ ደቀመዛሙርቱ ተነሥቷል እያሉ ማውራት ቢጀምሩ ወዲያውኑ በድል ስሜት ማስተባበል ነበረባቸው። ስለዚህ የቀረውና እውነተኛው ነገር አንድ ብቻ ነው! ይኸውም፡- ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ ዛሬም በሕይወት አለ!

ማቴዎስ 28፡1-15 አንብብ

ድንጋዩን ያንከባለለው ማን ነበር? ......................................

ወታደሮቹ የተከፈላቸው ምን እያሉ እንዲያወሩ ነበር? ......................

.........................................................................

ማንኛውም የሮም ወታደር በተበቃ ተረኛ ሆኖ ሳለ ተኝቶ ቢገኝ በሞት እንደሚቀጣ ካስታወስን በአይሁድ መካከል የተሰራጨው ወሬ የማይረባና ዋጋ የሌለው እንደነበር እንረዳለን።

ኢየሱስ ለደቀመዘሙርቱ ከሞት እንደሚነሣ አስቀድሞ ደግሞ ደጋግሞ የነገራቸው ቢሆንም፥ ይህ ነገር በተፈጸመ ጊዜ ደቀመዛሙርት እራሳቸው በነገሩ እጅግ ተደንቀው እንደነበር መመልከት የሚያስገርም ነው፤ (ሉቃስ 24፡1-11)። በዚያው ምሽት ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ተገለጠና ከሞት መነሣቱን አረጋገጠላቸው፤ (ሉቃስ 24፡36-44)። ከሐዋርያት አንዱ የሆነውና በተጠራጣሪነቱ የታወቀው ቶማስ እንኳ በመጨረሻ ኢየሱስ መነሣቱን አምኗል፤ (ዮሐንስ 20፡28-29)።

ዮሐንስ 20፡24-29 አንብብ።

ኢየሱስ ማን እንደሆነ በተገነዘበ ጊዜ ቶማስ ምን አለ? (ቁጥር 28።)

.........................................................................

በምዕራፍ 14 ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለመወሰን በምንሞክርበት ጊዜ ይህን ዐረፍተ ነገር ብሚገባ መመልከት በጣም ይጠቅመናል።

## ኢየሱስ ወደ ሰማይ ዐረገ

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለ40 ቀናት ለደቀመዛሙርቱ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ሲሰጥ ቆይቶ ወደ ሰማያዊ ክብሩ ዐረገ። በመጨረሻው ጊዜም ተመልሶ ይመጣል።

የሐዋርያት ሥራ1፡1-11 አንብብ።

ወደ ደቀመዛሙርቱ የሚመጣው (የሚወርደው) ማን ነው? (ቁጥር4፥5፥8)።

.........................................................................

መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ የሚመጣው በእነርሱ የሕይወት ዘመን ነው ወይስ ከመቶ ዓመታት በኋላ? .....................................................

ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣው እንዴት ነው? ..................................

## ፈተና ቁጥር 10

የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን ወስንና መልስ ስጥ። መልስህንም በገጽ 83 ከሚገኙ መልሶች ጋር አወዳድር

1. ኢየሱስ እንዴት እንደሚሞት ያውቅ ነበር። ...................
2. ኢየሱስ መሞት ይገባው ነበር። ...................

3. ኢየሱስ ለፋሲካ በዓል አዲስ ትርጉም ሰጥቷል። ................

4. በኢየሱስ ምትክ የሞተው ሌላ ሰው ነበር። ................

5. ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስን ሬሳ ሰርቀው ወስደውት ነበር።...............

## 11. የእግዚአብሔር መንግሥት

ኢየሱስ ካስተማራቸው መሠረታዊ ትምህርቶች አንዱ የመንግሥተ ሰማያት ጉዳይ ነበር። በሌላ አነጋገር መንግሥተ ሰማያት የእግዚአብሔር መንግሥት በመባልም ይታወቃል። ኢየሱስ ገና ከአገልግሎቱ መጀመሪያ ጀምሮ «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» (ማቴዎስ 4፡17) በማለት ያስተምር ነበር።

### መንግሥተ ሰማያት ምንድነው? በየትስ ይገኛል?

ኢየሱስ ዘላለማዊ እውነቶችን ለመግለጽ ብዙ ጊዜ በዕለት ተዕለት ሕይወት የሚታዩ ታሪኮችን ይጠቀም ነበር። ኢየሱስ ተራ የሆኑ ሰዎች እንኳ እንዲረዱት ይፈልግ ነበር። በማቴዎስ 13፡1-52 ሰባት ምሳሌዎችን የያዘው ስለ መንግሥተ ሰማያት የሰበከውን ስብከት እናገኛለን። ከመጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ክፍሎች አንብባቸው።

አነበብካቸውን? ካላነበብካቸው አስቀድመህ አንብባቸው።

ስለ መንግሥተ ሰማያት የሚከተሉትን እውነታዎች ተመለከታለህ፡-

1. መንግሥተ ሰማያት፡- «ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ» እንደሚሉት አይደለም። (እውነተኛና ከሞት በኋላ የምናገኘው ዘላለማዊ ሥፍራ ነው።) ሆኖም መንግሥተ ሰማያት ንጉሡ በሚገዛበት በማንኛውም ሥፍራ በዚህ በምድር የሚጀምር ነው።

2. ያለማቋረጥ በጠላት (በዲያብሎስ) ጥቃት የሚሰነዘርበት ቦታ ነው፤ (ቁጥር 19፥25፥39።)

3. ከዘር ሁሉ የምታንስ ከምትመስል ከሰናፍጭ ቅንጣት ዓይነት በትንሹ ጀምራ የምታድግ ናት፤ (ቁጥር 31-33።)

4. «በስንዴው» መካከል «እንክርዳድም» አለ። እውነተኛ አማኞችን ከአስመሳዮች መካከል መለየት ሁልጊዜ የሚቻል ነገር ባይሆንም በፍርድ ቀን ግን ይለያሉ፤ (ቁጥር40-43፥49-50)።

5. መንግሥተ ሰማያት በቀላሉ በእኛ እጅ ሊወድቅ እንደማይቻል እንደ «ተሰወረ መዝገብ» ነው። አጥብቀን ልንፈልገውና ምናልባትም በርትቶ መቆፈርን የሚጠይቅ ይሆናል፤ (ቁጥር 44)።

6. መንግሥተ ሰማያትን ያገኘ ሰው ያገኘው ዘንድ ያለውን ሁሉ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው፤ (ቁጥር 44፥46)። [በተጨማሪ ማቴዎስ 6፡33፤ ማርቆስ 9፡47 ተመልከት።]

7. ማንም ሰው የመንግሥቱን መልእክት ሊሰማ፥ ሊረዳና ሊቀበል ያስፈልገዋል፤ (ቁጥር 23)።

በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንግሥት የሚባለው መንግሥተ ሰማያት በምድር ላይ ካሉ መንግሥታት ሁሉ የተለየ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡-

«......የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤.......እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና፤ (ሉቃስ 17፡20-21)።

የመንግሥቱ መምጣት በውጫዊና በሚታይ መንገድ ሳይሆን «ከልብ» ከሰው ውስጣዊ ክፍል የሚሆን ነው። ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና ውጫዊ መታጠብ ንጹሕ ልብን ሊፈጥር ጨርሶ አይችልም። ማቴዎስ 15፡10-20 አንብብ። ሰዎች መልካም ሥራን የሚሠሩት በሌሎች ሰዎች የመታየት ዝንባሌ ስላላቸው ነው። ኢየሱስ እንደነዚህ ዓይነት ሥራዎች ዋጋ እንደሌላቸው ይገልጻል፤ (ማቴዎስ6፡1-6፥16-21)።

መንግሥተ ሰማያት አሁን በዚህ ዘመን በምድር ላይ የሚሠራ ቢሆንም ዘላለማዊ መንግሥት ነውና በሙላት የሚገለጸው ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ነው፤ (ዳንኤል7፡13-14)። በዚህ መንገድ በኢሳይያስ 9፡6-7ና በኤርምያስ 23፡5-6 የተነገረው ትንቢት በመጨረሻ በክርስቶስ ይፈጸማል። ይህ ዘላለማዊ መንግሥት ለኖህ፥ለአብርሃም፥ለሙሴና ለዳዊት የተሰጠ ተስፋ ነበር፤ (ለምሳሌ መዝ. ዳዊት 89፡3-4፥27-29፥35-37)። የመንግሥቱ የመጨረሻ ምጽአት በሐሰተኛው ክርስቶስ ተቃውሞ ይገጥመዋል። ይህ ተቃውሞ ግን ከንቱ ነው፤ (ዳንኤል7፡25-28፤ ራእይ 20፡10)።

ኢየሱስ፥ ምሕረቱን ለመቀበል ለመረጡና በዚሁ መሠረት ሕይወታቸው ለተለወጠላቸው ሰዎች በፍርድ ቀን እንዲህ ይላቸዋል፡-

> «እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ»፤ (ማቴዎስ 25፡34)።

እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለዳዊት ተስፋ የተሰጠው የዘላለማዊው መንግሥት፥ ዘላለማዊ ንጉሥ መሚሐ ኢየሱስ እንጂ ማንም ሊሆን እንደማይችል ያመለክታሉ።

ምን ዓይነት ንጉሥ!

ኢየሱስ ኃይሉንና ንጉሥነቱን የገለጠበት ጊዜ ጨርሶ የለም ይልቁንም ስለ መንፈሳዊ መሪነት ፍጹም የተለየ ፅንሰ ሐሳብን አስተዋውቆአል።

ማቴዎስ 20፡25-28 አንብብና የጎደሉትን ቃላት ሙላ፡-

> «እንዲሁም የሰው ልጅ............ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ ...............አልመጣም..........»

በዮሐንስ 13፡1-15 እንደምናነበው፥ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እግር በማጠብ ይህንን መመሪያ ጨርሶ ሊረሳ በማይችል መንገድ ገልጾታል። ይህ ክብርና ምገስ ሁሉ የእርሱ የሆነ ጌታ ለሰው ልጅ ባለው ፍቅር ሊያገለግለን መረጠ። ይኸንን ፍቅር የምናውቀው እጅግ በጥቂቱ ነው፤ (1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4-7)።

ንጉሡ እራሱን ያስተዋውቃል

ኢየሱስ ሥልጣኑንና ልንታመንበት የምንችልበት መሆኑን ባደረጋቸው ብዙ ምልክቶችና ስለ እርሱ ተነግረው በፈጸማቸው ትንቢቶች አረጋግጧል። እርሱን በበለጠ ለማወቅ ጥረታችን ይሁን።

በተሰጡህ ጥቅሶች አንፃር ኢየሱስ እራሱን ምን ብሎ እንደሚጠራ ጻፍ።

ዮሐንስ 6:35-40:- ..................................

ዮሐንስ 8:12:-......................................

ዮሐንስ 10:7-18:-...................................

ዮሐንስ 10:27-30:-..................................

ዮሐንስ 11:25-26:-..................................

ዮሐንስ 14:6:-......................................

ዮሐንስ 14:9:-......................................

እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ከሦስት አማራጮች መካከል የአንዱን ብቻ እውነትነት ያረጋግጣሉ:-

1. ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ እንደሆነ በውሸት ስለተናገረ ሐሰተኛ ነው። ወይም

2. ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ እንደሆነ አድርጎ እራሱን በስሕተት በማመኑ ኢየሱስ እብድ ነው። ወይም

3. ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ በመሆኑ ኢየሱስ ሐቁን ተናገረ። የመጨረሻው ዓ.ነ. ብቻ እውነት መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሐቅ በሰው ሁሉ ላይና ባንተም ጭምር ላይ የሚያስከትለው ዘላለማዊ ነገር አለው።

ስለሆነም በእግዚአብሔር መገለጥ መሠረት ኢየሱስ ነቢይ መሆኑ እውነት ቢሆንም ከነቢያት መካከል አንዱ ብቻ አልነበረም። ነገር ግን ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ እንደሆነ ተገልጧል! (ራእይ 9:11-16)። አንድ ቀን በፍቅርም ሆነ በኃፍረት ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከካል! (ፊልጵስዩስ 2:5-11)።

## ፈተና ቁጥር 11

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጥና መልሶችህን በገጽ 83 ከሚገኙ መልሶች ጋር አመሳክር።

1. የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመጣው ከሞት በኋላ ብቻ ነው።............

2. የእግዚአብሔር መንግሥት በአማኞች መካከል ነው። ............

3. የእግዚአብሔር መንግሥት በዓመጽና በጦርነት የሚመጣ ነው።............

4. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ነው።

. . . . . . . . . . . . . . . .

5. በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከሌሎቹ መለየት ቀላል ነው። . . . . . . . . . . . . . . . .

## 12. የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ መሆን እንዴት እንደሚቻል

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ መሆንን ማረጋገጥ ከሁሉም የላቀና እጅግ አስፈላጊ ነገር መሆኑ በዚህ ጊዜ ግልጽ መሆን አለበት። ጸሎቶችና ጾሞች ሌሎችም ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች በሙሉ ያለዚህ ዜግነት ዋጋ የላቸውም።

ኢየሱስ በማቴዎስ 7፡22 ላይ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስጠነቅቅ ብዙ ሃይማኖታዊ ሰዎች የመንግሥቱ አካል ዉርሶ እንዳልነበሩ በፍርድ ቀን ይገነዘባሉ አለ።

> «በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ሀጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ሀ ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ሀከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁሀ ብዩ- እመሰክርባቸዋለሁ።»

ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች መሆናችንን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

### በልደት የሚገኝ ዜግነት

ኢየሱስ አይሁዳዊ፥ የሥነ መለኮት ትምህርት ሊቅ ለነበረው ለኒቆዲሞስ በሚናገርበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግቢያ መንገድን ገልጧል።

ዮሐንስ 3፡1-21 አንብብ።

የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ምን ያስፈልገናል? (ቁጥር3።) ........ ...

.................................................................

ይህ ዳግም ልደት በሥጋዊ አካል ዳግም መወለድ ነውን? (ቁጥር 4።)..........

በቁጥር 6 መሠረት በቁጥር 5 የተጠቀሰው ውሃ ምንን የሚያመለክት ነው? ......

.................................................................

አንድ ሰው ዳግም የሚወለደው እንዴት ነው? (ቁጥር 8።)................

ኢየሱስ የመጣው ከየት ነው? (ቁጥር 13።)........................

እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያሳየው እንዴት ነው? (ቁጥር 16።).......

.................................................................

እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደዚች ምድር የላከው ለምን ነበር? (ቁጥር 17።).....

.................................................................

በእግዚአብሔር የማይፈረድበት ወይም የማይኮነን ማን ነው? (ቁጥር 18።).....

.................................................................

ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን ማን ነው? (ቁጥር 19፤ ዮሐንስ 8፡12).........

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ኢየሱስ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ወይም «የእግዚአብሔር ልጅ» ለመሆን ዳግም መወለድ አለብን ይላል። በመጀመሪያ በሥጋዊ አካል የተወለድን ብንሆንም የእግዚአብሔር መንግሥት አካል ለመሆን ደግሞ በመንፈስ እንደገና መወለድ አለብን። በመንፈሳዊ ሕይወትና በመንፈሳዊ ሞት መካከል ያለው ልዩነት የእምነት ውጤት በሆነው በመንፈሳዊ መወለድ ላይ የተመሠረተ ነው።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና፤» (ዮሐንስ3፡16።)

ወይም ደግሞ በዮሐንስ 1፡10-13 እንደምናነበው፥

«በዓለም ነበረ፤ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፤ ዓለሙም አላወቀውም። የእርሱ ወደሆነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።»

ወይም ደግሞ በገላትያ 3፡26 እንደምናነበው፥

«በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ።»

## የይቅርታ ቁልፍ

አንድ ቃል በተደጋጋሚ እንዴት እንደተደረገ ልብ ብለሃልን? ይህ በተደጋጋሚ የተነገረው ቃል «እምነት» የሚለው ቃል ነው። ዳግም የተወለዳችሁ በእምነት ነው።

ይህ ተአምር እንዲፈጸም የሚያደርገው እምነት ሕያው የሆነ እግዚአብሔር መኖሩን ከማመን የበለጠ ነገር ነው። የሚያድን እምነት የእግዚአብሔር መንገድ በሆነውና በኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኘው ይቅርታ መደገፍ ነው።

በዮሐንስ 3 እንደምትመለከተው እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ዓለም በእርሱ ይድን ዘንድ ወደዚህች ምድር ላከው። ሌላ መንገድ የለም።

ዮሐንስ 3፡36 በማንበብ የጎደሉትን ቃላት ሙላ፡-

«. . . . . . . . . . . . . . .የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። . . . . . . . . . . . . . . .

የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።»

እግዚአብሔር ይቅርታን የሚሰጥበት መንገድ ከሰው መንገድ ጨርሶ የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው። እኛ ይቅርታን ከእግዚአብሔር ዘንድ የምናገኘው የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ እንደሆነ እንገምታለን። ነገር ግን አስቀድመን በትምህርት 8 እንደተመለከትነው፥ በእግዚአብሔር መመዘኛዎች መሠረት የእግዚአብሔርን ሕግ

መጠበቅ ጨርሶ የማይቻል ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር አዲስ የይቅርታን መንገድ ከፍቷል።

«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በእርሱ በኩል የኃጢአት ስርየት እንዲነገርላችሁ በሙሴም ሕግ ትጸድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ፥ ሁሉ ያመነ ሁሉ በእርሱ እንዲጸድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፤»

(የሐዋርያት ሥራ 13፡38-39)።

«ጽድቅ» የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም «ኃጢአተኛ አይደለህም ብሎ ማወጅ» ወይም «ኃጢአተኛ እንዳልሆነ መቁጠር» ማለት ነው። ነገሩ ከይቅርታ በላይ ነው። አንድ ወንጀለኛ ኋላ ይቅርታ ቢያገኝም እንኳ ጥፋተኛ መሆኑ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ግን ይቅር በሚለን ጊዜ ከዚህ ቀደም ጨርሶ ኃጢአትን አድርገን እንደማናውቅ ያህል ነው።

«ዓመጻቸውን እምራቸዋለሁና ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም»

(ዕብራውያን 8፡12፤ ኤርምያስ 31፡34)።

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው። እርሱ ኃጢአትን ይጠላል። ኃጢአት በሞት መቀጣት አለበት። ደግሞም እግዚአብሔር አፍቃሪና መሐሪ ነው። የጠፉ ኃጢአተኞችን ይቅር ለማለት ይፈልጋል። ይህ የሚቻለው ኃጢአት የሌለበት ሰው ጥፋተኛ በሆነው ሰው ምትክ ቅጣቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ ብቻ ነው። ሰዎች ሁሉ ደግሞ ኃጢአተኞች ስለሆኑ፥ እግዚአብሔር እራሱ (ሮሜ 3፡23) ኃጢአት የሌለበትን ሰው ማዘጋጀት ነበረበት።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ፥ ኃጢአት ያለወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጢአት አደረገው፤» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

ይህንን ይቅርታ የመቀበያ ብቸኛው መንገድ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ መታመን ነው። ሮሜ 3፡20-31ን በሚገባ እስከምትረዳ ድረስ ደጋግመህ አንብበው።

ገላትያ 2፡15-16 አንብብ

ሰው ሊጸድቅ የማይችለው እንዴት ነው? ..............................

ሰው የሚጸድቀው ደግሞ እንዴት ነው? ..............................

## ቁልፉን ተጠቀም

እጅግ በጠና ታመህ፥ ሳለህ በዓለም ላይ ከሚገኙ መድኃኒቶች ሁሉ የተሻለውን ብታገኝ፥ እስካልወሰድከው ድረስ ሊረዳህ አይችልም፥ መታመምህን ስትገነዘብ ብቻ መድኃኒቱን ትወስዳለህ።

የአንድ የተዘጋ በር ቁልፉ ቢኖርህም እንኳ ቁልፉን እስካልተጠቀምክ ድረስ በሩ እንደተዘጋ ይቀራል። በበሩ መግባት በእርግጥ የምትፈልግ ከሆነ ግን በቁልፉ ትጠቀማለህ።

በተመሳሳይ ሁኔታ የደኅንነት ብቸኛ መግቢያ ወይም በር ኢየሱስ ነው፤ (ዮሐንስ 10፥9-10)። የክርስትናን እምነት ለመረዳት የሚያስችል ተገቢ ጥናት አድርገሃል። ምናልባትም ይቅርታ እንደሚያስፈልግህ ተገንዝበህ ይሆናል። በማርቆስ 1፥15 የተመዘገበውን የኢየሱስን የመጀመሪያ ስብከት አድምጥ።

«ዘመኑ ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ።»

ንስሐ መግባት ማለት ኃጢአትህን መተውና ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው። ኢየሱስ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ኃጢአተኛን እንዴት እንደሚቀበል የሚያስረዳ ታሪክን ተናግሯል።

ሉቃ. 15፥11-24 አንብብ።

ታናሹ ልጅ ድርሻውን የጠየቀው ለምን ነበር? (ቁጥር 12።)..............

.............................................

ጠይቶ የወሰደውን ድርሻውን እንዴት ተጠቀመበት? (ቁጥር 13።)..........

.............................................

የዓመፁ ውጤት ምን ነበር? (ቁጥር 15-16።)....................

.............................................

በመጨረሻ ምን ተገነዘበ? (ቁጥር 17።).......................

ከዚህ ግንዛቤ በኋላ ምን ለማድረግ ወሰነ? (ቁጥር 18-19።)............

ከዚህ ውሳኔው በኋላስ ምን አደረገ? (ቁጥር 20።)...................

ለወሰደው እርምጃ የአባቱ ምላሽ ምን ነበር? (ቁጥር 21።)............

ይህ አባት ለዚህ አጥፊ ልጅ ምን ሰጠው (ቁጥር 22-23።)..............

.............................................

ለምን? (ቁጥር 24።)...............................

ከሁሉ የተሻለውና ቆንጆ የነበረው ልብስ ኃጢአቱን የመሸፈን አምሣያ ነበር። ቀለበቱ ደግሞ በቤቱ የልጅነትን መብት እንደገና የማግኘቱ ምልክት ነበር። መጫሚያው ደግሞ ነፃ የሆኑ ሰዎች ብቻ የሚያደርጉት ነገር ስለነበር አዲስ ያገኘው የነፃነቱ አምሣያ ነበር። ስለ እርሱ መመለስ የተደረገው ግብዣ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ የሚመለስ ማንኛውም ሰው በሚያገኘው ይቅርታ የሚለማመደውን ታላቅ ደስታ የሚያሳይ ነው።

## ፈተና ቁጥር 12

ቀጥለው የተሰጡትን ቃሎች በተሰጡት ትክክለኛ ክፍት ቦታዎች ሙላ:-

ያለ ኃጢአት፥ ካመንክ፥ በመቀበል፥ ዳግም፥ መንፈሳዊ

ትክክለኛዎቹን መልሶች በገጽ 83 ላይ ታገኛቸዋለህ።

1. የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት .............. መወለድ አለብህ

2. ይህ ዳግም ልደት ................... ልደት ነው።

3. አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን .......... ነው።

4. መጽደቅ ማለት .............. ነህ መባል ማለት ነው።

5. በኢየሱስ ክርስቶስ ............... ኃጢአትህ ሁሉ ይቅር ይባላል።

# 13. የመንግሥተ ሰማያት ዜጋ የሕይወት አኗኗር ስልት

«በዚህ ወቅት ይቅርታ የሚገኘው በፀጋ ብቻ ነው የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የክርስቲያኖችን ሕይወት የሚነካው እንዴት እንደሆነ በማሰብ እየተደነቅህ ይሆናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በሚደረግ እምነት ብቻ እንጂ በአድካሚ ሃይማኖታዊ ምግባራት የማይገኝ እንዲሁ የሚሰጥ ርካሽ ይቅርታ» ኃጢአትን ወደተሞላ አኗኗር አይመራምን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት የሚቀጥለውን ማብራሪያ እንመልከት።

## ይቅርታ ነፃ ሲሆን ግን ርካሽ አይደለም

1ኛ ጴጥሮስ 1፡ 14-19 አንብብ።

በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱ ክርስቲያኖች ያልተዋጁት በምንድነው? (በቁጥር 18።)

..........................................................

እውነተኛው ሊከፈል የሚገባው ዋጋ ምን ነበር? (ቁጥር 19።).............

ክርስቲያኖች የተዋጁት ከምንድነው? (ቁጥር 14ና 18።)...............

እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ እማኝ የሚጠብቀው ነገር ምንድነው? (ቁጥር 15-17።)

..........................................................

ከነናቸው የተሰጡትን ቁጥሮች እያነበብክ ለጥያቄዎቹ መልስ ሰጥተሃልን? ኢየሱስ ሊከፍል ያስፈለገው ዋጋ ይህን ያህል እጅግ ከፍተኛ ከሆነ እግዚአብሔር ከሰው ከፍተኛ የሆነ የቅድስና አኗኗር ይጠብቃል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ላደረገው ነገር ምስጋና የማቅረቢያው መንገድ ይኸ ስለሆነ ነው። በሮሜ 6፡1-14 እንደምናነበው ፀጋ፥ ሰው ያለማቋረጥ ኃጢአትን እንዲሠራ የሚጋብዝ ነው ብለው የሚያስቡ ሰዎች ነበሩ። ለዚህ አከራካሪ ሐሳብ ጳውሎስ የሰጠውን መልስ ከእነዚህ ቁጥሮች ላይ አንብብ።

## አካባቢህን ተመልከት

አካባቢህን ስትመለከት ብዙ «ክርስቲያኖች» በሥነምግባር ጉድለት፥ በሰካራምነት፥ ታማኝ ባለመሆን፥ በስስት፥ በጥላቻና በትዕቢት ለምን ይኖራሉ? የሚል ጥያቄ ሊፈጠርብህ ይችላል። ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት ሕይወትን የሚኖሩ ሰዎች በእርግጥ ክርስቲያኖች ናቸውን?

ኢየሱስ፥በማቴዎስ 7፡21-23 ሲናገር ብዙ «ክርስቲያኖች» ሰብከት የሰበኩና በኢየሱስ ስም ብዙ ተአምራትን ያደረጉ ቢሆኑም እንኳ በመጨረሻው ቀን እራሳቸውን በዘለአለም ጥፋት ውስጥ እንደሚያገኙት ተናግሯል። «የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።»

ገላትያ 5፡19-21 አንብብና የሚቀጥለውን ዐረፍተ ነገር አሟላ፡-

«አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ..................» ስለዚህ በእንደዚህ ዓይነት ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች እራሳቸውን እንደ ክርስቲያን የሚቆጥሩ ቢሆኑም እንኳ፥ ክርስቲያን ናቸው ብለህ አታስብ።

## የክርስቲያን ሕይወት

ታዲያ ክርስቲያኖች መኖር ያለባቸው እንዴት ነው? አንድ ሰው በትክክል እንዳስቀመጠው «ክርስቲያኖች ፍጹማን አይደሉም፤ ነገር ግን ይቅርታን ያገኙ ናቸው»። ክርስቲያኖች ለራሳቸው ሳይሆን ለእግዚአብሔር የሚኖሩ ናቸው፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡14-15)። መልካም ተግባርን የሚያደርጉት ለመዳን ሳይሆን ስለዳኑ ነው፤ (ኤፌሶን 2፡8-10)።

አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚታዘዘው ከፍቅር የተነሣ ነው። (ዮሐንስ14፡21፥23)። ፍቅር ሊጠነከር የሚችለው አንዱ ከሌላ ጋር ሲገናኝ ነው። የማታውቀውን ሰው ልትወድ አትችልም። እንዲሁም ኢየሱስን ስለ ማንነቱና ስለ ምንነቱ ልትወደው የምትችለው ስታውቀው ብቻ ነው፤ አልታዘዝም ብለህ የምትጠላውም ስታውቀው ነው።

እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ኢየሱስን መውደድ ማለት ነው። ኢየሱስን መውደድ ማለት ደግሞ እግዚአብሔርን መውደድና (1ኛ ዮሐንስ 2፤22-23) ሰዎችን በተለይ ደግሞ አማኝ የሆኑ ወንድሞችና እኅቶችን መውደድ ማለት ነው። ኢየሱስ እንደተናገረው፥

> «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ፤» (ዮሐንስ 13፡34-35።)

ክርስቲያን ለእግዚአብሔርና ለወዳጁ ብሎም ለጠላቱ ፍቅር እንዳለው የሚታወቀው ለሌሎች ሰዎች በሚያደርገው እንክብካቤ ነው። (በሉቃስ 10፡25-37።) የሚገኘውን የሩኅሩኁን ሳምራዊ ምሳሌ አንብብ።

ክርስቶስ የሕይወትህ ጌታ ሲሆን፥ የሕይወትህ አቅጣጫ በሙሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ይውላል። ቤትህ፥ሥራህ፥ዝግሬህና ሌላም ሁሉ ለእርሱ ክብር ይሆናሉ። ለምሳሌ ቆላስይስ 3፡1-4፥6 አንብብና በዚያ ሥፍራ የተሰጡትን ትዕዛዛት በሙሉ ዘርዝር። ያገኘኸውን ነገር በሙሉ ብትመረምርና ብታጠቃልለው የአንድ ደስተኛ ሕይወት አጠቃላይ መግለጫ መሆኑን ትገነዘባለህ።

ኢየሱስ፥ የክርስቲያንን ሕይወት «ፍቅር» በሚል አንድ ቃል አጠቃሎታል፥ (ማቴዎስ 22፡35-40)። ይህ፥ ኢየሱስ የክርስቲያንን ሕይወት ያጠቃለለበት ቃል በአንድ ወቅት የክርስትና መሪ የነበረው አውግስጢኖስ የተባለው ሰው የሚከተለውን ሕግ እንዲደነግግ አድርጎታል፡- «እግዚአብሔርን ውደድና የምትፈልገውን ሁሉ አድርግ!» ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከወደድህ እርሱን ሊያስደስቱ የሚችሉ ነገሮችን ብቻ ለማድረግ ትሞክራለህና።

የክርስቲያኖች ጥረት ወደ ፍፁምነት መድረስ ቢሆንም፥ ሰዎች ስለሆንን በዚህ ምድር ሙሉ በሙሉ ፍፁማን ልንሆን አንችልም። ስለዚህ ለየቀኑ ውድቀታችን ፈውስ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ይቅርታን የምናገኝበትን መንገድ ከፍቶልናል፤ (1ኛ ዮሐንስ 1፡5-10፤ ምሳሌ 28፡13)።

## የስማያዊው ዜጋ የበዓል ቀናት

በየዓመቱ ልዩ የሆኑ የበዓል ቀናት ይከበራሉ። የሚያሳዝነው ነገር ግን በስም ብቻ ክርስቲያን የሆኑ ብዙዎች ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን መታሰቢያ ከሆነው ከገና በዓል ጀምሮ አብዛኛዎቹን በዓላት ፍፁም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማክበራችው ነው።

ከበዓላት ሁሉ ታላላቆቹ የስቅለትና የትንሣኤ በዓላት ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም። በስቅለት ቀን የክርስቶስን ሞት፣ በትንሣኤ ዕለት ደግሞ ከሞት መነሣቱን እናስባለን።

የበዓለ ሐምሳ በዓል የሚከበረው ከትንሣኤ በኋላ በሰባተኛው ሳምንት ሲሆን በደቀመዛሙርቱ ላይ መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ቀን የሚያስታውሰን ነው፣ (የሐዋርያት ሥራ 2፡1-13)። ከበዓለ ሐምሳ አሥር ቀናት በፊት ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገበት የዕርገት መታሰቢያ ነው፣ (የሐዋርያት ሥራ 1፡9-11)።

«የጌታ እራት» ወይም «ቅዱስ ቁርባን» ወይም «እንጀራውን የመቁረስ» ሥርዓት በዓል ደግሞ አንድ የተለየ ቀን ሳይበጅለት በተወሰነ ጊዜ በየእሑዱ ይከበራል። ይህ ሥርዓት (በዓል) ክርስቲያኖች ሞቱን ያስታውሱ ዘንድ ኢየሱስ እራሱ የደነገገው ነው፤ (ሉቃስ 22፡14-20፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡23-31)።

እያንዳንዱ ክርስቲያን፥ ኢየሱስ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት (ማቴዎስ28፡18-20)፥ በሕይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ በውኃ ይጠመቃል። «ጥምቀት» የሚለው ቃል መጥለቅ ወይም መነከር ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። የሚያመለክተውም የአማኞች ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የታጠበ መሆኑን ነው፤ (1ኛ ዮሐንስ1፡7)። ጥምቀት በተጨማሪ ለእግዚአብሔር ለመኖር ለኃጢአት መሞትን ያመለክታል፤ (ሮሜ 6፡3-14)።

### ፈተና ቁጥር 13

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጥ፡-

ትክክለኛውን መልስ በገጽ 83 ላይ ታገኛለህ።

1. ክርስቲያኖች በኃጢአት መኖራቸውን መቀጠል ይችላሉ። .............
2. ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው መዋደድ አለባቸው። .............
3. ክርስቶስ የሚለውጠው ሃይማኖታዊ ሕይወትህን ብቻ ነው። ..............
4. የስቅለት ቀን ኢየሱስ ከሞት የተነሣበት የመታሰቢያ ቀን ነው። ............
5. እያንዳንዱ ክርስቲያን መጠመቅ አለበት። ......................

# 14 ኢየሱስ፡ - ከነቢይ በላይ ነው

የመጽሐፍ ቅዱስን እምነት ለመረዳት በእርግጥ የምትፈልግ ከሆነ ማረጋገጫውን በታማኝነትና በንቁ አእምሮ ልታይ ይገባሃል። ምናልባት ለአንተ አዲስ የሆኑ ስለ ኢየሱስ የሚገልጹ በርካታ እውነታዎችን እስከአሁን ተመልክተህ ይሆናል። ይሁን እንጂ ምናልባት «አእምሮዬን አስተካክዬአለሁ፤ በተለያዩ እውነቶች ልታወናብደኝ አትሞክር» እንዳለው ሰው ይህንን አዲስ ብርሃን ላለመቀበል እየሞከርክ ይሆናል። ነገር ግን የክርስትና እምነት በተለያዩ እውነታዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ሐቅ ነው። እስኪ ቀጥለን እነዚህን ነገሮች እንመርምራቸው።

## ስሙን እንመልከት

ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት የኢየሱስን እናት ማርያምን ለጋብቻ አጭቶ ወደነበረው ወደ ዮሴፍ አንድ ሰማያዊ መልእክተኛ (መልአክ) መጣ።

ማቴዎስ 1፡18-25 አንብብ።

ለሕፃኑ ስም ያወጣው ማን ነበር? (ቁጥር 21።)........................

ለምን?..........................................................

በተጨማሪ የተሰጠው የነቢይነት ስም ማን የሚል ነበር? (ቁጥር 23።).........

ይህስ ምን ማለት ነው?.............................................

«ኢየሱስ» የሚለው ስም «የሽሁዋ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የአማርኛ ትርጉም ሲሆን ትርጉሙም «እግዚአብሔር ደኅንነታችን ነው ማለት ነው።» ይህ ስም በዚያን ጊዜ በጣም የተለመደና ብዙ ሰው የሚጠቀምበት ስም ቢሆንም ከሌላው ለየት የሚያደርገው እርሱ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያድናቸው» ስለነበረ ነው፤ (ማቴዎስ1፡21።)

ክርስቶስ የሚለው ስም የመጣው «መሽያ» (መሢሕ) ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የግሪክ ትርጉም ሲሆን ትርጉሙም በቀጥታ ካየነው «የተቀባ» ማለት ነው። በቀድሞ ጊዜ የሴሜቲክ ሕዝቦች ታሪክ፥ ነገሥታት (1ኛ ሳሙኤል16፡12-13)፥ነቢያት (1ኛ ነገሥት19፡16)ና ካህናት (ዘጸአት29፡7) ለአገልግሎት ሥፍራቸው ይቀቡ ነበር። ይህም ንጉሥን እንደ መቀባት ዓይነት ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት በሚሾመው ሰው ራስ ላይ ልዩ የሆነ ጣፋጭ ሽታ ያለው ዘይት ይደረጋል። ይህ መቀባት በአንድ በኩል ለእግዚአብሔር አገልግሎት የመስጠት ምልክት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህ አገልግሎት በእግዚአብሔር በራሱ የመመረጥ፥ የመጠራትና የመዘጋጀት ምልክት ነው። ቀስ በቀስም ይህ መሢሕ የሚለው ስም ነቢያት ለሚናገሩለት አንድ ለተለየ የዳዊት ዘር የሚያመለክት መሆኑ ግልጽ ይሆናል፤ (ዳንኤል 9፡25፤ዮሐንስ 4፡25)።

## ልደቱን እንመልከት

ሉቃስ 1፡26-38 አንብብ።

መልአኩ ሕፃኑን የገለጠው እንዴት ነበር? (ቁጥር 32፥35።)..............

በቁጥር 35 ላይ የምናገኘው ቃል የሚገልጠው አካላዊ ተግባር ነውን? . . . . . . . . .

ኢየሱስ የተፀነሰው በአካላዊ (ሥጋ) ተግባር ውጤት ያለመሆኑን እንዴት እናውቃለን? (ቁጥር 34፣ 37።). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

አንዳንድ ሙስሊሞች የክርስትና እምነትን ይህን ነጥብ በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል። ማንኛውም እውነተኛ ክርስቲያን ኢየሱስ የተወለደው በእግዚአብሔርና በማርያም መካከል በተፈጸመ የሥጋ ግንኙነት ነው ብሎ ይህንን እግዚአብሔርን የመሳደብ አሳብ አያራምድም። እንዲህ ዓይነቱ አሳብ ለማንኛውም ሙስሊም እንደሆነው ሁሉ ለክርስቲያንም እጅግ የተጠላ ነው።

አንድ ሙስሊም «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለውን ቃል በሚሰማበት ጊዜ የሚያየውን ችግር አንድ አነስተኛ መግለጫ ሊያቃልለው ይችላል። በግለይ ቋንቋ ቁልፉ «ኩቲሺ» ተብሎ ሲጠራ መክፈቻው ደግሞ «አና ኩቲሺ» በመባል ይጠራል። አና ኪቲሺ ማለት በቀጥታ ስናየው «የመክፈቻ ልጅ» ማለት ነው ማላይቶች ይህን ሲሉ አንድ «ኩትሺ» ከሌላ «ኩትሺ» ጋር ተጋብቶ በማርገዝ ኋላ «አና ኩትሺን» ወለደ ማለታቸው ነውን? አይደለም ነገር ግን ይህ መክፈቻ የዚህ ቁልፍ ነው ማለታቸው ነው እንጂ። ቁልፉን ደግሞ ያለ መክፈቻ ልንከፍተው አንችልም። ቁልፉ ያለ መክፈቻው ያልተሟላ ነው። እንዲያውም ጥቅም የለውም። ልክ እንደዚሁ በዐረቢያ አንድ መንገደኛ «የመንገድ ልጅ» ይባላል። ይህንን አባባል ማንኛውም ቅንና ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው በተሳሳተ መንገድ ሊረዳው አይችልም።

## አምላክነቱን እንመልከት

አሁን ይህንን ጥያቄ አጥብቀን ልንመለከተው ይገባል። ኢየሱስ ከነቢይ የላቀ ሊሆን ይችላልን? እርሱ «እግዚአብሔር ከኛ ጋር» ሊሆንልን ይችላልን?

አንድ አዲስ ፅንሰ ሐሳብ በሚያጋጥመን ጊዜ ልንሰጣቸው የምንችላቸውን ሁለት ምላሾች በመግለጫ እንመልከት። አንድ ከዚህ በፊት ከምናውቀውና ከለመድነው የተለየ አዲስ ዓይነት የጣሳ መክፈቻ ለሽያጭ ቢቀርብ፥ እንዲህ ዓይነት ስሜት ሊሰማን ይችላል:-

«እስከ ዛሬ ድረስ የምናውቀውን የጣሳ መክፈቻ የማይመስል ከሆነና የሚሠራውም እንደ ቀድሞው ዓይነት ካልሆነ የጣሳ መክፈቻ እንዴት ሊሆን ይችላል?» ብለን እንጠይቃለን ወይም «ጣሳን መክፈት ይችላልን? ከቻለ እንደ ጣሳ መክፈቻ ልቀጥረው እችላለሁ! » በማለት መቀበል ይቻላል። ኢየሱስ እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀውን ነገር ካወቀና የእግዚአብሔር ብቻ የሆነ ኃይል ካለው እርሱ ያለው ነገር ትክክል ስለሆነ ልንቀበለው እንችላለን። እግዚአብሔር እራሱን ለእኛ መግለጥ ያለበት በዚህ መንገድ ነው ብለን ከምናስበው ሐሳብ ሁሉ ባሻገር እርሱ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማራችሁትን አስታውሱ። ኢየሱስ የሠራቸውን በርካታ ተአምራት አስታውሱ። እርሱ ሙታንን አስነሥቷል፤ሽባን፥ ዕውርን፥ ደንቆሮንና ለምፃምን ፈውሷል፤ አጋንንትን ከሰዎች ውስጥ በሥልጣን አውጥቷል። ደግሞም ያለኃጢአት የኖረ ብቸኛ ሰው ነበር። በውኃ ላይ ተራምዷል፤ ማዕበልን ፀጥ አድርጓል። በርካታ ሰዎችን ለመመገብ ጥቂት ዳቦንና ዓሣን በመባረክ አብልቷል። ውኃን ወደ ወይን

ጠጅ ለውጧል። ሞትን ድል አድርጓል። በመጨረሻም የተከታዮቹ ዓይን እያየው በአካል ወደ ሰማይ አርጓል።

ቁርዓንም የራሱን ሐሳብ በሚገልጥበት ጊዜ ይህንን ያረጋግጣል:-

1. የተወለደው ከድንግል ነበር፤ (ሱረቱ 19:16-35)።

2. መሢሕ ነበር፤ (ሱረቱ 4:171)።

3. ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መንፈስ ነበር፤ (ሱረቱ 4:171)።

4. እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ (ሱረቱ 4:171)።

5. አንዳችም ኃጢአት አላደረገም ነበር፤ (ሱረቱ 19:9)።

6. በዚህ ዓለምና ከዚህም ዓለም በኋላ ዝናው የገነነ ነው፤ (ሱረቱ 3:45)።

7. ለሙታን ሕይወትን መስጠት ይችላል፤ (ሱረቱ 3:49 ከ22:73 ጋር)።

8. ወደ ሰማይ የተወሰደው በእግዚአብሔር ነበር፤ (ሱረቱ 4:158)።

9. የፍርድ ሰዓት እንደቀረበ ለማመልከት ዳግም ይመለሳል፤ (ሱረቱ 43:61)።

## የደቀመዛሙርቱን መረጃ እንመልከት

እባክህ ወደ ሙሴ ፈጥነህ አትድረስ። መረጃውን ምንም ልዩነት የማያደርግ ዳኛ አድርገህ ቁጠረው። የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ በሆነው በምሳሌ 18:13 እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን:- «ሳይሰማ ነገርን በሚመልስ ስንፍናና እፍረት ይሆንበታል።»

ቀጥሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተመዘገቡ ዐረፍተ ነገሮች አንዳንዶቹን አንብብና የተሰጡትን ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ታማኝ ሆነህ መልስ ስጥበት

1. ዮሐንስ 1:1-3፥10-12 አንብብ።

   የሚከተለውን ዐረፍተ ነገር በጎደለ ቦታ ሙላ:-

   «መጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም .........»

   ሁሉን ነገር የፈጠረ ማን ነው? (ቁጥር 3።).......................

   ቃል ማን ነው?.........................................

   የተቀበሉት ምን ይሆንላቸዋል? (ቁጥር 12።).....................

   ..............................................

2. ቆላስይስ 1:15-20 አንብብ።

   የሚከተለውን ዐረፍተ ነገር አሟላ:- «እርሱም (ኢየሱስ) ............ ምሳሌነው።የሚከተለውን ዐረፈተ ነገር አሟላ:- «እግዚአብሔር

. . . . . . . . . . . .ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም

አድርጎ. . . . . . . . . . . . . . . . ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአል።»

3. ዕብራውያን 1፡1-3፤7-10 አንብብ።

የሚከተለውን ዐረፍተ ነገር አሟላ፡- «እርሱም የክብሩ. . . . . . . . . . . . . . . .

የባሕርዩ. . . . . . . . . . . . . . . . . .ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ

በቁጥር 8 ላይ እግዚአብሔር ኢየሱስን ምን ብሎ ይጠራዋል? . . . . . . . . . .

በቁጥር 10 ላይስ ምን ብሎ ይጠራዋል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

4. ፊልጵስዩስ 2፡5-11 አንብብ።

በቁጥር 6 ላይ ኢየሱስ የተገለጠው እንዴት ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . .

በእርሱ ፊት የሚሰግደው ማን ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ምላስ ሁሉ ምን ብሎ ይመሰክራል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

«ምላስ ሁሉ» የሚለው ቃል አንተንም ይጨምራልን? በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ደግሞ ብዙ ጊዜ ኢየሱስን ማመልከታቸው ልንጠቅሰው የሚገባ ሌላ አስፈላጊ የሆነ እውነት ነው። ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ኢሳይያስ 6፡10ን ከ1ኛ ዮሐንስ 12፡40-41 ጋር አወዳድር።

ኢሳይያስ 44፡6ን ከራእይ 22፡13 ጋር አወዳድር።

መዝሙር 102፡26-28ን ከዕብራውያን1፡10-12 ጋር አወዳድር።

በተጨማሪ 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡20፤ ቲቶ2፡11-14፤ 2ኛ ጴጥሮስ1፤ 1፥2፥11ን ሮሜ 9፡5፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡16-18 አንብብ።

አንድ ሰው በእርግጠኝነት ኢየሱስን ነቢይ ብቻ ነው ሊል ይችላልን? እንዳየነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስን አምላክነት በተደጋጋሚ ይናገራል። ከኢየሱስ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው፥ እርሱ በሰዎች መካከል የሚያድር እንደሆነ በግልጽ ይረዳል።

## የኢየሱስን ቃላት እንመልከት

አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ፥እራሱን አምላክ ነኝ ጨርሶ አላለም የሚባል አነጋገር ይሰማል። እስኪ የሚከተለውን ዐረፍተ ነገር እንመርምር፡-

ራእይ 21፡6-7 አንብብ። ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- «ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል፤ አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።»

ዮሐንስ 20፡27-29 አንብብ። ቶማስ ኢየሱስ ከሞት መነሣቱን ካረጋገጠ በኋላ በመጨረሻ «ጌታዬና አምላኬ» አለው። ቶማስ ይህንን ምስክርነት የሰጠው በመጨረሻ በመሆኑና ለማመን በመዘግየቱ ከደረሰበት ግሣጼ በስተቀር ከኢየሱስ ዘንድ ለዚህ ጉዳይ ተቃውሞ አልገጠመውም።

ዮሐንስ 10፡24-33 አንብብ። ኢየሱስ «እኔና አብ አንድ ነን» አለ። አይሁዶችም ይህ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቁ ስለነበር ኢየሱስን በድንጋይ ወግረው ሊገድሉት ሞከሩ። «አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው» አሉት። ይህን በሚሉበት ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውት ቢሆን ኖሮ ሐሳቡን በትክክል እንዲረዱት ለማድረግና በድንጋይ ከመወገር ለማምለጥ መሞከሩ የማይቀር ነበር። እርሱ ግን በቀጥታ ተቃራኒውን ተናገረ! (ዮሐንስ 14፡6-10)።

ኢየሱስ በውኃ ላይ በመራመድ ማዕበሉን ጸጥ ካሰኘ በኋላ «በታንኳይቱም የነበሩት «በእውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብለው ሰገዱለት!» (ማቴዎስ14፡33)። ኢየሱስ ቀደም ብሎ በማቴዎስ 4፡10 ላይ «ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» ብሎ የተናገረ ቢሆንም ይህንን አምልኮ ተቀብሏል።

ስምዖን ጴጥሮስ ኢየሱስን «አንተ ክርስቶስ፥የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ሲለው ኢየሱስ አልገሠጸውም። ይልቁንም «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ» አለው! (ማቴዎስ 16፡16-17)።

ማርቆስ 2፡3-12 አንብብ። የሕግ አስተማሪዎች «ከአንዱ ከእግዚእብሔር በቀር ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ማን ይችላል?» አሉ። ኢየሱስ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን እንዳለው ያሳየው እንዴት ነበር? (ቁጥር 11።)

ኢየሱስ በካህናት ጉባኤ ፊት ለፍርድ በቀረበ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ፥ «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንክ እንደሆነ እንድትነግረን በሕያው እግዚአብሔር ስም አምልሃለሁ» አለው። ኢየሱስም ሲመልስ! «አንተ አልህ! ነገር ግን እላችኋለሁ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሊቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ» አለው! (ማቴዎስ 26፡63-64 ከዳንኤል 7፡13-14 ጋር አወዳድር)።

ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊትም ነበረ። በዮሐንስ 8፡58 ለአይሁዶች ሲነግራቸው «እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ» አላቸው።

ከ700 ዓመታት በፊት በኢሳይያስ 9፡6 የተነገረው ትንቢት በኢየሱስ የተፈጸመ መሆኑ ያለአንዳች ችግር በግልፅ የምንመለከተው ነው።

ኢሳይያስ 9፡6ን በማንበብ የጎደሉትን ቃሎች አሟላ:-

«ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም፥ ድንቅ፥ መካር ኃያል.......፥የዘለአለም........፥የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።»

## ስለ «ሥላሴ» እንመልከት

መጽሐፍ ቅዱስን በቁም ነገር የሚመለከት ማንኛውም ሰው በኢዮብ ምዕራፍ 36:26 ያለውን እውነት ቀይቶም ቢሆን ይገነዘባል።

«እነሆ እግዚአብሔር ታላቅ ነው እኛም አናውቀውም»

ማንኛውም ፍጥረት ፈጣሪውን በሚገባ የመረዳት ተስፋ እንደሌለው ብዙም ሳይዘገይ ግልጽ ይሆናል። እስካሁን ድረስ እንደተመለከትነው መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከተራ ነቢይ በላይ እንደሆነ ይገልጣል። እርሱ በእኛ መካከል የተገለጠ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነበር፤ ነውም። በሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ እግዚአብሔር እራሱን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚገልጽ እንመለከታለን። ሆኖም ግን እግዚአብሔር አንድ ነው! (ዘዳግም 6:4፣ ማርቆስ 12:29)።

በማቴዎስ 28:19 እንደምናየው የኢየሱስ ደቀመዛሙርት መጠመቅ ያለባቸው በአብና በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ በአንድ ስም እንጂ በስሞች አይደለም።

በኢሳይያስ 44:6 ላይ ደግሞ «እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም» የሚል ቃል እናነባለን። በኢሳይያስ 63:7-10 ባለው አንድ ወጥ ክፍል ውስጥ ግን እግዚአብሔር ጌታ፥ አዳኝ፥ የሕልውናው መልአክና መንፈስ ቅዱስ በመባል ተጠርቷል። በመላ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህ መለኮታዊ ባሕሪዎች ለሦስቱ የሥላሴ አካላት በየተራ ተሰጥተው እናያለን።

ይህ ታላቅ ምስጢር ቤ.ክን እግዚአብሔርን በሥላሴነቱ እንድታስተምር አድርጓታል። ይህም (በሦስትነት ውስጥ ያለ አንድነት ማለት ነው)።

ሦስት፥ አንድ ሊሆን የሚችለው ግን እንዴት ነው?

ሦስቱ፥ እንድ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለመረዳት ምሣሌ ይረዳህ እንደሆን፥ ስለ ባለሦስት ማዕዘን ቅርፅ (ትሪያንግል) አስብ። ሦስት ማዕዘን ያሉት ቢሆንም ትሪያንግሉ ግን አንድ ነው። ከሦስቱ ማዕዘኖች አንዱ እንኳ ቢቀነስ ትሪያንግልነቱ ይቀራል ማለት ነው።

እግዚአብሔር አንድ ነው። እራሱን ግን በሦስት አካላዊ ሕልውናዎች ገልጧል፥ ይኸውም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በማለት ነው። ይህንን ጉዳይ በሚገባ መረዳት ወይም መከራከር አያስፈልገንም። እራሱ በገለጠው መንገድ ብቻ እርሱን ልናምነው ይገባል።

## የግል ውሳኔህን ተመልከት

ውድ አንባቢ ይህንን ምዕራፍ ከማጥናትህ በፊት መጸለይን አስታውሰሃልን? ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጡትን ጥቅሶች አነበብከን? ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ታስባለህ? በእውነት ከልብህ እርሱ እንደ ማንኛውም ነቢይ ነው ትላለህን? ላለፉት 20 ክፍለ ዘመናት የነበሩ ክርስቲያኖች በሙሉ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣ አምላክ መሆኑን አምነዋል። አንተስ ብትሆን እስካሁን የተጠቀሱትን መረጃዎች በታማኝነት ከመዘንክ ወደ ሌላ የማጠቃለያ ውሳኔ ልትደርስ ትችላለህን?

ፈተና ቁጥር 14

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና የአንተን መልስ በገጽ 83 ከሚገኘው ትክክለኛ መልስ ጋር አወዳድር።

1. አማኑኤል ማለት ምን ማለት ነው? ..............................

2. እንደመልአኩ ምስክርነት ኢየሱስ የማን «ልጅ» ነው? ................

3. ቶማስ ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስን ማን ብሎ ጠራው? ..................

4. የሚከተለውን የኢየሱስን ቃል አሟላ «እኔና አብ ................. ነን»

5. ኢየሱስ መኖር የጀመረው መቼ ነው? ..............................

# 15 መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነ

እስካሁን ድረስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ከአንድ ጊዜ በላይ አንብበሃል። አሁን ስለ እርሱ የበለጠ እንማራለን። እግዚአብሔር ለአማኞች ከሚሰጣቸው ታላላቅ በረከቶች አንዱን ወደ ማወቅ እየተቃረብን ነው። ሕያው የሆነው አንዱ እግዚአብሔር እራሱን እንደ ሥላሴ (በሦስትነት ያለ አንድነት) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገልጻል።

እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል፤ (ሮሜ 1፡7)።

እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል፤ (ቆላስይስ 2፡9፤ ዕብራውያን 3፡8)።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል፤ (የሐዋርያት ሥራ 5-3-4፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡17-18)።

እግዚአብሔር አንድ ነው፤ (ማርቆስ 12፡29)።

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ መጀመሪያና መጨረሻ የለውም ስለዚህ ዘለዓለማዊ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምናነበው የመጀመሪያ ተቅስ በዘፍ. ም.1 ቁ. 2 ላይ ሲሆን በመጨረሻ ደግሞ የምናነበው ከዮሐ. ራእይ ም.22 ቁ.17 ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጠው እርሱ በአማኞች ልብና አእምሮ ውስጥ የሚሠራውን ሥራ እንመለከታለን። እርሱ መንፈስ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜ በሁሉም ሥፍራ መሆን ይችላል። ስለሆነም በአማኞች ሁሉ ውስጥ በመኖር ያስተምራቸዋል ይመራቸዋልም።

ዮሐንስ 14፡15-17 አንብብ።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው ነው ወይስ ቁስ ነው? ...............

ከቁጥር 16-17 ባለው ክፍል መንፈስ ቅዱስ የተገለጠባቸው ሁለት ስሞች ምንና ምን ናቸው? ..........................................

መንፈስ ቅዱስን ሊቀበለው የማይችለው ማን ነው? .....................

መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው የት ነው? (ቁጥር 17።)...................

ሙስሊም አንባቢ ኢየሱስ በዚህ ቦታ የሚናገረው፡-

ሀ. ስለ መንፈስ አንጂ ስለ ነቢይ እንዳይደለና......................

ለ. ይህ መንፈስ በደቀመዛሙርቱ ሕይወት ውስጥ እንደሚኖር ወዲያውኑ ይገነዘባል።

..........................................

ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ይህ ቃል ስለ መሐመድ የሚናገር ያለመሆኑ ግልጽ ነው።

## የመንፈስ ቅዱስ ስሞች

መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ የተለያዩ ስሞች ተጠርቷል:-

| | |
|---|---|
| የእግዚአብሔር መንፈስ | ዘፍጥረት 1:2፤ ኤፌሶን 4:30 |
| የጌታ መንፈስ | ሉቃስ 4:18 |
| የልጁ መንፈስ | ገላትያ 4:6 |
| የክርስቶስ መንፈስ | ሮሜ 8:9 |
| የቅድስና መንፈስ | ሮሜ 1:4 |
| የፀጋና የምገስ መንፈስ | ዘካርያስ 12:10 |
| የጥበብና የመገለጥ መንፈስ | ኤፌሶን 1:17፤ምሳሌ 8 |
| የጥበብ፥ የማስተዋል፥ የምክርና የኃይል መንፈስ | ኢሳይያስ 11:2 |
| የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ | ኢሳይያስ 11፤2 |
| የእውነት መንፈስ | ዮሐንስ 14:17፤ 15:26 |
| የፍቅር፥የኃይልና ራስን የመግዛት መንፈስ | 2ኛ ጢሞቴዎስ 1:7 |
| የልጅነት መንፈስ | ሮሜ 8:15 |
| አጽናኝ | ዮሐንስ 14:16 |
| መንፈስ ቅዱስ የሐዋርያት | ሥራ 1:5፥8፤ 2:1-4 |

## የመንፈስ ቅዱስ መምጣት

መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ሥፍራ ሁልጊዜ ያለ ነው። ሆኖም በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ የምናነበው የተወሰኑ ሰዎችን አንድ የተወሰነ ተግባር እንዲፈጽሙ፥ ለአንድ ለተወሰነ ዓላማ ይሞላቸው እንደነበር ነው። (ለምሣሌ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት ዘጸአት 31፤3፤ ዘኁልቁ 11:17፤ 24:2፤1ኛ ሳሙኤል 10:6፤ 1ኛ ዜና 28:12፤ ነህምያ 9:30፤ ኢሳይያስ 42:1፤ ሕዝቅኤል 1:5 ወዘተ)።

በአዲስ ኪዳን ግን መንፈስ ቅዱስ ወደ እያንዳንዱ አማኝ እንደሚመጣና እንደሚሞላው ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቶአል። ይህ ተስፋ መፈጸም የጀመረው ክርስቲያኖች በአንድነት ተሰብስበው በነበሩበት በበዓለ ኃምሳ ቀን ሲሆን «በሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው»። (የሐዋርያት ሥራ 2:4)። በሐዋርያት ሥራ 4:31ና 10:44-46 እንደምናነበው ይህ ነገር በተደጋጋሚ ተፈጽሟል።

ጳውሎስ የተባለው፥ ሳኦል በተለወጠ ጊዜ እንደሆነው መንፈስ ቅዱስ ወደ እያንዳንዱ አማኝ በመምጣት በውስጡ ይኖራል፤ (የሐዋርያት ሥራ 9:17-19)። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-

«የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም፡» (ሮሜ 8:9)። ስለዚህ ልዩ ስለሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ብሉይ ኪዳንም አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፤ (ሕዝቅኤል 36:26-27)። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለነበሩ አማኞች ሲጽፍ እንዲህ በማለት ሊያስታውሳቸው አስፈላጊ ነበር፡-

«የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? (1ኛ ቆሮንቶስ 3:16።)

አንድ አማኝ እንደ ራሱ ፈቃድ መኖሩን እስከቀጠለ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አይችልም። በመንፈስ ቅዱስ ሳይሞላ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ሊኖር ይችላል። መንፈስ ቅዱስ አንድን አማኝ የሚሞላው እራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ሲሰጥ ብቻ ነው፤ (ሮሜ 12:12፤ ኤፌሶን 5:38።)

## በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ማድረግ ያለብህ ነገሮች

1. በተሰቀለውና ከሞት በተነሣው በክርስቶስ እመን፤ (ገላትያ 3:1-5)።

2. ለእግዚአብሔር ታዘዝ፤ (የሐዋርያት ሥራ 5:32)።

3. እግዚአብሔርን ጠይቅ፤ (ሉቃስ 11:13)።

4. እግዚአብሔር ፈቃዱን እንደሚያሟላ በእርሱ ታመን፤ (1ኛ ዮሐንስ 5:14-15)።

በሚቀጥለው ትምህርታችን መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ስለሚያደርገው ነገር እንማራለን።

## ፈተና ቁጥር 15

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና መልስህን በገጽ 83 ከሚገኝ ትክክለኛ መልስ ጋር አወዳድር፡-

1. ክርስቲያኖች የሚያመልኩት ስንት አምላክ ነው? ....................

2. መንፈስ ቅዱስ ሌላ ነቢይ ያለመሆኑን እንዴት እናውቃለን? .............

.................................................

3. መንፈስ ቅዱስ በእውነተኛ አማኞች ሕይወት ውስጥ ሁሉ ለመኖር የመጣው መቼ ነበ ር? .........................................

4. እግዚአብሔር እራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ እንደገለጠ የሚያብራራው ቃል የቱ ነው?

.................................................

5. በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን የሚሞላው ለምን ነበር?

.................................................

# 16. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሕይወቱ እንደሚኖር ማወቁ የእያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ደስታ ነው። እውነተኛው የክርስትና ሕይወት አስቸጋሪ ከባድና የማይቻል ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ የማይቻለውን እንደሚቻል ያደርገዋል። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጣችን ይሠራል። ይህንንም ሥራ እንዴት እንደሚሠራ ቀጥለን እንመልከት፡-

## ስለ ኃጢአታችን ይወቅሰናል

በኢየሱስ ክርስቶስ ባለማመናቸው ምክንያት ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው የሚወቅሳቸው መንፈስ ቅዱስ ነው፤ (ዮሐንስ16፡8-11)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ዐመፀኝነታችንን እንድናቆም ጥሪ ያደርግልናል፤ (ነህምያ 9፡30)።

## አዲስ ልደትን ይሰጠናል

መንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ ውስጥ ሲሠራ፥በተአምር ዳግመኛ እንዲወለድ ያደርጋል። የዚህም ሥራ ውጤት ሁሉን አዲስ ማድረግ ነው፤ (ዮሐ. 3፡8፤ 2ኛ ቆሮ.5፡17)።

## ዋስትናን ይሰጠናል

ይቅር እንደተባልንና በአዲስ ልደት አማካይነት የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ሙሉ ዋስትና ይሰጠናል፤ (ሮሜ 8፡13-16)። ቀጥሎም እግዚአብሔር እርሱን ለሚወዱ ሁሉ ያዘጋጃቸውን አስደናቂ በረከቶች ይገልጥልናል፤ (1ኛ ቆሮንቶስ2፡9-10)። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መሆናችንን የሚያረጋግጥልን ማኅተም ነው፤ (ኤፌሶን 1፡13-14፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡24)።

## የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለአማኞችና በአማኞች ሕይወት ውስጥ ይሠራል

እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገልገል የሚያስችል ንፁሕ ሕይወት እንዲኖረን ያዘጋጀናል። እግዚአብሔርን የሚፈራ ሕይወት እንዲኖረንም ኃይልን ያስታጥቀናል።

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጣቸውን ሌሎች በረከቶች ምን እንደሆኑ ፈልገህ አግኝ።

ቀጥለው ከተሰጡት ጥቅሶች ምን እንደተማርክ በጥቅሱ አንፃር ጻፍ።

መዝሙር 143፡10...........................................

ማቴዎስ 10፡19-20.......................................

ሉቃስ 2፡26-27...........................................

ዮሐንስ 14፡26............................................

ዮሐንስ 16፡12............................................

ዮሐንስ 16፡13-14.......................................

የሐዋርያት ሥራ 1፡8......................................

የሐዋርያት ሥራ 4:31..................................

የሐዋርያት ሥራ 8:29..................................

የሐዋርያት ሥራ 13:2-4..................................

የሐዋርያት ሥራ 15:28..................................

የሐዋርያት ሥራ 16:7..................................

የሐዋርያት ሥራ 20:28..................................

ሮሜ 5:5..................................

» 7:6..................................

» 8:11..................................

» 8:26-27..................................

ይህ ጥናት የተወሰነ ጊዜ እንደወሰደብህ እርግጠኛ ነኝ። ሆኖም ከዚህ ጥናትህ በኋላ እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ መኖሩ ምን ያህል ታላቅ ዕድል እንደሆነ መገንዘብህ መልካም ውጤት ነው።

በዮሐንስ 16:12 ኢየሱስ፥ ለደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው ቃል ገባላቸው። ከበዓለ ሐምሳ በኋላ በዚህ የተሰፋ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን የተለያዩ መጻሕፍትን በሁሉም ዘመናት ለኖሩ ለተለያዩ ሰዎች እንዲጽፉ መራቸው። ዛሬም ቢሆን እንኳ እነዚህን እውነቶች እንድናይና እንድንረዳ የሚረዳን እርሱ ነው።

## የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ

አንድ አማኝ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ቁጥጥር እራሱን የበለጠ በሰጠ ቁጥር «የመንፈስ ቅዱስ ፍሬም» በሕይወቱ የበለጠ እየታየ ይመጣል።

«የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው፤» (ገላትያ5:22-24)። ደግመህ ወደዚህ ዝርዝር ተመልከትና ከራስህ ሕይወት ጋር አዛምድ። በእርግጥ የዚህ ዓይነቱ ፍሬ እግዚአብሔርን ያስከብረዋል።

## መንፈስ ቅዱስን አትቃወሙ

መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ሊሰጠን የሚፈልጋቸውን በረከቶች ሳናገኝ ልንቀር እንችላለን፤ ይህም የሚሆነው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው:-

- መንፈስ ቅዱስን ስንቃወም (ኢሳይያስ 63:10፤ የሐዋርያት ሥራ 7:51)።
- መንፈስ ቅዱስን ስናሳዝን፥ (ኤፌሶን 4:30)።
- መንፈስ ቅዱስን ስንዋሽ፥ (የሐዋርያት ሥራ 5:3)።

- መንፈስ ቅዱስን ስንፈትን፥ (የሐዋርያት ሥራ 5፡9)።

- መንፈስ ቅዱስን ስናከፋፋ፥ (ዕብራውያን 10፡29)።

- መንፈስ ቅዱስን ስንሳደብ፥ (ማቴዎስ 12፡31፤ ማርቆስ 3፡29-30)።

እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራት የሚያስከትሉአቸው ነገሮች እጅግ አስጨናቂዎች ናቸው። ወደ ጨለማ፥ ተስፋ መቁረጥ፥ ወደ ኃጢአትና ጥፋት በሕይወትም ትርጉም ወደ ማጣት ያመጣሉ፤ (ዕብራውያን 6፡4-6፤ 10፡26-31)።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፡- «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» (ዕብራውያን3፡7)።

## ፈተና ቁጥር16

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥና በገጽ 83 ከሚገኙ ትክክለኛ መልሶች ጋር አመሳክር።

1. መንፈስ ቅዱስ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚሠራቸውን አራት ነገሮች ጥቀስ።

   1፡1.........................................

   1፡2.........................................

   1፡3.........................................

   1፡4.........................................

2. የመጀመሪያው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ምንድነው?

## 17. የእግዚአብሔር ሰዎች በሕይወት ውስጥ ያላቸው ዓላማ

በዘመናችን ያሉ አብዛኛዎቹ ሰዎች የእነርሱ መኖር ምንም አስፈላጊ እንዳልሆነ ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለሕይወት የሚሆን አዲስ ዓላማን ይሰጣል። ይህም ለእግዚአብሔር መኖርና ለዘለአለም በእርሱ ደስ መሰኘት ነው፤ (ሮሜ 14፡7-8)። እግዚአብሔር በቃሉ ምን እንደሚል እንመልከት፡-

1. እግዚአብሔር እርሱ እንድንፈልገውና እንድናገኘው ይፈልጋል

«ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፤» (የሐዋርያት ሥራ 17፡27)።

2. እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በክርስቶስ ለማዳን ይፈልጋል

«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው፤» (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡3-5)።

3. እግዚአብሔር ቅዱስ እንድንሆን ይፈልጋል

«ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን፤» (ኤፌሶን 1፡3-4)።

4. እግዚአብሔር እርሱን እንድንመሥል ይፈልጋል

«ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን፤» (2ኛ ጴጥሮስ 1፡4)።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን በአምሣያው ፈጥሯል፤ (ዘፍጥረት 1፡26)። ይህም በሥጋ ሳይሆን በጽድቅና በቅድስና ነው፤ (ኤፌሶን 4፡24)። እያንዳንዱ አማኝ «የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል ዕውቀትን ለማግኘት መታደስ አለበት፤ (ቆላስይስ 3፡10)፥ «ደግሞም የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናአል፤» (ሮሜ 8፡29)። ይህ ማለት መቼም ይሁን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንሆናለን ማለት አይደለም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች አባል የሆኑበትን የእግዚአብሔርን ቤተሰብ የበለጠ እየመሠሉ ይሄዳሉ።

ለአምልኮ በአንድ ላይ በምንሆንበት ጊዜ «ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤» (2ኛ ቆሮንቶስ 3፡18)።

5. እግዚአብሔር በምድር ላይ ምስክሮቹ እንድንሆን ይፈልጋል

እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን።

«..ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን፤» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡20)።

«..እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፤» (የሐዋርያት ሥራ1፡8)።

«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ... ናችሁ» (1ኛ ጴጥሮስ 2፡9)።

ይህ የሆነው እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲመጣ እንጂ እንዳይጠፉ ስለሚፈልግ ነው፤ (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)።

እነዚህ ነገሮች በሙሉ በእግዚአብሔር ቃል በአንድ ክፍል በጣም ጥሩ በሆነ ሁኔታ ተጠቃለው ቀርበዋል፤ (ኤፌሶን 1፡5-14)፡-

«በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ። በውድ ልጁም እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን። እርሱም የበደላችን ስርየት ፀጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን። በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳቡ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና በዘመን ፍፃሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው። እንደፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው። እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ። እርሱም የርስታችን መያዣ ነው። ለእግዚአብሔር ያለው ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።»

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር በዓላማ አንድ መሆንና ከእርሱ ጋር መስማማት የእያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን የዘወትር ዕቅድ ነው። ይህ ለእግዚአብሔር እራሳችንን የመስጠት ጉዳይ ማንነታችንን፥ አስተሳሰባችንን፥ ንግግራችንና ተግባራችንንም ሁሉ የሚነካ ነው። ፈቃዳችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን እግዚአብሔርን ልንታዘዘውና ደስ ልናሰኘው እንችላለን፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡9)።

## እራስን የመመዘኛ ሙከራ ቁጥር 17

ዋጋ ያለው ሕይወት ለመኖር መወሰድ ያለባቸውን አምስት ደረጃዎችን ጥቀስ። መልስህን በገጽ ... ከተሰጡት መልሶች ጋር አመሳክር።

1...............................................

2...............................................

3...............................................

4...............................................

5...............................................

# 18። የእግዚአብሔር ሕዝቦች የወደፊት ጉዳይ ዋስትና ያለው ነው

ውሸትና ዋስትና ማጣት በሞላበት በዚህ ዓለም ስለ ወደፊት ጉዳይ ሙሉ ዋስትና ማግኘት አስደናቂ ነገር ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሉ ዋስትናን ስለሰጠ ክርስቲያን ስለ ፍጻሜው ሊጠራጠር አይገባም።

**ዘላለማዊነት የተረጋገጠ ነው**

ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት እግዚአብሔር አንዳንድ እውነቶችን ገልጧል።

ሉቃስ 16፡19-31 አንብብ።

አልዓዛር ከሞተ በኋላ የሄደው ወዴት ነው? (ቁጥር 22።)................

በዚያ ሥፍራ ምን ደረሰበት? (ቁጥር 23።)........................

ሀብታሙ ሰው ከሞተ በኋላ ወዴት ሄደ? (ቁጥር 23።)..................

በዚያ ሥፍራ ምን ደረሰበት? (ቁጥር 24-25።)......................

የነበሩበትን ሥፍራ መለወጥ ይችሉ ነበርን? (ቁጥር 26።)...............

ልዩነት ሊያደርግ የቻለው የማን መልእክት ነበር? (ቁጥር 31።)...........

መልእክቱስ ምን ነበር? (ዮሐንስ 1፡45።).........................

ሰው ከሞተ በኋላ የሚሄድባቸው ሥፍራዎች ሁለት ብቻ ናቸው። እነርሱም መንግሥተ ሰማያትና ገሃነም በመባል ይታወቃሉ።

በመንግሥተ ሰማያት መሆን ማለት በእግዚአብሔር ፊት መሆን ማለት ነው። መንግሥተ ሰማያት አዲሲቷ ኢየሩሳሌም (ራእይ 21፡1-22፡6)፥ ገነት (ሉቃስ 23፡43)፥ ከክርስቶስ ጋር መሆን (ፊልጵስዩስ 1፡23፤ የሐዋርያት ሥራ 7፡55-60) ወይም የአብርሃም እቅፍ (ሉቃስ 16፡22) በመባል በተለያዩ ስሞች ይጠራል። የደስታና የመፅናናት ሥፍራ ነው። (ራእይ 21፡3-4።)

በሌላ አንገር ደግሞ ገሃነም፥ በዘላለማዊ እሳትነትና በቅጣት (ራእይ 20፡10፤21፡8፤ማቴዎስ 25፡41፥46፤ 13፡42፥50)፥ በኃዘንና በጨለማ (ማቴዎስ 25፡30)፥ ከጌታ ፊትና በሁሉን ቻይነት ከተሞላው ክብሩ ጨርሶ እንደመለየት ሆኖ (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡9) ተገልጿል።

**ፍርድ የተረጋገጠ ነው**

በምድር ላይ በኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ላይ የሚፈፀም ታላቅ የፍርድ ቀን ይመጣል። ይህ ቀን የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ሲመለስ ነው። ኢየሱስ እንዳለው

> «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ፥ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል። አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም

በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል ......! » (ማቴዎስ 25:31፤ 46)

ሮሜ 14:10-12 አንብብና የጎደሉትን ቃላት ሙላ:-

« .............. በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንን» ... .......... እንግዲያስ ............ ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን?» አንተም በዚያ ትሆናለህን?

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለዚያ ቀን በጣም ግልጽ የሆነ ራእይ ተሰጥቶታል።

ራእይ 20:11-15 አንብብ።

በዙፋኑ ፊት የሚቆመው ማን ነው? (ቁጥር 12።)......................

እነዚህ ሰዎች ከየት የመጡ ናቸው? (ቁጥር 13።)......................

የሚፈረድባቸውስ ከምን አኳያ ነው? (ቁጥር 13።)....................

የተኮነኑት እነማን ናቸው? (ቁጥር 15።)........................

በሕይወት መጽሐፍ ስማቸው የተፃፉት ሰዎች (ራእይ21:27) ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአታቸውን ዋጋ በመስቀል ላይ እንደከፈለላቸው በማመን በምስጋና የተቀበሉትና በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ምሕረት ያገኙ ናቸው፤ (ዮሐንስ 3:18፤ 5:24፤ሮሜ 8:1)። ካለዚህ እምነት የሚደረጉ ራስን መካድ መልካም ሥራዎች በሙሉና ጸሎት ዋጋ የላቸውም።

> «እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።» (1ኛ ዮሐንስ 5:11-12።)

## ደኅንነት የተረጋገጠ ነው!

አንድ ክርስቲያን «ስለ ደኅንነት» ሲናገር ከፍርድ ቀን ስለ መዳን መናገሩ ነው። ምክንያቱም ኃጢአቱ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ይቅር ተብሏል። ክርስቲያን ሞትን አይፈራም። ምክንያቱም ይህ ለእርሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግቢያ በሩ ነው። ከጳውሎስ ጋር በአንድነት እንዲህ ይላል «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና!» (ፊልጵስዩስ 1:23።)

ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድ ይገባኛል፤ መብቴ ነው፤ የምትል ብትሆን ኖሮ መቼም እርግጠኛ መሆን አትችልም ነበር። ይቅር ያልተባለ አንድ ኃጢአት እንኳ ቢኖርብህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ብቁ አይደለህም፤ (ራእይ 21:27)።

አሁን ግን ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ሁሉ በሥጋው በመስቀል ላይ ስለተሸከመልን (1ኛ ጴጥሮስ 2:24፤ ኢሳይያስ 53:5-6)፥ ለሙሉ ይቅርታ መንገዱን ከፍቶልናል።

> «ስለበደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ባስነሣው ለምናምን፥ እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ በእርሱ ደግሞ ወደቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል። በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። ይልቁንም እንግዲህ አሁን በደሙ ከፀደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን። ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም። ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፤» (ሮሜ 4፡25፤5፡1-2፥ 9-11)።

ክርስቲያን በመንግሥተ ሰማያት የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ያለው ዋስትና በባሕርይው ወይም በሕይወት ብቃቱ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ነገር ግን በእምነት በተቀበለው በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ብቻ ነው። እምነትንም ያደረገው ቀጥሎ ያለውን ቃል በተናገረው በኢየሱስ ላይ ነው፡-

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል። እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም፤» (ዮሐንስ 10፡27-28)።

ዋስትናው የእግዚአብሔር ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚመጣ ነው።

1ኛ ዮሐንስ 5፡13 በማንበብ የጎደለውን ቃል ሙላ፡-

«የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ............ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላቸዋለሁ።»

በእንደዚህ ዓይነቱ ታላቅና አፍቃሪ አምላክ ፊት ትሕትና በተሞላበት ምስጋና «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን እናውቃለን» (1ኛ ዮሐንስ5፡19-20) ለማለት እንችላለን።

ፈተና ቁጥር 18

ከእያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር አጠገብ እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጥና መልስህን በገጽ 83 ከተሰጠው ትክክለኛ መልስ ጋር አመሳክር።

1. ማንኛውም ሰው ለኃጢአቱ ይቅርታን ለማግኘቱ እርግጠኛ መሆን አይችልም።

................

2. ገሃነም ጊዚያዊ ቅጣት ነው። ................

3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ሁሉ ላይ ይፈርዳል። ................

4. የክርስቲያን ዋስትና በመልካም ሥራ ላይ የተደገፈ ነው................

5. ይቅር ያልተባለ አንድ ኃጢአት ብቻ እንኳ ከመንግሥተ ሰማያት ያስቀራል ................

# ማጠቃለያ

ይህንን መጽሐፍ ለማጥናት ሠፊ ጊዜህን ስለሰጠህ እናመሰግናለን። እዚህ ገጽ ለመድረስ ብዙ ደክመሃል። በጣም ጥሩ አደረግህ!

ያጠናኸው ግን ሌላ ሃይማኖት ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስህን ስታነብ የክርስትናን እምነት በአዲስ መንገድ ተረድተሃል። መጽሐፍ ቅዱስ የያዛቸው ነገሮች ያለጥርጥር ልንታመንባቸው የምንችልባቸው መሆናቸውንና መልእክታቸውም ተግባራዊ የሚሆኑ መንፈሳዊና በጣም ግሩም መሆናቸውን ተረድተሃል። ከዚህ ቀደም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሰማኸው ነገርና አሁን የተማርከውን ነገር ለማወዳደር ከመድፈርም አላመለጥክም።

አሁን ውሳኔ ወደማድረጊያው ደርሰሃልና መወሰን አለብህ። ስሜታዊ ሳትሆን እራስህን በመግዛት የምትሰጠው ውሳኔና የምታደርገው ምርጫ የዘላለም ሕይወትና ሞት ጉዳይ ነው።

በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ እንደተዘረዘረው የእግዚአብሔርን ምሕረት በኢየሱስ በኩል የመቀበል ዋጋው ምን እንደሆነ ትኩረት ሰጥተህ ተመልክተኸው ይሆናል። ዋጋው በጣም ከፍተኛ እንደሆነም ተገንዝበሃል። ኢየሱስ ዋጋቸውን ተምነው እርሱን የሚከተሉትን ሰዎች ያበረታታል፤ (ሉቃስ 14፡27-33፤ ማቴ 16፡24-26)።

ለአንድ ነገር የተሰጠውን ዋጋ በምትመለከትበት ጊዜ ያንን ዋጋ ከፍለህ ከምታገኘው ነገር ጋር ታወዳድረዋለህ። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ለመፍጠር አንድ ሰው ምን ያህል ዋጋ መክፈል ይችላል? ኃጢአታችን በሙሉ ይቅርታ አግኝቶ አዲስና ንፁሕ የሆነ ሕይወትን ለመጀመር ለመክፈል የተዘጋጀነው ዋጋ ምን ያህል ነው?

ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?» (ማቴዎስ 16፡26።)

ከቤተሰብህ ዘንድ ስለሚደርስብህ ነገር ስታስብ ይህንን መጽሐፍ ከአንተ ጋር የሚያጠኑበትን መንገድ ማሰቡም አስፈላጊ ነው። አንድ ቤተ ሰብ ኢየሱስን በመቀበል ከእግዚአብሔር ሰላምን መሻቱና ማግኘቱ ያለ ነገር ነው። ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡-

> «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል!» (ራእይ 3፡20)።

እግዚአብሔር እውነቱን ለማየት እንዲያስችልህና በእምነት ያንን በር እንድትከፍት እንዲረዳህ እንጸልያለን። ይህንን ውሳኔ ለራስህ አድርግ። ማንም ሰው ተፅዕኖ ሳያደርግብህ ያለህበትን ሥፍራ መርምር። እግዚአብሔርንና ቃሉን ብቻ ታዘዝ በዚህ ጥናት መጽሐፍ ውስጥ አልተመለሰም ብለህ የምታስባቸው ጥያቄዎች ካሉ እባክህን ጻፍልን።

ውሳኔህ ምንም ይሁን ምን ውሳኔህንና ወደዚህ ውሳኔ የደረስክበትን ምክንያት አሳውቀን። ሁሉን የሚችልና ዘለአለማዊ አምላክ ለእርሱ በውነት መታዘዝና እራስህን መስጠት ትችል ዘንድ ጥበብንና ማስተዋል ይስጥህ!

አሁን የዚህን መጽሐፍ ጥናት የመጨረሻ ፈተና ከመጽሐፉ ላይ አውጣና ሠርተህ በፖስታ ቤት ላከው።

## የፈተናዎቹ ትክክለኛ መልሶች

### ፈተና ቁጥር1

1. ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን

2. 66

3:1 የሙሴ መጻሕፍት

3:2 የታሪክ መጻሕፍት ዘገባዎች ይሆነን

2:1 መሢሕ እንደነበር

3:3 የግጥምና የቅኔ መጻሕፍት

3:4 የትንቢት መጻሕፍት

4:1 የታሪክ መጻሕፍት

4:2 የማስተማሪያ ደብዳቤዎች (መልእክቶች)

4:3 የትንቢት መጻሕፍት

### ፈተና ቁጥር 2

1. የመጽሐፉ ደራሲ እግዚአብሔር ነው

2:1 በቀጥታ ንግግር

2:2 በሕልሞች ወይም በራእዮች

2:3 በነቢያት በኩል

2:4 በታሪካዊ ክስተቶች

### ፈተና ቁጥር 3

1. ትንቢቱ በትክክል መፈጸም አለበት

2. መረጋገጥ ስለሚችል ነው

3. ኢየሱስ ክርስቶስ

### ፈተና ቁጥር 4

1:1 የተፈጸሙ ትንቢቶችን ይዟል

1:2 የዓይን ምስክሮችን ዘገባ ያካትታል

1:3 ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ታሪካዊ ጉዳይ ያረጋግጣሉ

2:2 ከሞት የተነሣ መሆኑን

### ፈተና ቁጥር5

1:1 በፍጥረት ሥራ

1:2 በታሪክ

1:3 በሰው ኅሊና

1:4 ከቅዱሳት መጻሕፍት

1:5 በኢየሱስ ክርስቶስ

### ፈተና ቁጥር 6

1. በእግዚአብሔር አምሳል

2. እንድትታዘዛቸው

3.1 በእግዚአብሔርና በሰው

3.2. በሰውና በሚስቱ

3.3 በሰውና በተፈጥሮ

4. ምንም ተጽዕኖ አይደርስበትም

### ፈተና ቁጥር 7

እውነት 2፥3፥5

ሐሰት 1፥4

4፡1 አይሁዶች ቅዱሳት መጻሕፍትን

4፡2 አንዳንድ ትርጉሞች

ከክርስቶስ በፊት ተሠርተው ነበር

4፡3 ከክርስቲያኖች በፊት የነበሩ አንዳንድ

የእነዚህ ትንቢት ቅጂዎች እስካሁንም

ስላሉ ነው

ፈተና ቁጥር 8

1፡1 ኃጢአት ምን እንደሆነ ሲያሳየን

1፡2 ሊጠብቀን

2. አንድ ብቻ

3. አይደለም

4. የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ አንችልም

5. አስተሳሰቦች

ፈተና ቁጥር 9

1. የእግዚአብሔር በግ

2፡1 ማስተማር

2፡2 ተአምራትን ማድረግ

2፡3 ሥልጠና መስጠት

3. ያለ ኃጢአት ነበር

ፈተና ቁጥር 10

እውነት፥ 1፥3

ሐሰት፡- 2፥4፥5

ፈተና ቁጥር11

እውነት 2፥4

ሐሰት፡- 1፥3፥5

ፈተና ቁጥር 13

እውነት፡- 2፥5

ሐሰት፡- 1፥3፥4

ፈተና ቁጥር 14

1. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው

2. የእግዚአብሔር ልጅ

3. ጌታዬና አምላኬ

4. አንድ

5. ዓለም ከመፈጠሩ በፊት

ፈተና ቁጥር 15

1. አንድ

2. በእግዮች መካከል ለመኖር

ይመጣል

3. የበዓለ ሃምሣ ቀን

4. «ሥላሴ»

5. አንድ የተለየ ተግባርን ይፈጽም

ዘንድ ለማስቻል

ፈተና ቁጥር 16

1፡1ስለኃጢአት ይወቅሳል

1፡2 አዲስ ልደትን ይሰጣል

1፡3 ዋስትናን ይሰጣል

1፡4 ሰዎች እግዚአብሔርን

## ፈተና ቁጥር 12

1. ፈተና
2. መንፈሳዊ
3. በመቀበል
4. ያለ ኃጢአት
5. ካመንክ

## ፈተና ቁጥር 17

1. እግዚአብሔርን መፈለግና ማግኘት
2. በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መዳን
3. ለመቀደስ መጣር
4. ክርስቶስን ለመምሰል መጣር
5. ለክርስቶስ ምስክር መሆን

ለመታዘዝ እንዲችሉ ይረዳቸዋል

2. ፍቅር

## ፈተና ቁጥር 18

እውነት:- 3፥5

ሐሰት:- 1፥2፥4